26ኛ ዓመት ቁጥር 18
26ndYear No. 18

ባሕር ዳር ጥር 15 ቀን 2014 ዓ.ም
Bahir Dar, January 23, 2022

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## of the Council of the Amhara National Region in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the Auspices of the Council of the Amhara National Region

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 2416.38 ብር
Unit PriceBirr 2416.38

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር 280/2014 ዓ.ም**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የአስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ

**Content**

**Proclamation No. 280/2021**

The Revised Executive Organs Re-Establishment and Determination of its Powers and Duties Proclamation in the Amhara National Regional State

## አዋጅ ቁጥር 280/2014 ዓ.ም

### በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የአስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በሀገራችን የተቀጣጠለውን ለውጥ ተከትሎ በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን ፈርጀ-ብዙ እንቅስቃሴ ቅቡልነትና ዘላቂነት ለዚሁ በሚመጥን ተቋማዊ የማሻሻያ እርምጃዎች ማጀብና መደገፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No. 280/2021

### The Proclamation Issued to Establish and Determine the Powers and Duties of the Revised Executive Organs in the Amhara National Regional State

WHEREAS, it is found necessary to escort and support the acceptance and sustainability of multi-sectormovements, being taken place in the region-following the change wave which started in our country, with institutional reform measures that fit for this purpose;

በሀገሪቱ የተነደፈውን የአስር ዓመት የልማትና የመልካም አስተዳደር እቅድ በብሔራዊ ክልሉ ልማት ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ድርሻ በዓይነትም ሆነ በመጠን ከፍ ለማድረግና የሕዝቡን የላቀ ተሳትፎ ይበልጥ በማሳደግ ፍትሐዊ የልማት ተጠቃሚነቱን በተጨባጭ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን እውን በማድረግ ማሕበራዊ ልማትን በማስፋፋትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ክልሉ ያለውን እምቅ ሰብዓዊና ቁሳዊ አቅም ተጠቅሞ ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን መፍጠር በማስፈለጉ፤

በክልሉ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ዋነኛ ተዋናዮች የሆኑ የልማት ሀይሎችና ዘርፎች በልማቱ ውስጥ በሙሉ አቅማቸው እንዲረባረቡ ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክልሉ ውስጥ የተቋቋሙት የተዋረድ አስተዳደር እርከኖች እርስበርስ ተቀናጅተው የሚመሩበትን ሥርአት ከማዘመን ጎን ለጎን የክልሉ ኢኮኖሚ ስፋት፣ ውስብስብነትና ፍጥነት በሚጠይቀው መጠን መንግሥታዊ ተቋማትን ፈትሾ እንደገና ለማደራጀት፣ በብቃት ለመምራትና ለመደገፍ የሚያስችል ቁመና ያለው ተቋም እውን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በክልሉ ውስጥ የሀብት ብክነትን የሚቀንስና ውጤታማነትን የሚያረጋግጥ፣ ተጠያቂነትን የሚያጎለብት፣ እርስበርስ ተናቦና ተቀናጅቶ መሥራትን የሚያበረታታ፣ ክልሉ ያለውን የተፈጥሮ ጸጋ በሚገባ አልምቶ የሕዝቡን ከድህነት የመውጣት ፍላጎት የሚያሳካና ብልጽግናን እውን ለማድረግ የሚያግዝ ተቋማዊ ባህል መፍጠር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whreas, it is found necessary to practically ensu development beneficiary of the people th enabling the National Regional developmentto its share both in kind and quantity and enhan peoples' greater participationon the ten development and good administration plan form at the national level;

Whereas, it is needed to create conducive co that enables the region to ensure susta development using its human and material pot by promoting social development and securing governance through realizing basic economic stru change;

Whereas, it is found necessary toenable develo powers and sectors, who are main actors i development mobilization in the region, to take their full potencial;

Whereas, it is needed to realize institutions effectively lead and support re-organizing institutions requiring the region's wide eco complexity and expedition side-by-side mode the bottom administration levels' integrated l system in the region;

Whereas, it is found appropriate to create instit culture in the region helping to decreasing r wastage and securing success,strengt accountability, encouraging mutual and int working, secceeding to lift the people from through developing properly the region's resource, and realizing prosperity;

በአስር ዐመቱ የልማት እቅድ ውስጥ የተለየ ትኩረት የተሰጣቸውን ተልእኮዎች በማሳካት፣ የውድድር መንፈስን በመፍጠር፣ ብቁ ተቋማትን በማፍራት፣ እርስበርስ የተሳሰረ አቅም በመገንባትና ለሕዝቡ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት፣ የዕዝ ሰንሰለቱን አሳጥሮ ተገልጋዩን ሕብረተ-ሰብ የሚያረካና አስፈጻሚ አካላት በውስን ወጪ ጥራት ያለው የተቀላጠፈ ውሳኔ እንዲሰጡ በማበረታታት የሥራው አካልና ባለቤቶች እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለዚህም ያመች ዘንድ የማደግና የመበልጸግ እሳቤ ያለውና በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተቃኘ ሰብአዊ ሀብት ማፍራትና ይህንኑ በጠንካራ ተነሳሽነት ፈጥኖ ወደሥራ ማስገባት አንገብጋቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህንኑ መነሻ በማድረግ እርስበርስ ተመጋጋቢና ተያያዥ ባሕርይ ያላቸውን የተበታተኑ የሥራ ዘርፎች አሰባስቦ በአንድ አስፈጻሚ አካል ስር ከማጠቃለል ጎን ለጎን የክልሉን ዓላማ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ለልማቱ መፋጠንና ለዴሞክራሲያዊ ሥርአቱ መጎልበት ባላቸው ተጨባጭ እርባና ላይ በመመሥረት ቁልፍ የትኩረት መስኮቻቸውን ከወዲሁ ለይተው በነዚሁ ላይ ይበልጥ እንዲረባረቡና ለአመርቂ አፈጻጸም እንዲተጉ የሚያስችላቸውን አደረጃጀት የመፍጠሩ አስፈላጊነት ስለታመነበት፤

Whereas, it is found necessary to make the executive organs part and owner of the work through seceding specially focused missions given in the ten year's development plan, creating competitive spirit, building powers integrated eachother and giving expedicious and successful services, and encouraging the executive organs to give quality and instant decision that satisfies the people with less cost shortening the command chain;

Whereas, it is found a burning issue to build human resource inculcated in prospering and democratic thought and engaging it into work in strong initiation for the sake of sameabove;

Whereas, it is belived in creating structuresenabling the regional executive organs to better participate and work tirelessly to satisfying implementation pre-identifying key focus areas of the region's objective implementing offices based on their concrete importance to fostering for the development and strengthening the democratic system side-by-side of merging drifted subsequent and similar work sectorsinto one executive organ based on sameabove;

በሥራ ላይ ያለው የክልላዊ መንግሥቱ አወቃቀር ለአዳጊና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት ይቻለው ዘንድ አስፈጻሚ አካላቱን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌደራል መንግሥቱ አቻዎቻቸው ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን የሥራ ቀረቤታ፣ የተልእኮ ትስስርና እርስ በእርስ ተናቦና ተቀናጅቶ የመሥራት ፋይዳ ታሳቢ አድርጎ እንደገና በመቃኘትና ዝርዝር የሥራ ድልድላቸውን በመከለስ አንጻራዊ ማስተካከያ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከዚሁ በመነጨ አመክንዮ ቀድሞውኑ ከተቋቋሙበት ተልዕኮ ጋር የተገናዘበ የኃላፊነት ሽግሽግም ሆነ የተጠሪነት ለውጥ ሊደረግባቸው የሚገቡትን አንዳንድ የክልሉን መንግሥታዊ ተቋማት በውል ለይቶና ነባር አደረጃጀቶቻቸውን ፈትሾ ከፌደራሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት አወቃቀርና የሥልጣን ድልድል ጋር ማጣጣምና ለሀገራዊው የጋራ ግብ ስኬት እርስበርሳቸው ተደጋግፈውና ተቀናጅተው የሚሠሩበትን የተሳለጠ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እንደሚገባ በመታመኑ፤

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1)ድንጋጌ ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 280/2014 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።



WHEREAS, it is necessary to to make relative correction on the Structure of the existing Regional State by surveying and revising the Work Redeployment of the Executive Organs in consideration of the would be work relationship, mission integration and working in line with their concerned Federal Bodies so as to enable them to give seasonal response for progressive and changeable situations;

WHEREAS, on the basis of this logic, it is believed that to accommodate some regional state institutions those need a shift of responsibilities as well as change of accountability in comformity with their prior establishment objectives and to clearly provide for the legislation of their organizational set up to possibly harmonize with the executive organs structure and authority redeployment of the federal government and thereby to create a speedy system in which they would support each other for the common objective of the nation;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region in accordance with the powers Vested in it under Article /49/ sub Articles 3/1/ of the revised Constitution of the National Regional State, here by issued this proclamation.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as "**the Amhara National Regional State Revised Executive Organs Re-Establishment and Determination of its Powers and Duties Proclammation No. 280/2021**."

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ�:-

1) **"ቢሮ"** ማለት በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ የተቋቋመና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባል የተደረገ የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ መሥሪያ ቤት ነው፤

2) **"የቢሮ ኃላፊ"** ማለት የዚሁ መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ሆኖ እንዲያገለግል በሕገ-መንግሥቱ መሠረት የተሾመ ወይም የሚሾም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

3) **"ምክር ቤት"** ማለት የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን እንደተገቢነቱ የየርከኑን አስተዳደር ምክር ቤቶችን ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ርዕሰ-መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ-መስተዳድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

### 3. ስለ ርዕሰ-መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

የአማራ ክልል ርዕሰ-መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 60 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል፡፡

### 4. ስለ ምክትል ርዕሰ-መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

የአማራ ክልል ምክትል ርዕሰ-መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 61 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል፡

## 2. Definitions

In this proclamation, unless the context rquires otherwise:

1) "**Bureau**" shall mean an executive office established or to be established as per this proclamation or any other laws and having become member of the Council of Regional Government thereof;

2) "**Head of Bureau**" shall mean any natural person appointed or to be appointed to serve in such an executive office pursuant to the provisions of the constitution;

3) "**Council**" shall mean the council of the National Regional Government which may as appropriate, include those administrative councils at various levels.

## PART TWO

## THE HEAD OF GOVERNMENT, DEPUTY HEAD OF GOVERNMENT AND THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT

### 3. Powers and Duties of Head of Government

The Powers and Duties of the Head of Government of the Amhara National Regional State shall be those stipulated under the provisions of Article 60 of the Revised Regional Constitution.

### 4. Powers and Duties of Head of Government

The powers and duties of the Deputy Head of Government of the Amhara National Regional State shall be those stipulated under the provisions of Article 61 of the revised Regional Constitution.

## 5. ስለ ምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 58 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል፡፡

## 6. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል፦

ሀ/ ርዕሰ-መስተዳድሩ፤

ለ/ ምክትል ርዕሰ-መስተዳድሩ፤

ሐ/ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የተሾሙ የክላስተር አስተባባሪዎች፤

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ሥር የተመለከቱትን አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የሚመሩ የበላይ ኃላፊዎች፤

ሠ/ በርዕሰ-መስተዳድሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለሥልጣናት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (መ) ድንጋጌ ሥር የተመለከተው የትኛውም የቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በተለየ ሁኔታ በጽሑፍ ካልወከለ በስተቀር በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ይሣተፋል፡፡

## 7. ስለ ምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት

1) የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር በተደነገገው መሠረት የርዕሰ-መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት ይሆናል፤

## 5. Powers and Duties of the Council

The powers and duties of the council of the Amhara National Regional Government shall be those stipulated under the provision of Article 58 of the Revised Regional Constitution.

## 6. Members of the Council of the Regional Government

1) The Council of the Regional Government shall have the following members as bellow:

A/ The Head of Government;

B/ The Deputy Head of Government;

C/ Cluster Coordinators to be assigned in the Deputy Head of Government Status;

D/ Those superintendents in charge of the Bureaus as are enumerated under Article 10 of this proclamation;

E/ Other officials to be assignated by the Head of Government.

2) Whenever any one of the Head of Bureau indicated under Sub-Article 1/D/ of this Article hereof, is unable to attend sessions of the council, the Deputy Head of Bureau having seniority in appointment shall so participate in such sessions provided that no other delegations have been conferred before in writing on exceptional grounds.

## 7. Office of the Council of the Regional Government

1) The office of the Council of the Regional Government shall be the office of the Head of Government indicated under the provisions of Article 62 sub article /2/ of the Revised Regional constitution.

2) ጽሕፈት ቤቱ የሚኖረው ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር ይህንን አዋጅ ተከትሎ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፤

3) የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በቢሮ ኃላፊ ማዕረግ የሚሾም ሆኖ፡-

ሀ) የምክር ቤቱን ጉዳዮች በበላይነት ያስፈጽማል፤

ለ) በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ያለድምፅ ይሳተፋል፣ ሐሣብና አስተያየትም ይሰጣል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥር የሰፈሩት ድንጋጌዎች የበታች የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቶችንም ሆነ ኃላፊዎቻቸውን አስመልክቶ በተመሳሳይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

## 8. ስለ ምክር ቤቱ የመሰብሰቢያ ጊዜ፣ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓትና አመራር

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት፡-

ሀ) ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤

ለ) ምልአተ-ጉባኤ የሚሆነው ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ሲገኙ ይሆናል፤

ሐ) ምክር ቤቱ ውሳኔዎችን የሚያሳልፈው በተባበረ ድምፅ ይሆናል፤ በተባበረ ድምጽ መወሰን ካልተቻለ ግን ጉዳዩ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይወሰናል።



2) The detailed powers and duties of the council shall be determined by the regulation to be issued following this proclamation.

3) To be appointed at the status of Head of Bureau, the Head of the office shall:

A/ direct over the execution on the council affairs;

B/ attend, without vote, the council sessions as well as render suggestions and opinions.

4) The provisions of sub-article /1/ and /2/ of this article hereof shall, mutatis mutandis apply to the subordinate administrative offices as well as their respective Heads.

## 8. Meeting Time, Procedure and Chairing of the Council

1) The Council of the Regional Government shall:

A/ The details being specified in a regulation, undertake ordinary and extra ordinay sessions;

B/ The quorum in this regard shall require the presence of more than half of its members at the meeting;

C/ Its decisions shall be passed by acclamation, provided that they may be taken by a majority vote in default of same.

2) የምክር ቤቱ አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ-መስተዳድሩ፡-

ሀ/ ለምክር ቤቱ የመወያያ አጀንዳ ሆነው የሚቀርቡትን ጉዳዮች ይለያል፣ ይወስናል፤

ለ/ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፤

ሐ/ ለምክር ቤቱ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ የቀረበ ማናቸውም ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ በኩል መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ሲያገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል፡፡

3) ርዕሰ-መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ምክትል ርዕሰ-መስተዳድሩ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡

## 9. ስለመስተዳድር ምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት ይረዱት ዘንድ የሚቋቋሙና የምክር ቤቱ አባላት የሚታቀፉባቸው ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፤

2) የነዚህ ቋሚ ኮሚቴዎች ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

# ክፍል ሶስት

# ስለቢሮዎች በጠቅላላው

## 10. ስለ መቋቋም

የሚከተሉት የክልሉ አስፈጻሚ አካላት በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-



2) Without prejudice to the rights of the members of the Council of the Regional Government to submit an agenda, the Head of Government shall:

A/ identify and decide on the agenda submitted to the council;

B/ preside over the councils meeting;

C/ postpone the meeting if he finds out that a given agenda is subject for consideration by the standing committee of the council concerned.

3) In the absence or inability of the Head of Government, the deputy Head of Government shall, in his place, preside over the meetings of the council.

## 9. Standing Committees of the Administrative Council

1) The council of the regional government shall have various standing committees comprising of the council members with the view to assisting discharge its responsibilities.

2) The details of the functions and responsibilities of these standing committees shall be determined by a directive to be issued by the council in accordance with this proclamatuiion.

# PART THREE

# ABOUT BUREAUS IN GENERAL

## 10. Establishment

The following bureaus are hereby established by this proclamation:

1) የግብርና ቢሮ፤
2) የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ፤
3) የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ፤
4) የመሬት ቢሮ፤
5) የከተሞችና መሠረተ-ልማት ቢሮ፤
6) የውኃና ኢነርጂ ቢሮ፤
7) የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ፤
8) የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ፤
9) የመንገድ ቢሮ፤
10) የሥራና ሥልጠና ቢሮ፤
11) የገንዘብ ቢሮ፤
12) የገቢዎች ቢሮ፤
13) የትምህርት ቢሮ፤
14) የጤና ቢሮ፤
15) የፍትሕ ቢሮ፤
16) የሰላምና ጸጥታ ቢሮ፤
17) የቱሪዝም ቢሮ፤
18) የሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤
19) የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፤
20) የፕላንና ልማት ቢሮ፤
21) የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን፤
22) የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ፤
23) የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለሥልጣን፡፡

## 11. ስለ ቢሮዎች የወል ሥልጣንና ተግባር

1) እያንዳንዱ ቢሮ በየሥራ መስኩ፡-

ሀ/ የፌደራል መንግሥቱን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች መሠረት ያደረጉና የክልሉን ነባራዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ክልል-አቀፍ ፖሊሲዎችን፣



1) Bureau of Agriculture;
2) Bureau of Industry and Investment;
3) Bureau of Trade and Market Development;
4) Bureau of Land;
5) Bureau of Urbans and Infrastructure;
6) Bureau of Water and Energy;
7) Bureau of Irrigation and Lowland Areas Development;
8) Bureau of Mineral Resource Development;
9) Bureau of Road;
10) Bureau of Work and Training;
11) Bureau of Finance;
12) Bureau of Revenues;
13) Bureau of Education;
14) Bureau of Health;
15) Bureau of Justice;
16) Bureau of Peace and Order;
17) Bureau of Tourism;
18) Bureau of Women, Children and Social Affairs;
19) Bureau of Youth and Sport;
20) Bureau of Plan and Development;
21) Comission of Civil Service and Human Resource Development;
22) Bureau of Government Communication;
23) Authority of Environment and Forest Protection.

## 11. Collective Powers and Duties of the Bureaus

1) Each and every bureau, in connection with its sphere of activities, shall:

A/ initiate regional policies, strategies and laws based on those policies and programs of the Federal Government and having due regard to the

ስትራቴጅዎችንና ሕግጋትን ያመነጫል፣ የሥራ እቅድና የማስፈጸሚያ በጀት ረቂቆችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የክልሉንና የፌደራሉን መንግሥታት ሕጎችና ደንቦች በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) አግባብ ካለው የክልሉ መንግሥት አካል ጋር በመመካከር የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

መ) እንዳስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ የራሱን የበታች አደረጃጀቶች ይፈጥራል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ መሰል አደረጃጀቶች እንዲቋቋሙላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡለትም ለብሔረ-ሰብ፣ ለወረዳዎችና ለከተማ አስተዳደሮች ተገቢውን ድጋፍና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

ሠ) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በውስጡ የሚታዩትን የአቅም ክፍተቶች ይለያል፣ በወቅቱ የሚሞሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ረ) በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄደውን ሁለንተናዊ ልማት ለማፋጠንና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን ለማሳካት የተቀረጹ ልዩ ልዩ የማሻሻያ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ከመሥሪያ ቤቱ ተልእኮና ፍላጎት ጋር በተጣጣመ መንገድ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

objective realities of the regional state as well as prepare work plan along with the budget proposal and implement same upon approval;

B/ implement the federal and regional laws and regulations throghout the regional state;

C/ in collaboration with pertinent bodies of the region, perform research activities; collect, compile and analyze information and distribute same to the pertinent bodies;

D/ create, as may be necessary, its subordinate structures throughout the region, follow up and monitor their activities as well as provide the appropriate support and advisory services to the nationality, wereda and city administrations when requested to assist them in the establishment of their own similar structures;

E/ in collaboration with pertinent bodies, identify capacity gaps seen in it, facilitate conditions to fill the gaps in time;

F/ cause the designed different programs and projects be implemented in line with the ofice's mission and demand to foster the overall development and to realize the democratic building system that is taken place in the country;

ሰ) ከተግባርና ኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ዝርዝር የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፤

ሸ) ለየሥራ ዘርፉ ባለው ተገቢነት ላይ አተኩሮ የሴቶችን፣ የሕፃናትን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋውያንን ሕገ-መንግሥታዊ እኩልነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የነዚህን የሕብረተ-ሰብ ክፍሎች ጉዳይ በዕቅድ አካቶ ይሠራል፤

ቀ) በሕግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ስምምነቶችን ያደርጋል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡

2) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 ወይም በየማቋቋሚያ ሕጎቻቸው ስር በተደነገገው መሠረት ተጠሪዎች የተደረጉለትን አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች፣ ተቋማትና ድርጅቶች አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፣ አደረጃጀቶቻቸውንና የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን መርምሮ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት አካላት ቀርበው እንዲወሰኑ ያደርጋል፤

3) በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

4) የሥራ ክንውንን በተመለከተ ወቅታዊ ዘገባዎችን እያዘጋጀ ለርዕሰ-መስተዳድሩና ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

G/ may issue detailed implementation directives in relation to its own powers and duties;

H/ emphasize on the appropriate sector to the work that shall ensure enabling constitutional equality and beneficiary of the women, children, youths, disableds and elders, and work for these persons by mainstreaming their issue in the plan;

J/ enter into contracts pursuant to law, own property, conclude agreements, sue and be sued in its own name.

2) It shall direct the overall implementation of the executive offices, institutions and organizations they are made accountable pursuant to the provisions of Article 37 of this proclamation or their respective establishment laws; coordinate their works as well as examine their structures and operational programs prior to the decision that such be submitted for approval to the pertinent body of the regional government;

3) It shall implement the specific powers and duties as are provided for it in this proclamation and other laws;

4) It shall submit periodic reports to the Head of government and the Council in respect of the performance of its duties.

## 12. የቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነትና ተግባር

እያንዳንዱ የቢሮ ኃላፊ፡-

1) ተጠሪነቱ ለርዕሰ-መስተዳድሩና ለምክር ቤቱ ይሆናል፤
2) የሚመራውን ቢሮ ይወክላል፣ ሥልጣንና ተግባራቱን በሥራ ላይ ያውላል፤
3) ለቢሮው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤
4) በቢሮው ውስጥ ውጤታማ የሥራ አመራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል።

## 13. የምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነትና ተግባር

1) እያንዳንዱ ምክትል የቢሮ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለሚመለከተው ቢሮ ኃላፊ ሆኖ በዚሁ የበላይ ኃላፊ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

2) የቢሮ ኃላፊው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል፤

3) በማናቸውም ቢሮ ውስጥ የሥራው መጠንና ውስብስብነት የሚጠይቅ ሆኖ ከመገኘቱ የተነሣ ከአንድ በላይ የሆኑ ምክትሎች በሚገኙበት ጊዜ የቢሮ ኃላፊው በተለይ የጽሑፍ ውክልና የሰጠው ሰው መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር እርሱን ተክቶ ቢሮውን የሚመራው በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል የቢሮ ኃላፊ ይሆናል።



## 12. Accountability and Duty of the Heads of Bureau

Each and every head of bureau shall:

1) Be accountable to the Head of Government and to the council;

2) Represent the Bureau under his leadership and implement its powers and duties;

3) Effect expenditures in accordance with the work program and budget approved for the Bureau;

4) Put in place an effective management system in the Bureau is implemented and follow up its observance thereof.

## 13. Accountability and Duty of the Deputy Heads of Bureau

1) Each and every Deputy Head of Bureau shall, being accountable to the Had of Bureau concerned, carry out such duties as are specifically assigned to him by this Head;

2) He shall replace and act on behalf of the Bureau in the absence and inability of the Head of Bureau to carry out the tasks;

3) Whenever there is more than one Deputy in a Bureau due to the requirement of the amount and complexity of work, the Deputy Head of Bureau having seniority in appointment, shall so lead the Bureau replacing him, provided that no other delegations have been conferred before in writing on exceptional ground.

## ክፍል አራት

## ስለ ቢሮዎች ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር

### 14. የግብርና ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ግብርና ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የአገሪቱን የግብርና መር ፓሊሲና ስትራቴጂ መሠረት ያደረጉ የክልሉን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂካዊ ዕቅዶችና ኘሮግራሞች ያዘጋጃል፣ ይፈጽማል፣ በክልሉ ውስጥ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
2) ለአርሶ-አደሩ የኤክስቴንሽን አገልግሎትና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣ ለምርምር አገልግሎት የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤
3) የሰብልና የእንስሳት በሽታዎችን፤ ፀረ-ሰብል ተባዮችን እና አረሞችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የማቴርያልና የቴክኒክ እገዛ ይሰጣል፤
4) በምርምር የተገኙ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ያቀርባል፣ ያላምዳል፣ ኘሮቶታይፓችን ያመርታል፣ እንዲመረቱ በማድረግ ያሰራጫል፤
5) በግብርናዉ ዘርፍ መዋእለ-ንዋያቸውን ማፍሰስ ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች ተገቢውን መረጃና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤



## PART FOUR

## Specific Powers and Duties of the Bureaus

### 14. Bureau of the Agriculture

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Agriculture shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Prepare and implement the short, medium and long term strategic plans and programs of the region on the basis of the country's agricultural-lead-into industrialization policy as well as cause the promotion of rapid and sustainable agricultural development;
2) Avail extension service and technical support to the farmers, render initial proposal for research purpose and follow up their effective application thereof;
3) Provide material and technical support with the view to preventing and controlling crops' and animal's diseases as well as anti harvest pests and weeds;
4) Introduce and adapt new technological findings obtained by research, produce prototypes and disseminate same to causing to be produced;
5) Provide the appropriate information and advisory services to private investers wishing to invest their capital in the agricultural sector;

6) በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ መስክ ለአርሶ-አደሩና በግብርናው ዘርፍ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ስለ ልማቱ አጠባበቅ፣ አያያዝና አጠቃቀም የትምህርት፣ የሥልጠናና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ የልማቱን፣ የጥበቃውንና አጠቃቀሙን ሁኔታ በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

7) ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ግብአትነት የሚያገለግሉ የግብርና ውጤቶችን በበቂ መጠንና ጥራት እዲመረቱ ያደርጋል፤

8) የኢንዱስትሪ እና ኤክስፖርት ሰብሎች እንዲስፋፉ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፣ ያስተባብራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

9) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአርሶ-አደሩ የብድር አገልግሎት የሚቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

10) የውሃ እቀባ፣ በአነስተኛ አርሶ አደርና በቤተሰብ ደረጃ የሚሠሩ የባህላዊና ዘመናዊ ወንዝ ጠለፋ ሥራዎችን ያከናውናል፣ ለውሃ መሳቢያ ሞተሮች ለአርሶ አደሩ የሚቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

11) የግብርና ግብዓቶች ጥራታቸው ተጠብቆ በወቅቱ ለተጠቃሚዎች መቅረባቸውንና መሰራጨታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

12) የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲስፋፉ እና እንዲጠናከሩ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፤

6) Render educational, training and counseling services to the farmers and private investors engaged in the agricultural sector as regards the protection, keeping and use of the development, closely follow up and supervise over the development, protection and utilization of same thereof;

7) Cause agricultural products, used for agro-processing industry input, be produced in sufficient amount and quality;

8) work in integration with pertinent bodies for the promotion of industry and export crops, coordinates and supports same;

9) Ficilatate, in collaboration with pertinent bodies, on conditions how farmers get credit service;

10) Carryout water conservation, river diversion works those could be done by small farmer and family levels, facilitate how water pumping motors could be supplied;

11) Follow up and control over the supply and dissemination of agricultural inputs in time and quality;

12) Make follow up and support for the promotion of cooperatives;

13) በክልሉ ውስጥ የግብርና ሜካናይዜሽን እንዲስፋፋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፣ ያስተባብራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

14) የግብርና ልማቱን ለማፋጠን የገጠር ቴክኖሎጂዎችን ለማሻሻል የሚረዱ ማሰልጠኛ ተቋማትንና ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ይመራል፤

15) በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሰብል፣ የእንስሳትና የገጠር ቴክኖሎጂ ብዜት ማዕከላትን ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣ አዳዲሶች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤

16) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የደን ልማት ተግባራትን ያከናውናል፤

17) የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራና ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በገበያ የሚቀርብ ማናቸውንም የሰብል ምርት፣ የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

18) በግብርና ልማቱ ላይ ተፅዕኖ የሚኖራቸውን ወቅታዊ ሁኔታዎች ይከታተላል፤

13) Work in integration with pertinent bodies for the promotion of agricultural mechanization in the region, coordinate and make support;

14) Establish and lead training institutions and centers those help to improve rural technologies so as to foster the agricultural development;

15) Promote and administer crop, animal and rural technology duplication centers found in the region, cause newones to be established;

16) Conduct forest development activities in the region in collaboration with pertinent bodies;

17) Make technical support so that agricultural development to be led by market and modern production to be strengthened, cause marketingties to be created, devise a system_in collaboration with pertinent bodies, crop, animal and fish product products and bi-products supplied to the market meet their standards, follow up the applicability thereof;

18) Follow up current conditions having impact on the agricultural development;

19) የግብርና ምርት ደህንነቱ የተጠበቀ፣በንጥረ-ነገር ይዘቱ የበለፀገ የተሰባጠረና ጤናማነቱ የተጠበቀ የአመራረት ሥርዓት መኖሩን ያረጋግጣል፤

20) የእፅዋትና እንስሳት ጤና አገልግሎትን ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 15. የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1) በክልሉ ውስጥ የኢንዱስትሪ ተቋማት እንዲያብቡና እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ይደግፋል፣ የጥናት፣ የሥልጠና፣ የቴክኒክና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

2) የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን በመደገፍ ረገድ ቁልፍ ሚና ካላቸው የክልሉና የፌደራሉ አስፈጻሚ አካላትም ሆነ የከፍተኛ ትምህርትና ምርምር ተቋማት ጋር የጋራ ዕቅዶችን አውጥቶ ይሠራል፤

3) አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ለሚሰማሩ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የኢንዱስትሪ መንደሮችን፣ የክላስተር ማዕከላትንና የኢንዱስትሪ ልማት ፓርኮችን ያደራጃል፣ ለነዚሁ የሚያስፈልገው መሬት ከሦስተኛ ወገኖች ይዞታ ነፃ እንዲሆን

19) Ensure the presence of agricultural product safety, nutrient en-riched, diversified and healthy production system;

20) Devise systems helping to improve plant and animal health service quality and accessibility, make follow up and support thereof.

## 15. Bureau of Industry and Investment

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Industry and Investment shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Support and encourage industry institutions to be flourished and expanded in the region, render study, training, technical and advisory services;

2) Work for by issuing communal plans with the regional and federal executive bodies as well as with higher education and research institutions that have a great contribtion, with regard to supporting the manufacturing sector;

3) In collaboration with pertinent government bodies, organize industry villages, cluster centers and industry Development parks which can be used for manufacturing small, medium and higher industry services for those engaging in the manufacturing sector in the region;

ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፣የቦታ ካርታና ፕላን በማሠራትም ሆነ እስከየ መዳረሻቸው የሚዘልቅ መሠረተ-ልማት እንዲሟላላቸው በማድረግ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ያስተላልፋል፤

4) በክልሉ ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ሁለንተናዊ አቅም ለማሳደግ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣል፣ የድጋፍ ማእቀፎችን ያዘጋጃል፤

5) የአምራች ኢንዱስትሪያሊስቶች አቅም የሚገነባባቸውን ተቋማት ያደራጃል፣ ይደግፋል፣ የእዉቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከላት ሆነው እንዲያገለግሉ ያደርጋል፤

6) ኢንዱስትሪያሊስቶችን ለመፍጠር ወይም በሥራ ላይ የሚገኙትን ለማጠናከር የሚረዳ ክልል አቀፍ የኢንተርፕሬነርሽፕ ፕሮግራም ቀርጾ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

7) ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መስፋፋት ዘላቂ ፋይዳ ያለው የአዋጭነት ጥናትና የፕሮጀክት ትግበራ፣ ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ቀርፆ ገቢራዊ ያደርጋል፤

8) በገጠርም ሆነ በከተማ ከአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በኩል የሚቀርቡለትን ፕሮጀክቶች ይቀበላል፣ ወደየ ክላስተር ማእከላት፣ የኢንዱስትሪ መንደሮች ወይም ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሊገቡ የሚችሉትን በአይነት ይለያል እንዲሁም ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ የየፕሮጀክቶቹን ፕላንት ሌይአውት ይገመግማል፣ የሚያስፈልጋቸውን የመሬት መጠን ይወስናል፤

Work with concerned bodies to free the land from third parties for this service; transfer to industry parks development corporation by causing map and plan of the plot to be prepared as well as infrastructures extending to their destinations to be fulfilled;

4) Give industry extension service support in order to enhance the overall capacity of manufacturing industries in the region; prepare supporting frameworks;

5) Organize institutions that will enhance the capacity of manufacturing industrialists; support; make them to be served as a means of knowledge and transfer of technology;

6) Implement, by designing a regional-wide enterpreneurship program that can enable to create industrialists or to strengthen the existing ones; and gives trainings thereof;

7) Design feasibility study and project implementation, supervison and support system having sustainable relevance for expansion of manufacturing industries and other investment projects, and cause to be implemented;

8) Receive projects submitted from the sector of manufacturing industriesin rural as well as urban; identify in kind those could be entered to cluster centers, industry zones or industry parks as well as evaluate the layout of each project out of industry park plant and determine their demand of land;

9) የአነስተኛ፣ የመካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የዘርፍ ማኀበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

10) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ሐሳቦችን በየጊዜው እያመነጨ በሚገባ ተጠንተው በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን በመለየት አግባብ ላለው የፌደራል መንግሥት አካል ያስተላልፋል፣ በክልሉ አቅም ሊፈጸሙ የሚችሉት ደግሞ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

11) በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ፣ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚሸጋገሩ ባለሀብቶች በተሸጋገሩበት ዘርፍ እድገታቸው እንዲፋጠን ለማድረግ የማምረቻ ቦታና የመሠረተ-ልማት አገልግሎት እንዲሟላላቸው ይሠራል፣ በፕሮጀክት ዝግጅትም ሆነ በአዋጭነት ጥናት ረገድ ይደግፋል፤

12) በክልሉ ውስጥ ቀላል፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ተስማሚ ቴክኖሎጅዎችና አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ የዘርፉ የመወዳደር አቅም እንዲጎለብት ይሠራል፤

13) በክልሉ ውስጥ የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ለማስፋፋት በየአካባቢው ያለውን የመልማት አቅም መሠረት ያደረጉ የኢንዱስትሪ ዓይነቶችን ይለያል፣ የኢንዱስትሪ መንደሮችን ያደራጃል፣ ተፈላጊው መሠረተ-ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤

9) Give the necessary support for the small, medium and higher manufacturing industries sector associations get organized;

10) Transfer investment project ideas, by creating same from time to time and identifying those could be applicable after being studied well, to a pertinent federal body; and cause to be implemented those could be applied by capacity of the region;

11) Work for investors transferred from small to medium, from medium to higher levelsto have production place and infrastructure service to be fullfiled in order to speed up their growth with their transitional sector in the manufacturing industry sector; support in the project preparation as well as feasibility study;

12) Work for the sector's competitive capacity to be developed so that small, medium and higher industries are promoted in the region by designing comfortable technologies and new procedural systems;

13) Identify types of industries on the basis of local development capacity to promote rural industrialization in the region; organize industrial zones and cause the demanded infrastructure to be fulfilled;

14) የአምራች ኢንዱስትሪና ሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎችን ለማስፋፋት የሚረዱ ምርጥ ተሞክሮዎችን ያሰባስባል፣ ይቀምራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

15) በክልሉ ውስጥ ምቹና ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት ከባቢ እንዲፈጠር የሚያበረታቱ የፖሊሲ ሐሳቦችን ያመነጫል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

16) በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት እድል መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ በመረጃው መሠረት ክልላዊ የኢንቨስትመንት መሪ እቅድ እና ተያያዥ እቅዶችን ያዘጋጃል፣ ቀዳሚ የኢንቨስትመንት ዘርፎችን ይወስናል፣ መረጃዎችን ለባለሀብቶች ያሰራጫል፣ ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ለነዚሁ ወገኖች ያስተዋውቃል፤

17) በሚመለከተው አካል ተለይቶ በተዘጋጀው የኢንዱስትሪ ቀጠና አምራች ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች እዲስፋፉ ይሠራል፣ የቀጠናዎቹ ወሰንና የአጠቃቀም ለውጥ በመሬት አስተዳደር መሥሪያ ቤቱ እዲመዘገብ ያደርጋል፣

18) ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ 17 በተደነገገው መሠረት ተለይቶ የተዘጋጀውን ወደ የኢንዱስትሪ ቀጠና እንዲገቡ ለተመረጡ አልሚዎች ያቀረቧቸውን ፕሮጀክቶች በመገምገምና የመሬት መጠን በመወሰን ውል ይዞ መሬት ያስተላልፋል፣ እንዳስፈላጊነቱ የመሠረተ-ልማት ማሟላት ተግባራትን ያከናውናል፣ በውላቸው መሠረት በማያለሙት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ መሬቱን ተመላሽ በማድረግ እና ለመሬት ቢሮ በማሳወቅ ለሌላ አልሚ ያስተላልፋል፤

14) Collect best practices those help to promote manufacturing industries and other investment sectors; make and distribute to users;

15) Create policy ideas those encourage conducive and competitive investment environment to be created in the region; implement same upon approval;

16) Collect data of resource accumulation and investment opportunity found in the region; compile; prepare regional master plan and related plans based on the data; determine prior investment sectors; distribute informations to investors; advertize concrete ivestment projects to these parties;

17) Work for the promotion of manufacturing industries and other investment sectorsin industry zones identified by concerned body; cause boundaries of the zone and change of use to be registered by office of the land administration;

18) Transfer land after having contract to the selected developers by evaluating their submitted projects and determining the amount of land in order to enter to the industry zone which is prepared being selected in accordance with the provision under sub-article 17 hereabove, carry out infrastructure fulfilment as deemed as necessary, take legal measure on those failing to develop pursuant to their contract, transfer the land to another developer by returning it and notifying same to the the Bureau of Land;

19) የተሻለ የኢንቨስትመንት ፍሰት ባለባቸው እና በሌሎች በጥናት በሚለዩ የክልሉ አካባቢዎች እንዲሁም በልዩ የኢኮኖሚ ቀጠናዎች ለግል ባለሀብቱ የተከለለ አገልግሎት የሚሰጡ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫዎችን ያቋቁማል፤

20) ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋትና ከማበረታታት ጎን ለጎን የክልሉን መልካም ገጽታ ለመገንባት የሚረዱ ጽሑፎችንና ፊልሞችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ አውደ-ርእዮችን፣ ዐውደ-ጥናቶችንና ሴሚናሮችን እንዳስፈላጊነቱ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ያካሂዳል፣ በተዘጋጁ ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ላይ ይሳተፋል፣ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

21) ስለ ኢንቨስትመንት የወጡ ሀገር አቀፍ ፖሊሲዎችና ሕጎች በክልሉ ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

22) በባለሀብቶች የሚቀርቡለትን የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች መርምሮ አግባብ ባላቸው የኢንቨስትመንት አዋጆችና ደንቦች ላይ የተደነገጉትን ተፈላጊ ሁኔታዎች አሟልተው ሲገኙ በተሰጠው የሥልጣን ክልል መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ትክና ለውጥ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ ከነዚሁ ግልጋሎቶች የሚመነጨውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤



19) Establish an enclosed one center service renderin to the private investors in the regional areas wher there is better investment flow and other area identified through study as well as special economi zones;

20) Prepare literatures and films those help to build th image of the region side by side from promoting an encouraging investment; distribute; conduct, as may b necessary, exhibitions, research findings and seminar in the country as well as foreign countries; participat in similar programs; render trainings;

21) Ensure and control the implementation of nation wide policies and laws issued concerning investmen whether they are applied correctly or not in the region;

22) Render investment license in its power limit afte investigating investment requests submitted b investors when they fulfill the requirenments provide in the relevant investment proclamations an regulations; give replacement and change, cance renew, and collect service fees generated from the services;

23) በክልሉ ውስጥ በኢንቨስትመንት ሥራ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ያበረታታል፣ ይደግፋል፣ ፈጥነው ወደ አፈጻጸም በማይገቡ ፕሮጀክቶች ላይ ደግሞ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ፈቃድ የመሰረዝና መሬት የማስመለስ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

24) የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች የሚያቀርቧቸው የማበረታቻ ጥያቄዎች ሕጉ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች አሟልተው የቀረቡ መሆናቸውን እያረጋገጠ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤

25) በባለሀብቶችና ጉዳዩ በሚመለከታቸው የክልል መስተዳድሩ አካላት መካከል የኢንቨስትመንት ተግባራትን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

26) በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አስመልክቶ ለባለሀብቶች ተገቢውን የምክርና የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፤

27) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በፌደራሉ መንግሥት የኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኩል ፈቃድ አግኝተው በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብቶች ተግባራት በቅርብ ይከታተላል፣ የባለሃብቶች ፎረም እንዲቋቋም ይረዳል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ትክክለኛ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ የማይገኙትን መሬቱን ነጥቆ ውሳኔውን ለክልሉ መሬት ቢሮ እና ለፌደራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ያሳውቃል፤

23) Encourage investmentors engaged in investment in the region; support; make and cause cancelation of license and land return administration measures to be taken, in collaboration with concerning bodies, on projects which do not timely enter into implementation;

24) Give an appropriate decision for incentive requests, submitted by investors who have given investment license, by ensuring whether the requests fulfilled requirements listed in the law or not;

25) Coordinate investment activities between investors and pertinent bodies of the regional government, and control thereof;

26) Render the necessary advisory and information service to investors concerning the ongoing investment activities taken place in the region;

27) In collaboration with concerned bodies, closely follw up the activities of local as well as foreign investors operating in the region getting license by the federal investment commission; cause the establishment of investors' forum, and render support; snach the land from those who do not on actual performance, and report same to the regional land bureau and to the federal investment commission;

3) በክልሉ ውስጥ በንግድ ሥራ የሚሰማሩትን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በንግድ ሕጉ መሠረት ይመዘግባል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

4) የክልሉን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ የነጋዴዎችን የተሟላ መረጃ ይይዛል፤

5) የገበያና የንግድ ሥራ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር፣ በመተንተንና በማሰራጨት ረገድ ተፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

6) የግብይት ልማት ዘርፉን ለማጠናከር በተመረጡ መስኮች ለክልሉ የግብይት ተዋናያን የብድር አገልግሎቶችን ያመቻቻል፤

7) በክልሉ ውስጥ የንግድ አደረጃጀቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ በንግድ አሠራር ረገድ ያላቸው ግንዛቤና ተሳትፎ እንዲዳብር ያደርጋል፤

8) በጠቅላላ የጥራት አሠራርና አስተዳደር እንዲሁም በድርጅቶች መካከል በውል ሊፈጠር ስለሚችል የሥራ ቁርኝት አሠራር ያስተዋውቃል፤

9) የክልሉን ምርቶችና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ የሚረዱ ቋሚ ኤግዚቢሽኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ለሚያዘጋጁ አካላትም ፈቃድና ድጋፍ ይሰጣል፣ ሌሎች ክልሎች በሚያዘጋጇቸው መሰል ኤግዚቢሽኖች ላይ ይሳተፋል፤

10) የዋና ዋና የግብርና ምርቶችና ሌሎች ግብአቶች የገበያ ፍላጎት ትንበያ ጥናት ያካሂዳል፣ ይቆጣጠራል፤

3) Register, pursuant to the commercial laws, issue and renew licensefor domestic investors to be engaged in trade activities throughout the region as well as collect the appropriate service fees;

4) Establish and administer the regional book of trade and thereby maintain the complete profile of the traders therein;

5) Provide the necessary support with regard to the collection, compilation, analysis and distribution of market and business related information and thereby cause the creation of marketing ties;

6) Facilitate credit service for the regional transaction operators to strengthen the market development in selected sectors;

7) Encourage and support the establishment of organizations in the region and make their awareness and participation in respect of business procedures to be developed;

8) Promote general quality function and administration as well as working ties to be created between and among organizations on the basis of contractual agreements;

9) Cause the preparation of permanent exhibitions where by the regionl products and services might be displayed, render license and support to those bodies preparing same and participate in such exhibitions that are organized by other regions;

10) Undertake and monitor market demand forecast studies with regard to those major agricultural products and other inputs;

11) በግብይት ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት ሂደቱ የተቀላጠፈ ይሆን ዘንድ ለዚሁ የሚያስፈልገውን አሠራር ይቀይሳል፣ የግብይት ሥርዓቱን ያዘምናል፣ እንቅስቃሴዎቹን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

12) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከላት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የግብይት አማካሪ ምክር ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

13) የግብርናም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤቶች የጥራት ደረጃቸው ተጠብቆ ለገበያ የሚቀርቡበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይከታተላል፤

14) የግብርና ምርቶች አቅርቦትና በገበያ ረገድ ያላቸው ቀጣይነት አስተማማኝ ይሆን ዘንድ እንዲስፋፋ ያበረታታል፤

15) የኢንዱስትሪ ተቋማት የፋይናንስ፣ የትራንስፖርትና ትራንዚት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

16) በየጊዜው የሚያሻቅበውን የዋጋ ንረት ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤ ሕጋዊ አሠራርን መሠረት አድረጎ ተግባራዊ ያደርጋል፤

17) የንግድ ስርዓቱንና ሸማቹን ጎብረተ-ሰብ የሚጎዱ የተለያዩ ሕገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፣ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ለሚመለከተው አካል ክስ እዲመሠረት ይልካል ፤

11) Devise a system, identifying would be challenges through study, of procedure for the expedition ofsame in relation to transaction; modernize the transaction system; lead the activities on top, and coordinate same;

12) Facilitate, in collaboration with pertinent bodies of the matter, conditions for the creation and strengthening of market centers for agricultural products; cause the establishment of transaction advisory council and thereby render support;

13) Set and follow up a system whereby agricultural as well as industrial outputs may be offered for marketing with their quality standard having been maintained;

14) Encourage the expansion of the sustainability of supply of agricultural products and marketing thereof;

15) Render the necessary support so that the industry institutions get financial, transport and transit facilities;

16) Design methods to preventing the frequent inflation; implement same on basis of legal procedures;

17) Supervise different illegal trade activities that would harm the trade system and the purchaser, take legal and administrational measures; send to concerned body to be charged;

18) የሸማቹን መብት ለማስከበር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችንና ለነዚሁ ሲባል የሚፈጠሩ አደረጃጀቶችን ይደግፋል፣ ያስተባብራል፤

19) በንግድ ውድድርና በሸማቾች መብት አጠባበቅ ረገድ የሚነሱ አለመግባባቶች በድርድር ወይም በእርቅ እንዲፈቱ የሚያስችል የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል፤

20) አይነታቸውና የዋጋ ዝርዝራቸው በፌደራሉ መንግሥት ንግድ ሚኒስቴር የሕዝብ ማስታወቂያ ክፍል የተገለጹት ወይም የሚገለጹት የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች በክልሉ ውስጥ ስለሚሰራጩበት፣ ስለሚሸጡበትና ከቦታ ቦታ ስለሚዘዋወሩበት ሁኔታ ይወስናል፤ እንዳስፈላጊነቱ እቃዎች ባለቁ ጊዜም እንዲተኩ ለነጋዴዎች መመሪያ ሊሰጥ ይችላል።

## 17. የመሬት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መሬት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

1) በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የገጠር መሬትም ሆነ የከተማ ቦታ አይነትና መጠን አጥንቶና መዝግቦ ይይዛል፣ አስተዳደሩንና አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2) በክልሉ ውስጥ የሚገኝን የገጠር መሬት አጠቃቀም ያጠናል፣ ይወስናል፣ የመሬት ተጠቃሚዎች በይዞታቸው ላይ የተለያዩ እንክብካቤዎችን ማድረጋቸውን ይከታተላል፣ መሬታቸውን በአግባቡ ለያዙት የተለያዩ የማትጊያ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ግዴታቸውን ባልተወጡት ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤



18) Support and coordinate the activities and structures that are created for this purpose so as to cause the purchaser's right to be respected;

19) Establish procedural systemenabling to resolve disagreements, which would be raised on trade competition and purchasers rights, through bargain or reconciliation;

20) Determine the way of their distribution, shall be sold and to transfer from place to place in the region of trade materials and services, which are specified or shall be specified of their lists and prices by the Federal State Ministry of Trade public Notice Pannel; and, as deemed as necessary, it may order merchants to replace these materials when they are finished.

## 17. Bureau of Land

Without prejudice to subsequent provisions to be issued, the Regional Bureau of Land shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Study, register and maintain the type and amount of rural as well as urban land available in the region, follow up and supervise its administration and use thereof;

2) Study and determine the land use found in the region; follow up that land users take care of their land holdings in various ways; devise various incentive methods for those who hold their land properly, and take an appropriate measure on those who do not discharge their own duties;

3) እንደ ሁኔታው ባህላዊና ዘመናዊ የቅየሳ ዘዴዎችን በመጠቀም እያንዳንዱን የገጠር መሬት ይዞታና ማሳ ይለካል፣ ይመዘግባል፣ በምዝገባው መሠረት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ ይሰጣል፤

4) በገጠሩ አካባቢ የመሬት ይዞታና የመጠቀም መብት የተሰጣቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የይዞታ መብታቸውን እንደ አግባብነቱ በውርስ፣ በኪራይ፣ በስጦታ ወይም በለውጥ ወይም በብድር ዋስትና የሚያስተላልፉበትን ሥርዓት ያስፈጽማል፣ በመሬት ይዞታ ላይ የሚካሄዱ ለውጦችን በየጊዜው እየመዘገበ መረጃውን ወቅታዊ ያደርጋል፤

5) በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ባለ ይዞታዎች ለሚቀርቡ የስሙ-ንብረት ዝውውር ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፣ በመሬት ይዞታ ላይ የሚካሄዱ ለውጦችን በየጊዜው እየመዘገበ መረጃውን ወቅታዊ ያደርጋል፤

6)የገጠር መሬት ኢንቨስትመንት መሬት ሊዝ አሠራሩንና ተመኑን በየጊዜው እያጠና ለክልሉ መንግሥት በማቅረብ ያስወስናል፣ ለኢንዱስትሪ የሚውሉ ቦታዎችን ይለያል፣ ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ያስተላልፋል፣ በገጠር በእርሻ ኢንቨስትመንት ለሚሳተፉ ያቀረቡትን ፕሮጀክት በመገምገምና የመሬት መጠን በመወሰን ውል ይዞ ለሦስተኛ ወገን መሬት ያስተላልፋል፣ ወደ ሥራ ከገቡ በኋላ ለታለመው ዓላማ ስለ መዋሉ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በዕቅዳቸውና በውላቸው መሠረት ተግባራዊ በማያደርጉት ላይ ከሚመለከተው አካላ ጋር በመተባበር በሕግ መሠረት እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንዲወሰዱ ያደርጋል፤



3) Having regard to circumstances, using traditional and modern surveying instruments, measure and register each rural land-holding and farm and thereby issue certificate of holding with map as per such registration;

4) Cause the execution of the system through which individuals or organizations having land–holding and use right in rural areas, as may appropriate, to be transferred such rights by inheritance, lease, bequeath or exchange or mortgage; update the information by registering changes taken place on land-holding;

5) Render an appropriate response for requests submitted from rural kebele centers reg arding transfer of title; update information by registering changes taken place on land-holding;

6) Cause rural land investment land lease procedure and rate to be determined by studying same from time to time and sumbit to the regional government, identifies in sites, transfer them to the Bureau of Industry and Investment, by reviewing your proposed project and determining the size of the land they the transfer land to third parties with contracts for agricultureal investment in rural areas, monitors the use of them for their intended purpose; in collaboration with the relevant body take and cause to be taken measures against those failing to perfrom in accordance with their plans and contracts pursuant to law;

7) ለገጠር ቀበሌ ማዕከላትና አዳዲስ ለሚፈጠሩ መንደሮች የመሬት አጠቃቀም ዕቅድና ዲዛይን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

8) አግባብ ካላቸው የከተማ አስተዳደሮች ወይም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሌሎች የክልሉ መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ለሕዝብ ጥቅም ታልሞ በሚወሰድ መሬት ምክንያት ከመሬታቸው የሚነሱ የልማት ተነሺ ባለይዞታዎችን ይለያል፣ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ የሀብትና ንብረት ቆጠራ ያካሂዳል፣ የሀብት ግምት በመሥራት ቅድሚያ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፈላቸው ያደርጋል፤

9) በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሱ ባለይዞታዎችን በጉዳት መጠናቸው በደረጃ ይለያል፣ አማራጭ የፕሮጀክት ሐሳብ ያዘጋጃል፣ ከተነሽዎች ጋር ይወያያል፣ ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር የልማት ፋይናንስ፣ የመሥሪያና የመኖሪያ ቦታ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ በዘላቂነት የማቋቋም ሥራ በማከናወን በሒደቱ የሚነሱ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች የሚፈቱበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

10) በዘመናዊ ሁኔታ በሚለሙ ትላልቅ የመስኖ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለሚኖሩ ቀደምት ባለይዞታዎች በሕግ አግባብ የመሬት ሽግሽግ ያካሂዳል፣ የሁለተኛ ደረጃ ደብተርና ካርታ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

7) Prepare land use plan and design for rural kebele centers and newly-emerging settlements, and follow up their implementation;

8) In collaboration with pertinent bodies of city administrations or the issue-concerned regional government bodies, identify land holders uprooted from their lands due to public interests, create awareness, conduct wealth and property counting, casue prior equitable compensation to be paid by doing property valuation;

9) Identify uprooted land holders due to development in their damage level, prepare alternative project idea, discuss with uprooteds, cause they get development finance, working place and living place in collaboration with stakeholders, devise mechanisms how raising appeals and grievances in the process to be solved by permanently rehabilitating them;

10) Having carried out land redistribution in accordance with law, cause the acquisition of second-grade holding certificate along with map for the original inhabitants inside large scale irrigation project areas being developd in modern way;

11) በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ የመሬት ይዞታዎችና ማሳዎች ልዩ ኮድ ይሰጣል፣ የተሰጠውን መለያ ኮድ ሌሎች መሥሪያ ቤቶችና የልማት ተቋማት እንዲገለገሉበት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

12) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በከተማ መዋቅራዊ ፕላንና አስተዳደራዊ ክልል ፕላን ወሰን መካከል የተጠቃለሉ የመሬት ይዞታዎችን አስተዳደርና አጠቃቀም ይወስናል፣ ይመዘግባል፣ ለባለ ይዞታዎችም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ ይሰጣል፤

13) በከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ከተካተቱት ውጭ ለተለያዩ የልማት አገልግሎቶች የሚውሉ መሬቶችን በጥናት ይለያል፣ ወደ መሬት ባንክ ያስገባል፣ በበቂ ሁኔታ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ለሚመለከተዉ አካል በሊዝ ሥርዓት የሚተላለፉበትን አሠራር ይዘረጋል፣ የአፈጻጸሙን ፍትሐዊነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

14) ለመሬት አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ የጅኦ ስፓሻልና ተያያዥ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ መስፈርቱን አሟልተው ለሚቀርቡ አገልግሎት ፈላጊ አካላት ተገቢውን አገልግሎት ይሰጣል፤

15) አነስተኛና የተበታተነ የገጠር መሬት ይዞታን በባለይዞታዎች ሙሉ ተሳትፎና ፍላጎት በሒደት ይዞታን ለማጠጋጋት (consolidation) የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ በክልሉ መንግሥት ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤



11) Render a special code to land holdings and farms found in the region and there by facilitate conditions whereby other offices and developmental institutions might use such identification codes;

12) In collaboration with appropriate bodies, decide land holding administration and use of which are incorporated betweenboundary of urban structural plan and administrational region plan as well as register same and thereby issue land holding certificate and maps;

13) Except those included in the urbans structural plan identify land used for different services through study, enter same to land bank, cause same to be prepared in sufficient condition, devise procedures how they are transferred to the concerned body, follow up and control the implementation fairness therebe;

14) Collect, compile and analyse geo-spacial and related data used for land administration system building, and render an appropriate service for service requires meeting the criteria thereby;

15) Devise a mechanism whereby small and separated rural land holdings to be consolidated through full participation and will of the holders, and apply same when permitted by the regional government;

16) መሬት ነክ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት ወጥነትና ግልጽነት ባለው አሠራር ይፈታል፣ የዘመናዊ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት በመገንባት የአገልግሎትና የመረጃ ተደራሽነትን ያሰፋል፤

17) የመሬት አስተዳደር ሥርዓቱን የሚያዘምኑና ቀጣይነቱን የሚያረጋግጡ ዓለማቀፍ ልምዶችን ይቀምራል፣ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

18) በመሬት አስተዳደር ሥርዓቱ ላይ የሚታዩ ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል የሚያስችሉ የአሠራር ስልቶችን ይነድፋል፣ የመሬት አስተዳደር ሒደቱንም ኦዲት (land transaction audit) ያከናውናል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

19) በገጠር መሬት ላይ የሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ግንባታዎች ዲዛይኑን መርምሮ ያጸድቃል፣ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣ አስፈላጊ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡

## 18. የከተሞችና መሠረተ-ልማት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የከተሞችና መሠረተ-ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የሚደነገግ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ከተሞች በእቅድና በከተማ ፕላን እንዲመሩ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤



16) Solve land related good governance problem in uniform and transparent procedure, promo service and data accessibility by buildin modern data administration system;

17) Formulate worldwide experiences modernizi and ensuring the sustainability of lar administration system, conduct research an apply same;

18) Devise mechanisms enabling to preve corruption seen in the land administratic sysytem, perform land transaction audit of th land administration procees, take correcti measures in collaboration with concerne bodies;

19) Approve by investigating investment buildi designs taken place on rural land, rend building license, and make follow up a control, take necessary corrective measu thereof.

## 18. Bureau of Urbans and Infrastructure

Without prejudice to the existing or subsequ provision of other laws, the Regional Bureau of Urb and Infrastructure shall, pursuant to this proclamati have the following specific powers and duties:

1) Particulars being stipulated with regulat being issued toimplement this proclamati follow up urbans found in the region to be by plan and urban plan, and support hereof;

2) ከተሞች የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ማዕከልነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል ሁለንብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፣ የከተማ አሰፋፈርና የዕድገት አቅጣጫውን ያጠናል፣ ይከታተላል፤

3) በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ከተሞች የከተሞችን ፕላን በጠበቀ መልኩ የመሠረተ-ልማት አውታሮች የሚስፋፉበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ በልማቱም ኅብረተ-ሰቡ ተሳታፊ እንዲሆን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

4) በከተማ መዋቅራዊ ፕላን ክልል ውስጥ የሚካሄድ ማናቸውም የመሬት አጠቃቀም ከከተማው ፕላንና ከወደፊት የከተማው እድገት ጋር የሚጣጣም መሆኑን እየገመገመ የይሁንታ ፍቃድ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

5) ከከተማ መዋቅራዊ ፕላን ክልል ውጭ የሚገኝ ማናቸውንም በሚመለከተው አካል የተዘጋጀ መሬት ይረከባል፣ ለሦስተኛ ወገን ያስተላልፋል፣ ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

6) በከተማ ባለይዞታዎች ለሚቀርቡ የስመ ንብረት ዝውውር ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፣ በመሬት ይዞታ ላይ የሚካሄዱ ለውጦችን ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያስተላልፋል፤ይመዘግባል፤



2) Render overall and intergrated support to enable urbans to potencially discharge their center of politics, social and economical development; study and follow up the urban settlement and direction of development thereby,

3) Devise mechanism whereby outlets of infrastructures to be expanded in urban centers in compliance with master plan of each city in the region, closely follow up and support therof, and devise a system making the society participant of the development;

4) Render acceptance license for any land use taken place in urban structural plan by evaluating the compliance of same with the urban's plan and future development of the city, follow up and control the performance;

5) Receive any land found outside boundary of urban structural plan and prepared by concerned body, transfer it to third body, develop same economically, administer and control it;

6) Render the appropriate response and register for transfer of property requests presented by urban holdings, timely transfer changes taken place on land holding to concerned body;

7) የከተማነት መስፈርት የሚያሟሉ የቀበሌ ማዕከላትን መረጃ ከሚመለከተው አካል ይወስዳል፣ ያጠናል፣ መስፈርቱን የሚያሟሉትን የከተማ እውቅና ይሰጣል፣ በክልሉ ውስጥ የታቀፉትን ከተሞች እድገት በየጊዜው እያጠና ከአንድ ደረጃ ወደሌላ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፣ ወደ ከተማ አስተዳደርነት ማደግ የሚገባቸው ቢኖሩ ይህንኑ አስመልክቶ የተጠየቀው ሽግግር እንዲፈቀድላቸው ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የውሳኔ ሐሳብ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

8) የክልሉ ከተሞች ሁሉን አቀፍ በሆነ ደረጃ የሚጠቀሙባቸውን ልዩ ልዩ ረቂቅ የሕግ ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፣ የእድገት ደረጃቸውን በጠበቀ መንገድ እንዲሻሻሉ ያደርጋል፤

9) የከተሞችን ልማት ለማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያግዙ የተለያዩ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሌሎችም እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ የአሠራር ስልቶችንም ይቀይሳል፤

10) ከተሞች ከአጋር አካላት ጋር በጋራ የሚሠሩባቸውን ስልቶች በመቀየስ ያልተማከለ አስተዳደር ሥርዓት የሚጠናከርበትን ዘዴ ይቀይሳል፣

11) ለከተሞች ዘላቂ ሥልጣን የሚያጎናጽፍ የልማት ፋይናንስና አስተዳደር እንዲኖራቸው ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

12) የክልሉ ከተሞች ውብ፣ ፅዱና አረንጓዴ እንዲሁም ለኑሮ እና ለሥራ ተስማሚና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲገኙ አስፈላጊውን ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፤



7) Take data of kebele centers, which ful criteria of urbaness, from concerned body a study same; render recogniction of city which fulfill the criteria; cause transfer urbans, found in the region, from one level another level by studying their growth fr time to time; when there are urbans th should be promoted to city administrati prepare recommendation and submit same the Regional Government council so that requested promotion to be permited;

8) Prepare different legal framework dra whereby cities of the region use same in embracing level; cause improvement of th level in keeping their growth level;

9) Conduct different studies helping to fo urbans development and ensuring g governance, casue same to be conducted others; devise working mechanisms;

10) Devise a method strengthening decentraliza administration system by devising syst whereby urbans work with partner bodies;

11) Make support and follow up so that url have developmental finance and administra that enables them sustainable authority;

12) Provide necessary support and assistance that urbans of the region become attrac clean, and green as well as competitive comfortable for habitation and work;

13) ከከተሞች ፕላን ጋር የሚጣጣምና የከተሞችን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ የቤት ልማት አማራጮችን ዓይነትና የሚያስፈልገውን የመሬት መጠን በመወሰን ለመሬት አቅራቢው አካል ያሳውቃል፣ የተጠየቀው መሬትም እንዲቀርብና ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ይከታተላል ወይም ያደርጋል፤

14) የግል ሴክተሩንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አቅም በማሳደግ በከተማ ልማት፣በሪል-ስቴት ሥራዎች እና በመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች በንቃት የሚሳተፉበትን ሥልት ይቀይሳል፤

15) በክልሉ መንግሥትና በከተሞች ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶችን በሚመለከት አግባብ ላላቸው አካላት ተፈላጊውን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ያደርጋል፤

16) የከተማው ነዋሪ ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠኑ መኖሪያ ቤቶችን ሠርቶ ይጠቀም ዘንድ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን እንዲመቻቹ ያደርጋል፤

17) የሀገሪቱ የሕንፃ ኮድና ስታንዳርዶች በዲዛይንና ግንባታ ሥራ ደረጃዎች ላይ በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

18) በክልሉ መንግሥት በጀት እና በግሉ ዘርፍ ለሚገነቡ ግንባታዎች የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችንና የመንግሥት የግንባታ ሥራ ውሎች በአግባቡ መዘጋጀታቸውን ቁጥጥር ያደርጋል፤



13) Report to theland supply body by deciding urbans plan basis and urban contextual house development alternatives and the size of land needed, follow up or make the requested land to be supplied and used for the intended objective;

14) Devise a system in which private sectors and public developmental organizations, through building their capacity, participate in urban development, real estate and similar activities;

15) Makethe necessary technical and administrative support to pertinent bodies concerning houses found under the regional government and urbans ownership;

16) Cause the facilitation of conditions enabling the inhabitants of the urbans to build dwelling houses comparable to their descent capacity and benefit therefrom;

17) Ensure the observance of the country's code and standards in design and construction work levels in the region;

18) Supervise thepreparation of designs and government contractual documents necessary for the construction of builidings financed by the regional government and private sector;

19) በክልሉ መንግሥት በጀት የሚከናወኑ የመንግሥት ግንባታዎች በተገባላቸው ውል መሠረት የጥራት ደረጃቸውና የጊዜም ሆነ የዋጋ ገደቦቻቸው ተጠብቀው መሠራታቸውን ይቆጣጠራል፤

20) በክልሉ ውስጥ የሥራ ተቋራጮችን፤ አማካሪዎችንና ሙያተኞችን ይመዘግባል፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፣ የግንባታ-ነክ አለመግባባቶች በሚከሰቱበት ወቅት የግልግል ሥራዎችን ይሠራል፤

21) በክልሉ ውስጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አቅም እንዲያድግ ተፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ የግንባታ ቴክኖሎጅዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ በጥቅም ላይ የሚውሉ የግንባታ ግብዓቶች ጥራታቸውን ጠብቀው እየተመረቱ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የጥራት ችግርም ሲያጋጥም እርምጃ ይወስዳል፤

22) በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት የሚኖራቸውን የኮንስትራክሽን፣ የከተማ ልማትና ቤት-ነክ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጅዎችን ይነድፋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

23) የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በብቃት መወጣት የሚያስችሉ የኮንስትራክሽን፣ የቤት-ነክ እና የከተማ ልማት መመሪያዎችን በማዘጋጀት በሥራ ላይ ያውላል፤

24) የከተሞችን ልማት ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት እንዲደራጁና የቢሮውንና በተዋረድ የሚገኙ ተቋማትን አደረጃጀት በማጥናት ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

19) Supervise the execution of governm constructions undertaken by the regional st budget is in conformity with the qual standards, time as well as cost limits provided in their contract;

20) Register contractors, advisors and profession in the region, render certification professional competency, cancel their licen when it finds necessary, make comprom works at times of construction-related conflic

21) Perform the necessary support so that capacity of construction industry in the reg to be promoted, encourage the promotion construction technologies, follow up control whether construction materials to used are produced in quality, take meas when quality problem is found;

22) Devise construction, urban development house-related policies and strategies to applicable in the region, apply same u approval;

23) Prepare construction, house-related and ur development directives enabling it effectively carry out its duties responsibilities, and effect same;

24) Cause the organization of institutions neces to quicken the urbans development and e upon approval by studying structures of bureau and lower institutions;

25) በክልሉ የሚገኙ ከተሞችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

26) የከተሞች ምግብ ዋስትናና ስትራተጂን መሠረት በማድረግ የዘርፉን ክልላዊ የልማት እቅድ ያዘጋጃል፤

27) የከተሞች ምግብ ዋስትናና የሥራ እድል ፈጠራን የሚያስተባብሩ የዞን /የከተማ አስተዳደር ተቋማትን የድጋፍ ማዕቀፍ በማዘጋጀት የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤

28) የልማታዊ ሴፍቲኔት፣ የኑሮ ማሻሻያና ልማት የድጋፍ ማዕቀፎችን ይቀርጻል፣ ተፈጻሚ ያደርጋል፤

29) በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የሥራ እድል ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ ሥራ የሌላቸውን፣ መሥራት የሚችሉና የማይችሉትን ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን በጥናት በመለየት መረጃ ይይዛል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፤

## 19. የውኃና ኢነርጂ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ውኃና ኢነርጂ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1) የክልሉን የውኃ ሀብት መረጃዎች በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለልማት ሥራዎች ያውላል፣ እንዲውሉ ያደርጋል፤
2) የክልሉን የውኃ ሀብት ክምችትና ስርጭት ያጠናል፣ እንዲጠና ያደርጋል፣ ያስተዋውቃል፣ ያስተዳድራል፤



25) Lead, on top, urbans found in the region, and supervise same.

26) Prepare a regional development plan of the sector based on urban food security and strategy;

27) Build the implementation capacity of zonal/city administration institutions which coordinate urban food security and job creation by developing a support framework;

28) Design and implement supportive frameworks for development of safety net, livelihood improvement and development;

29) Hold, analyze, and organize information on the identification of jobless, able and unable to work vulnerable people enabling to ensure food security and job creation in urban areas;

## 19. Bureau of Water and Energy

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Water and Energy shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Utilize and cause the utilization of the region's water resource for developmental works by collecting, organizing and analyzing information sameof;
2) Study water resource reserves and distribution of the region, cause to be studied, advert sameof;

3) የክልሉን የውኃ ሀብት ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
4) የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የክልሉን የከርሰ-ምድርና ገጸ-ምድር የውኃ ሀብት በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
5) የክልሉን ውኃ ሀብት ለማልማትና በጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤
6) በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የውኃ አካላትና ተቋማት ከብክለትና ከአደጋ ስለሚጠበቁበት ሁኔታ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር ተባብሮ ይሠራል፤
7) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል ውኃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል፣
8) በፌደራሉ መንግሥት ባለቤትነት በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የውኃ ልማት ፕሮጀክቶች ክንውን ድጋፍ ያደርጋል፤
9) በከተማም ሆነ በገጠር አካባቢዎች ንጹሕ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋኑን ለማሳደግ የአዳዲስ ጥናትና ዲዛይን ማሻሻያና ማስፋፊያ ሥራዎች እንዲካሄዱና ግንባታቸው እንዲከናወን ያደርጋል፣ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያካሂዳል፤
10) በከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ይዘረጋል፣ የተለያዩ ግንባታዎች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ ክትትልና ቁጥጥርም ያደርጋል፤

3) Devise mechanisms those help to utilize the region's water resource sustainably and reliably; supervise its applicability;
4) Identify ground and surface water resource of the region in volume and quality through conducting basine research, facilitate conditions whereby same is utilized;
5) Deliver license serviceto develop the region's water resource and to make same utilized, and follow up the implementation thereof.
6) Work in collaboration with pertinent bodies of the issue on the protection of water bodies and institutions found in the region from pollution and damage;
7) In collaboration with pertinent bodies, determine the would be standard of water that would be used for different services;
8) Render support with a status of ownerhip in respect of water development projects carried out in the regional state under the auspices of the federal government;
9) To promote supply of potable water both in urban and rural areas, cause the undertaking of newer study and design improvement, and expansion works as well as their construction, and carry out the appropriate follow up and supervision;
10) Devise a sewerage disposal system, cause building of different constructions, follow up and supervise therefrom;

11) በከተማና በገጠር አካባቢዎች ለንጹሕ መጠጥ ውኃ አቅርቦት የተገነቡ ተቋማት ዘላቂና አስተማማኝ አገልግሎት የመስጠት አቅም እንዲኖራቸው ሙያዊ ድጋፍ ይሠጣል፤

12) በክልሉ ውስጥ ወጥነትና ፍትሐዊነት ያለው የውኃ ታሪፍ፣ ሮያልቲም ሆነ የወጭ አመላለስና አወሳሰን ስርዓት ቀርጾ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ይህንኑ አስመልክቶ በየጊዜው ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሌሎችም እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

13) በክልሉ ውስጥ የተገነቡ የውኃ ተቋማት ዘላቂና ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ የመለስተኛና ከፍተኛ ጥገና ሥራዎችን ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

14) ከውኃ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጅዎች ጥራታቸውን የጠበቁና ስታንዳርዳቸውን ያሟሉ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በመፈተሽ ወደ ስርጭት እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያበረታታል፤

15) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በውኃ ሀብት ላይ የሚደረጉ ጥናቶችና ምርምሮችን ያካሂዳል፣ ያስተባብራል፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችንና የምርምር ውጤቶችን በክልሉ ውስጥ ያስፋፋል፤

11) Render professional support to enable institutions constructed for potable water supply in urban and rural areas so that they would provide sustainable and reliable service;

12) Formulate uniform and equitable water tariff, royalty as well as cost-recovery and determination system in the region and submit to the council of the regional government, and cause its implementation upon approval,conduct periodic studies and cause same to be undertaken by others;

13) Carry out medium and high–level maintenance works or cause same to be carried out so that constructed water facilities in the region may deliver the desired and sustainable service;

14) Ensure technologies having to do with water works meet the required quality and comply with the standards, authorize and encourage entry of latestsinto distribution after testing;

15) In collaboration with the pertinen bodies of the issue, conduct and coordinate studies and researches undertaken on water resource, promote newer technologiesand research findings in the region;

16) የክልሉን የውኃ ሀብትና የውኃ አቅርቦት ተቋማት በአግባቡ ለመጠበቅና ለመጠቀም የኅብረተ-ሰቡን የባለቤትነት ስሜት የሚያዳብሩና በዘርፉ የተሰማሩትን አካላት ክህሎት የሚያሳድጉ ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፤

17) በክልሉና በፌደራሉ መንግሥት አካላት የወጡ የውኃ ሀብት አስተዳደር ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

18) ክልል አቀፍ የሆኑ የውኃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ፣ ሕግና ደንብ ረቂቆችን፣ መመሪያዎችን፣ ስትራቴጂያዊ እቅዶችን፣ ስታንዳርዶችንና የሥራ ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

19) በክልሉ ውስጥ የኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሌሎች እንዲጠኑ ያደርጋል፤

20) የግል ባለሃብቶች በኢነርጂ ልማት ሥራዎች በስፋት እንዲሳተፉ ያነሳሳል፣ የተለያዩ የፕሮሞሽን ሥራዎችን በማከናወን ያበረታታል፤

21) የታዳሽ ኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ለማድረግ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ ያሉ የፀሐይ፣ የነፋስ፣ የጅኦ ተርማል፣ የዉኃና የባዮ ጋዝ ልማቶችን ያከናዉናል፤



16) Prepare and render trainings aimed a enhancing the community's sense o ownership and raising skills of bodie engaged in the sector with the view t properly handling and utilizing th region's water resource and water suppl facilities;

17) Cause the implementation of wate resource management laws, regulation and directives issued by both the regiona and federal government bodies in th region;

18) Prepare and distribute regional-wid water resource management policy, la and regulation drafts, directives, strategi plans, standards and working manuals a well as follow up and supervise thei implementation thereof;

19) Conduct studies for the promotion o energy development in the region; an cause to be studied by others;

20) Initiate private investors to participat widely in energy development activitie and encourage by performing differen promotion activities;

21) Implement solar, wind, geo-thermal, wate and bio-gas developments from small t higher-levels to cause the promotion o renewable energy development;

22) በክልሉ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማምረት በሚያስፈልገው ሜጋ ዋት መጠን ላይ አግባብ ካላቸው የፌደራሉ መንግሥት አካላት ጋር ይመካከራል፣ እንዳስፈላጊነቱም የሥልጣን ውክልና ሲሰጠው የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨትና የማሰራጨት ሥራ ፈቃዶችን ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

23) በገጠር ኢነርጂ አቅርቦት ረገድ የተለያዩ የኢነርጂ አማራጭ ቴክኖሎጅዎች በሠርቶ-ማሣያ ሙከራ ተደግፈው እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ የኢነርጂ ተጠቃሚዎችና የቴክኖሎጂ አምራቾች ተደራጅተው የብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

24) በክልሉ ውስጥ የማገዶ ተክል በስፋት እንዲለማና አቅርቦቱ የኅብረተሰቡን ፍጆታ የበለጠ እንዲሆን አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

25) የአካባቢ ጥበቃን ከግምት ውስጥ ያስገቡና በዋጋቸው ተመጣጣኝ የሆኑ የኢነርጂ ምንጮችንና ቴክኖሎጂዎችን ልማት፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀምና ቁጠባ ያጣራል፣ እንደ ሁኔታው በግል ባለሀብቶች፣ በመንግሥትና በሌሎች ዘርፎች በኩል ለኅብረተ-ሰቡ ያስተዋውቃል፤

26) ኢነርጂን የሚመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ እንዳስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል።



22) Negotiate with appropriate federal government bodies on the necessary mega watt amount to produce electric power in the region, as deemed as necessary, it shall render work licenses to produce and distribute electric power and supervise therein where delegation power is rendered to it;

23) Cause development of different energy alternative technologies to be widened_ supported with the demonstration with regard to supply of rural energy, facilitate on energy users and technology producers having been organized getcredit service;

24) Work in collaboration with pertinent bodies so that firewood to be produced and for wide production of firewood in the region and the supply is more than the demand;

25) Investigate energy sources and technologies development, distribution, utilization and saving whichof considerable with environmental protection and considerable price, promote to the society through private investors, government and other sectors as deemed as necessary;

26) Collect, compile and analyse information concerning to energy, and as deemed as necessary, it shall distribute same to beneficiaries.

## 20. የመስኖና የቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1) በክልሉ መንግሥት አማካኝነት የተገነቡ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የመስኖ ግድቦችን፣ ቦዮችንና ሌሎች የመስኖ አውታሮችን ተረክቦ ያስተዳድራል፣ ይንከባከባል፣ ይጠግናል፣ ስለ አጠቃቀማቸውም ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

2) በፌደራሉ መንግሥት ባለቤትነት በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ክንውን ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣ ተቋማትን ተረክቦ ያስተዳድራል፣ ውክልና ሲሰጠው የጥናትና ዲዛይን እንዲሁም የግንባታ ክትትል ሥራ ይሠራል፣ ያሠራል፤

3) የክልሉን የውኃ ሀብት ለመስኖ አገልግሎት ለማዋል የጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል ወይም በሌሎች ያሠራል፣ ግንባታቸው ጥራቱን ጠብቆ እንዲጠናቀቅ በማድረግ ለተጠቃሚዎች ያስረክባል፤

4) በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት በውኃና ኢነርጂ ቢሮ ጥናት የተለዩ የክልሉን የከርሰ-ምድር እና የገፀ-ምድር የውኃ ሀብት ለመስኖ ልማት የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤



## 20. Bureau of Irrigation and Lowland Areas Development

Without prejudice to the existing or subsequen provisions of other laws, the Regional Bureau o Irrigation and Lowland Areas Development shal pursuant to this proclamation, have the followin specific powers and duties:

1) Administer, care and maintain irrigation dams chanals and other irrigation outlets rangin from small to higher levels and constructed b the regional state by receving them, desig particular procedural system about thei utilization;

2) Support and followup for irrigatio development projects in the region undertake by ownership of the federal governmen administer institutions by receiving then carryout design as well as constructio followup works and cause same whe deligation is given to it;

3) Carryout study, design and construction worl to utilize the regional water rsource f irrigation service or cause same to be done b others, transfer same to beneficiaries by makir their construction completed keeping quality;

4) Facilitate conditions whereby the region ground and surface water resources identifi by water and energy burea's study on integrat basine development could be utilized irrigation;

5) የመስኖ ልማት ሽፋን እንዲያድግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

6) በመስኖ ልማት ሥራዎች ለሚሳተፉ አጋር አካላት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ የሚገነቡ የመስኖ አውታሮች ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

7) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በክልሉ ውስጥ በተለይም ቆላማና ከፊል ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች የውሀ እቀባና የአነስተኛ፣ የመካከለኛ እና ከፍተኛ መስኖ ልማት ሥራዎችን ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ የመስኖ አውታሮችን በተመለከተ የግንባታና የጥገና ሥራዎችን ያካሂዳል፣ የባህላዊ ወንዝ ጠለፋ ሥራዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

8) በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የመስኖ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ያደራጃል፣ ይመዘግባል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

9) በክልሉ ውስጥ የተገነቡ የመስኖ ተቋማት ዘላቂና ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ የመለስተኛና ከፍተኛ ጥገና ሥራዎችን ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

10) ከመስኖ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጅዎች ጥራታቸውን የጠበቁና ስታንዳርዳቸውን ያሟሉ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በመፈተሽ ወደ ስርጭት እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያበረታታል፤



5) Devise procedural system on the growth of irrigation development coverage, and followup the application therefrom;

6) Render professional support for partner bodies participating in irrigation development works, make the necessary oversight on the construction of irrigation outlets to be comparable with their standards;

7) In consultation with pertinent bodies, implement water reservation and small, medium and higher-level irrigation development works in the region-especially in lowland and semi-lowland areas, cause same to be implemented, conduct construction and maintenance works concerning irrigation development outlets, encourage and support on the promotion of traditional river diversion works;

8) Organize irrigation user associations found in the region, followup and support thereof;

9) Carry out medium and high–level maintenance works or cause same to be carried out so that constructed irrigation facilities in the region may deliver the desired and sustainable service;

10) Ensure technologies having to do with irrigation works meet the required quality and comply with the standards, authorize and encourage entry of latests into distribution after testing;

11) በከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ላይ ለአጠቃቀም እና አስተዳደር በሚያመች ሁኔታ እንዳስፈላጊነቱ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ይከፍታል፣ የተቀናጀ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

12) በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢው ኅብረተ-ሰብ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

13) በቆላማ አካባቢዎች ያለውን የመስኖ ልማት አቅም ለመለየት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የአካባቢውን የግብርና መሬት ለማልማት የሚያስችል የመስኖ ልማት ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

14) ከግብርና እና ውኃና ኢነርጂ ቢሮዎች ጋር በመተባበር የቆላማ አካባቢዎች ውኃን ማዕከል ያደረጉ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች እና የመስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

15) የመስኖ ልማት መረጃና ኢንፎርሜሽን ሥርዓትን ይዘረጋል፤

16) በክልሉ ውስጥ በጎርፍ አደጋ የሚጠቁ አካባቢዎች ቅድመ-ጥናት ያካሂዳል፣ የመከላከያ ግንባታዎችን ዲዛይን ይሠራል፣ ያስገነባል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሥራዎችን ይሠራል።

11) As demmed as necessary, openproject office higher irrigation projects in a way of enabli to use and administer, prepare integra development plan, work in collaboration w concerned bodies for their implementation;

12) Facilitate conditions in which the local soci to be participatory and beneficiary in irrigati development projects;

13) Conduct research to identify the potential irrigation development in lowland are formulate irrigation development progra enabling to develop the local agricultural la followup its applicability therefrom;

14) In collaboration with agriculture and water energy bureaus, cause the promotion of wa centering basine development works irrigation developments in lowlands;

15) Devise data and information system irrigation development;

16) Conduct prior-research on flood vulner areas in the region, make and cause desig prevention constructions, carryout pr warning works being with concerned body.

## 21. የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት ልማት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች እና ስትራቴጂዎች ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2) በክልሉ ውስጥ የማዕድን ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ጥናቶችን ያካሄዳል፣ በሌሎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ በነዚሁ ጥናቶች አማካኝነት የክልሉን ዕምቅ የማዕድን ሀብቶች በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት ይለያል፤
3) በክልሉ ውስጥ የሥነ-ምድር ጥናት፣ ካርታ ሥራዎች እና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል እንዲሁም አግባብ ካላቸው የክልል እና የፌደራሉ መንግሥት አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤
4) የሥነ ምድር ጥናት እና የማዕድን ልማት ሥራዎችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፣ ለኢንቨስትመንት እና ለልማት ተደራሽ ያደርጋል፤
5) የማዕድን ልማትን ለማፋጠን የሚያግዙ የቤተ-ሙከራ እና የማዕድን ጥራት ማረጋገጫ ማዕከላትን ያደራጃል፣ በዘርፉ ለሚሰማሩ አካላት እንደ አስፈላጊነቱ እንዲደራጁ ድጋፍ ያደርጋል፤



## 21. Bureau of Mineral Resoucre Development

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Mineral Resource Develoment shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Apply the country's mineral resource development policies, laws and strategies in the context of the region;
2) Conduct studies to promote mineral resource development in Ethiopia and cause same to be conducted by others, identify the regional potential mineral resources in kind, amount and quality based on the above studies;
3) Conduct geological study, map works and research works in the region as well as work with pertinent bodies of the region and federal state;
4) Collect, analyse and compile data concerning geological study and mineral development works, distribute same to users, access same for investment and development;
5) Organize laboratory and mineral quality assurance centers helping to foster mineral development, support bodies to be engaged in the sector, as deemed as necessary, to be organized;

6) በቀጥታ ወይም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በባህላዊ፣ በአነስተኛ፣ በልዩ አነስተኛና በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄድን የማዕድን ሀብት ፍለጋ፣ ምርመራ፣ ግኝት፣ ምርትና ይዞ የመቆየት ፈቃዶችን ይሰጣል፣ ያግዳል፣ ያድሣል፣ ያስተላልፋል፣ ይሠርዛል፤

7) ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸዉ ጉልህ የሆኑና ከውጪ የሚገቡ ማዕድንና የማዕድን ዉጤቶች የሆኑ የሲምንቶና ድንጋይ ከሰል፣ ሴራሚክ፣ ማርብልና ግራናይት፣ የብረት ማዕድን፣ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ የማዳበሪያ እና የፔትሮሊየም ልማት ዉጤቶች በክልላችን ዉስጥ እንዲመረቱ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል፤ ከፍለጋ እስከ ምርት ያለዉን የምርት ሰንሰለት ዉጤታማ እንዲሆን ሙሉ ድጋፍ ያደርጋል፣ በሂደቱም የውጪ ምንዛሬ ግኝት እንዲያድግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

8) የማዕድን ምርቶች የጥራት ደረጃቸዉን የጠበቁ፣ በአገር ደረጃም ሆነ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና የልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

9) ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ምርትና ግብይት ሕጋዊ መስመር እንዲይዝ አስፈላጊ ሥርዓት ይዘረጋል፤



6) In collaboration with direct or concerning bodies of the issue, render licenses forsearching, examination, finding, product and holding of mineral resource in traditional, small, special small and higher level; hold, renew, transfer and canceal same;

7) Make conducive conditions in which strategically important and imported mineral and mineral products like cement and charchol, ceramic, marble and granite, iron mineral, different construction inputs, fertilizer and petroleum development products to be produced in the region; render licesense and cancel same in consultation with concerned body; make full support to make the chain from searching to production to be effective; make conducive conditions whereby getteting hard currency in the process to be risen;

8) Devise a system for implementation of capacity building, research and development works so that mineral products to meet their quality standards and to be competitive at national as well as international levels, followup its implementation;

9) In collaboration with concerned bodies, design necessary system whereby precious and jewellery minerals produced by traditional and small level products and marketing to follow legal line;

10) በክልሉ ውስጥ የማዕድናትን አመራረት፣ ግብይትና አስተዳደርን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ዜጎች እኩል ተሳታፊ እና ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፤

11) የግል ባለሀብቶች በማዕድን ሀብት ልማት ሥራዎች የማዕድን ዘርፉ ለክልሉ የላቀ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውጤታማ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት አደረጃጀቱን በማሻሻልና አቅሙን በመገንባት ረገድ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፤

12) ባህላዊና አነስተኛ የማዕድን ማምረት ሥራዎችን ይደግፋል፣ በክልሉ ውስጥ ዜጎች ተደራጅተው በዚሁ ተግባር ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ያበረታታል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

13) አግባብ ባልሆነ እና በሕገ-ወጥ መንገድ የሚከናወን ማናቸውም የማዕድናት ምርትና ዝውውር እንዲገታ አስፈላጊውን የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይቆጣጠራል፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ተይዘው የተገኙ ማዕድናት በአግባቡ ተጠብቀው ሕጋዊ ውሣኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

14) የማዕድን ሥራዎች በሚከናወንበት አካባቢ የአካባቢውን ኅብረተሰብ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ የሕግ ማዕቀፍ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣ በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፍርቶችን መሟላታቸውን ይከታተላል፤

10) Followup and control minerals production, marketing and administration in the region,as well as work in stress that citizens be equal participatory and fair beneficiary;

11) Make the necessary effort through improving its organization and building its capacity so that the mining sector of private investors in mining resource works shall havegreater social and economical development contribution to the region;

12) Support traditional and small-scale mining activities, encourage the creation of employment opportunities for citizens who shall engage in same being organized in the region; render license, and supervise same;

13) Establish and supervise the necessary regulatory framework to curveimproper and illegal production and movement of minerals; ensure that illegally seized minerals are properly protected and made legal decisions;

14) Create conducive environment for benefit of the local community where mining activities are carriedout, creates legal framework, ensure the proper implementation upon approval by the concerned body, and monitor the compliance of standards issued by environmental protection;

15) ከማዕድን ሥራዎች የሚገኝ የሮያልቲ፣ የመሬት ኪራይና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች ክፍያዎችን ይሰበስባል፤

16) የማዕድን ልማት ሥራዎችን ለማፋጠን የሚዉሉ የቤተ-ሙከራና የማዕድን ጥራት ማረጋገጫ ማዕከላትን ያደራጃል፤

17) አግባብ ባላቸው የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ሕጎች ከተፈቀደው ወሰን ሳያልፍ በማዕድን ሀብት ልማቱ የመንግሥትን አክሲዮን ድርሻ ተግባራዊነት ይደግፋል፡ ይቆጣጠራል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

18) በማዕድን ሀብት ልማቱ ዘርፍ መዋዕለ-ንዋያቸውን ማፍሰስ ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች ተገቢውን መረጃና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣ በስፋት እንዲሳተፉ ያነሳሳል፣ የተለያዩ የፕሮሞሽን ሥራዎችን በማከናወን ያበረታታል፤

19) በማዕድን ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ረገድ ለማዕድን ሥራ ባለፈቃዶች፣ ለማዕድን ግብይት ተዋናዮች እና የተፈጥሮ ሀብቱ ባለቤት ለሆነዉ ኅብረተሰብ የሥልጠና፣ ድጋፍና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

## 22. የመንገድ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንገድ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-



15) Collect payments from royalties, land leases an other related services from mining activites;

16) Establish laboratory and mineral qualit assurance centers to accelerate mining development;

17) Support, enforce, and supervise th implementation of government shareholdin in the mining sector without exceeding th limits permitted by the relevant minin development promotionlaws;

18) Provide the relevant information and advic to private investors who want to invest in th mining sector, initiate them to participa widely, and encourage by implementin various promotion activities;

19) Provide training, support and adviso services to mining licensees, minin marketing operators and natural resour owners in the field of mineral developmer protection and utilization, closely follow and monitor same.

## 22. Bureau of Road

Without prejudice to the existing or subsequent law the Regional Bureau of Road shall, pursuant to th proclamation, have the following specific powers a duties:

1) በክልሉ የሚገኙ መንገዶችን ያስተዳድራል እንዲሁም በክልሉ ውስጥ ያሉ መንገዶችን የማልማትና የመጠገን ሥራ ያከናውናል፤
2) ከክልል መንገዶች ጋር በተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የክልሉን መንግሥት ያማክራል፣ ያስተባብራል፣ አፈጻጸሙን ይከታታላል፣ እገዛም ያደርጋል፤
3) የመንገድ ልማት እና ጥገናን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥት ሚኒስቴር፣ የመንገድ አገልግሎት እና ሌሎች ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር በጋራ ይሠራል፤
4) የተጠናከረ የብሔራዊ መንገድ ሀብት አስተዳደር መረጃ እንዲኖር የክልሉን የመንገድ አውታርና የመንገድ ሁኔታ መረጃ ለፌደራል መንገድ አስተዳደር ሪፖረት ያደርጋል፤
5) የተቀናጀ ብሔራዊ የመንገድ አዉታር ዕቅድ በማዘጋጀት ለፌዴራል መንግሥት ተገቢውን ግብዓት ያቀርባል፤
6) በክልሉ ውስጥ መንገዶችን ለማስፋፋት፣ ለመንከባከብና ደረጃ ለማሻሻል የመንገድ ልማት ዕቅዶችን እና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፤
7) ለመንገድ ሥራዎች የሚያስፈልጉ የዲዛይን ዝግጅት፣ የአዋጭነት ጥናት፣ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማና ሌሎች ተዛማጅ ጥናቶች ያዘጋጃል፣እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤
8) የመንገድ ሥራዎችን እና የማማከር አገልግሎቶችን ለማቅረብ ከግለሰቦች ወይም ከድርጅቶች ጋር ኮንትራቶችን ወይም ስምምነቶችን ያደርጋል፤



1) Manage roads found in the region as well ascarryout development and repair works in the region;
2) Advise the regional government on policy matters related to regional roads; coordinate, followsup its implementation and assist therefrom;
3) Work in collaboration with relevant federal ministry, road service and other agencies concerning road development and maintenance issues;
4) Report the regional road outlet and road condition data to the federal road administration for the presence of consolidated national road resource management information;
5) Develop an integrated national road outlet plan and provide the appropriate input to the federal government;
6) Develop road development plans and programs for the expansion, care and upgrading of roads in the region;
7) Prepare and cause the preparation of the necessary design, feasibility study, environmental impact assessment and other related studies necessary for road works;
8) Make contracts or agreements with individuals or organizations to provide road works and consulting services;

9) ለመንገድ ሥራና እና ለአማካሪ አገልግሎቶች ዉሎችን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይወዋላል፣ ሥራዎችን በዉላቸዉ መሠረት መፈጸማቸዉን ይከታተላል፣ ወይም ክትትል እንዲደረግ ያደርጋል፤

10) የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ጥራትን ይቆጣጠራል፣ ተገቢዉን ክትትል ያደርጋል፣ የራስን ኃይል በመጠቀም የመንገድ ግንባታ ጥገና ሥራዎች እንዲከናወኑ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

11) በክልሉ ዉስጥ ያሉ የፌደራል የመንገድ ፕሮጀክቶች የዕቅድ ዝግጅት እና ትግበራ ላይ ከፌዴራል መንግሥት ሀብት አስተዳደር ጋር በጋራ ይሠራል፤

12) በክልሉ ውስጥ በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ዉጤታማ እንዲሆን ትብብር ያደርጋል፣ ወቅታዊ ሪፖርትና መረጃዎችን ለፌደራል መንገዶች አስተዳደር ያቀርባል፤

13) በማኅበረሰብ ተሳትፎና በወረዳ በጀት ለሚገነቡ እና ለሚጠገኑ መንገዶች የቴክኒካልና ሌሎች የማቴሪያል ድጋፍ ያደርጋል፤

14) የመንገድ ጥናትና ምርምር ያካሄዳል ወይም እንዲካሄድ ያደርጋል እንዲሁም ለመንገድ ዘርፍ የሚፈለገውን የሰው ኃይል አቅም ይገነባል፤

15) በሕጉ መሠረት የክልሉ መንገዶችን ወሰን እና የግንባታ ማቴሪያል መገኛ ቦታዎችን ይለያል፤ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሠራል፤

9) Prepare and cause the preparation of contrac for road construction and consulting service make contracts, supervise and cause th supervision of contracts whether they are in lir with the coontract or not;

10) Supervise quality of road construction ar maintenance, make the appropriate folowu and create favorable conditions for roa construction and maintenance to be carried o using own power;

11) Work incollaborattion with federal governme resource management on the planning ar implementation of federal road projects in th region;

12) Collaborate for effective implementation road construction projects funded by the feder government in the region, provide up-to-da reports and information to the federal roa administration;

13) Provide technical and other material suppo for roads to be built and maintained community participation and wereda budget;

14) Conduct or cause conduction of road resear as well as build the required manpower for t road sector;

15) Identify boundaries and locations construction materials in accordance with t law, and work in collaboration with relev body;

16) መንገዶችን ከአደጋና ተገቢ ካልሆኑ አገልሎቶች ይከላከላል፣ በመንገድ ላይ የሚገኙ ለትራፊክ እንቅስቃሴ አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮችን ያስወግዳል ወይም እንዲወገዱ ያደርጋል፤

17) በክልልና በፌደራል መንግሥት ለሚገነቡ የመንገድ ሥራዎች አገልግሎት የሚዉል እንደ ካንፕ፣ ቢሮ፣ መጋዘን እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚዉሉ ከክፍያ ነጻ የሆነ ቦታና የግንባታ ማቴሪያል መገኛ ቦታ ያመቻቻል፤

18) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሕጉ መሠረት ለመንገድ ሥራ የሚፈለግን መሬት ተገቢዉን ካሳ እንዲከፈል በማድረግ ያቀርባል፣ በመንገድ ወሰን ክልል ዉስጥ ያለን ማንኛዉንም ሕገ ወጥ ንብረት ነጻ ያደርጋል፤

19) በመንገድ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ እንቅፋቶችን ወይም እንደ ነዳጅ፣ ዘይት-ነክ ፈሳሾችን በመንገዶች ላይ በሚደፉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

20) የመንገድ ሥራዎች በሚከናወኑበት ጊዜ አካባቢን ለመጠበቅ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

21) በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ መንገዶች ላይ የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን ወይም መሳሪያዎችን ንድፍ በማዘጋጀት አስፈላጊ በሆኑ የገጠር መንገዶች ላይ ያኖራል ወይም እንዲተከሉ ያደርጋል፣



16) Protect roads from accidents and inappropriate services, remove or cause the elimination of traffic congestions;

17) Facilitate free space used for camp, office, warehouse and other related services and location of construction materials for road construction held by the region and federal government;

18) Supply the required land for road construction by causing the payment of appropriate compensation in collaboration with concerned bodies, make free of any illegal property in the boundary of the road to be constructed;

19) Take and cause to be taken legal action against individuals and organizations that cause damage of road by flowing liquids such as fuel and oil spills;

20) Take necessary measures to protect environment at times of road construction;

21) Design traffic signs or devices on roads founds in the region and place them on necessary rural roads, and cause same to be placed;

22) በጋራ አገልግሎት እንዲውል በየትኛውም አካል ኃላፊነት የሚገነባውና የሚጠግነው ማናቸውም መንገድ ደረጃውን ጠብቆ ሲያገኘው መንገዱን ተረክቦ ያስተዳድራል፤

23) ለመንገድ ልማት ግብዓት የሚያገለግሉ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ማሽኖችንና ተሽከርካሪዎችን ያስተዳድራል፤

24) በመንገድ ግንባታ፣ ጥገና፣ ማሽኖችና መሳሪያዎች አጠቃቀምና አስተዳዳር ላይ መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

25) ከፌደራል፣ ከክልልና ሌሎች አጋር አካላት የሚገኙ ሀብቶችን በአግባቡ በመጠቀም የክልሉን ሕዝብ የመንገድ ተደራሽነት ጥያቄ በፍትሐዊ መንገድ እንዲዳረስ ያደርጋል።

## 23. የሥራና ሥልጠና ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የሥራና ሥልጠና ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሥራ ስምሪትን በተመለከተ ፖሊሲዎችና ሕጎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

2) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ሥራ ላይ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና ስለሙያው አመዳደብ ጥናቶችን ያካሂዳል፤

3) በክልሉ ውስጥ ሥራ ፈላጊዎችንና ክፍት የሥራ መደቦች እንዲመዘገቡ ያደርጋል፣ ለዚህም የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ሥራና ሠራተኛ እንዲገናኝ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፤



22) Administerby receiving any road constructe and maintained by any party's responsibility f joint servicewhen it finds meeting its standard;

23) Manage machinery and vehicles used for inpu of road development and found in the region;

24) Prepare, coordinate and cause tl implementation of directives on ro construction, maintenance, use ar management of machinery and equipment;

25) Cause the fair accessibility of roads request by the regional people through the prop utilization of resources found from feder region and other partners.

## 23. Bureau of Work and Training

Without prejudice to the existing or subseque provision of other laws, the Regional Bureau of Wo and Training shall, pursuant to this proclamation, ha the following specific powers and duties:

1) Enforce policies and laws regardi employment in the region;

2) In collaboration with relevant bodies, cond research on the manpower and professio classification engaged in formal and inforn work in the region;

3) Make the registration of job seekers a vacancies in the region, issue certificate for tl and take measures to contact employers w employees;

4) የሰው ኃይል ፍላጎትንና አቅርቦትን ለማጣጣም እንዲቻል ጥናት በማድረግ የሥራ ስምሪትና የሥራ ገበያ መረጃዎች ተሰብስበው፣ ተደራጅተውና ተተንትነው ለተለያዩ ተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚደረጉበት ዘመናዊ ሥርዓት ይዘረጋል፤

5) በክልሉ በቅጥር ላይ የተመሠረተ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት አገልግሎቶች እንዲሰጡ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፈቃድ ይሰጣል፣ ሕግን ተከትለውና አክብረው የሥራ ስምሪት አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ከሕግ ውጭ ሲሆኑ የተሰጣቸውን ፈቃድ ይሰርዛል፤

6) ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ከስደት ተመላሾችን ያቋቁማል፤

7) በክልሉ ውስጥ በገጠርም ሆነ በከተማ አካባቢዎች የሚካሄዱ የሥራ ዕድል ፈጠራዎችን ያስተባብራል፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ የሚሰማሩ ዜጎችን ሥልጠና እንዲያገኙና በክልሉ በሚገኙ የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ እና የግል ድርጅቶች የሥራ እድል እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ኢንተርፕራይዝ ፈጥረው እንዲሠሩ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

8) ለከተሞች፣ የሥራ እድል ፈጠራ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ተወዳዳሪነት ላይ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤



4) Set up a modern system to collect, organize and analyze employment and job market information and make it accessible to different users to meet the demand and supply of manpower through study,

5) Give licenses to local and foreign private employment agencies to provide fair, efficient and effective domestic and foreign employment services based on employment in the region, facilitate the provision of employment services in accordance with the law, and revoke their licenses when they are illegal;

6) Take measures to prevent human trafficking and establish returnees from migration;

7) Coordinate job creations taken place in both rural and urban areas of the region, make the provision training to whom engaged in micro and small scale enterprises, and get job in government, non-governmental and privite organizations found in the region, and make the necessary support to work creating enterprise;

8) Identify and cause to address issues that hinder urban, job creation, and development and competitiveness of micro and small scale enterprises;

9) በዘርፉ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በቂ የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች እንዲያገኙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፤

10) የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎችን በማደራጀትና በማስፋፋት የተጠናከረ የድጋፍ አገልግሎቶችን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችሉ የተሻሻሉና አዳዲስ ሥርዓቶችን በመዘርጋት የማዕከላቱን አቅም ይገነባል፤

11) ለሥራ እድል ፈጠራ አገልግሎት የተገነቡ ሼዶችን ያስተዳድራል፣ ለተጠቃሚዎችም ያስተላልፋል፤

12) ከአበዳሪ የፋይናንስ ተቋማትና ከሌሎች በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፣ ለአሠራር የሚረዱ ስልቶችን ይቀይሳል፣ የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤

13) በቴክኒክና ሙያ ረገድ በቂ እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ያለው የሰው ኃይል በመገንባት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወደሥራ እንዲገቡ በብድር አቅራቢ የፋይናንስ ተቋማት በኩል የብድር አገልግሎት እንዲመቻችላቸው ያደርጋል፤

14) ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በየዘርፎቻቸው በማኅበር እንዲደራጁ ይደግፋል፣ የገበያ ትስስሮችን በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያግዛል፤



9) Work in integration with concerned bodies of the issue so that enterprises engaged in the sector have adequate production and sales place;

10) Build the capacity of centers by devising improved and newly systems enabling to give strengthened supportive service through organizing and expanding one-service stations;

11) Administer shadows built for job creation services and transfer to users;

12) Work in integration with lending financial institutions and other bodies engaged in the sector, devise strategies helping for procedure and organizes consultation forums;

13) Cause the facilitation of loan service for micro and small scale interprises by finance institutions to engage the former through building human power having sufficent knowledge, skill and attitude concerning technique and vocation;

14) Support micro and small scale enterprises to be organized in their respective sectors, assist by creating market ties to make them beneficial;

15) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ የሥልጠና፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጅና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ያደርጋል፤

16) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሒሣብ አያያዝና የኦዲት አገልግሎት በራሱም ሆነ በሌሎች አማራጮች እንዲያገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

17) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የእርስ በርስ መደጋገፍና ዓለም-አቀፋዊ ተወዳዳሪነታቸውን የሚያስተዋውቁ ኤግዚቢሽኖችን፣ ባዛሮችንና ፌስቲቫሎችን ያዘጋጃል፤

18) በክልሉ ውስጥ የቴክኒክና ሙያም ሆነ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጅዎች በተገቢው ሁኔታ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣ በስትራቴጅዎቹ አፈጻጸም ዙሪያ የሚከሰቱ ችግሮችን እንዲፈቱ ያደርጋል፣ የስትራቴጅዎቹን አተገባበር ለማፋጠን የተዘጋጁ የድጋፍ ማዕቀፎችን፣ የአቅም ግንባታ መርሃ-ግብሮችንና አነዚህኑ ለማስፈጸም የተዘጋጁ መመሪያዎችን በሥራ ላይ ያውላል፤



15) Make the provision of training, financial, technological and industrial extension support services to micro and small scale enterprises in line with their growth level;

16) Provide the necessary support for micro and small scale enterprises to access account keeping and auditing services by their own and by other options;

17) Organize exhibitions, bazaars and festivals promoting micro and small scale enterprises' mutual support and international competitiveness;

18) Ensure the proper implementation of technical and vocational as well as micro and small scale enterprise development strategies in the region; cause problems related to implementation of the strategies to be solved, implement supportive frameworks, capacity building programs and directives prepared to accelerate implementation of the strategies;

19) የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የቴክኒክና ሙያም ሆነ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጅን ለኅብረተ-ሰቡ በስፋት የማስተዋወቅና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎችን ያከናውናል፤

20) የሞዴል ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችን እንዲሁም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርጥ ተሞክሮዎች ያጠናል፣ ይቀምራል፣ ያስፋፋል፤

21) በክልሉ ውስጥ ወጥ የሆነ የመረጃ ሥርዓት እንዲደራጅ በማድረግ ለዘርፉ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

22) በቴክኒክና ሙያ፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ መሠረት ኢንተርፕራይዞችን ይደግፋል፣ የደረጃ ሽግግር የሚያካሂዱ ኢንተርፕራይዞችን ይለያል፣ ለዚህም የዕውቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

23) በክልሉ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ፖሊ-ቴክኒክም ሆነ የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጆች እንዲሁም የአጫጭር ሥልጠና መስጫና የክህሎት ማጎልበቻ ማዕከላት እና ተቋማት ዕውቅና ይሰጣል፣ ከደረጃ በታች ሆነው ሲገኙ ደግሞ ዕውቅናቸውን ያነሳል፣ ሕግና አሠራር ጥሰው በሚገኙ ጊዜ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

24) በክልሉ ውስጥ አጫጭር ሥልጠናዎችን የሚመለከት ሥርዓተ-ትምህርት እንዲዘጋጅና በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤



19) Perform wide promotion and awarene creation works of technical and vocational well as micro and small scale enterpris development strategies to the public throu various means of communication;

20) Study, formulate and expand best practices model technical and vocational colleges as w as micro and small scale enterprise;

21) Collect, analyze, and organize informati necessary for the development of the sector establishing a uniform information system the region, and disseminate same to users;

22) Support enterprises in accordance with technical and vocational, micro and small sc enterprise development strategy, ident enterprises undergoing transfer of level, a render recognition certificate for this;

23) Recognize public, non-governmer organizations and private poly-technical as w as technical and vocational training colleges, well as short training and skill building cent and institutions involving in the region; can their recognition when they are under-level, a takes administrative measure when they viol law and procedure;

24) Cause the preparation and implementation c curriculum concerning short trainings in region;

25) በዘርፉ የክልሉን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን የሚያስችሉ የምርምርና የቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴዎች እንዲስፋፉ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣ በቴክኖሎጅ ጥናትና ምርምር ረገድ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ሌሎች መሰል አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሠራል፤

26) የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ውጤታማ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ለመስጠት ይቻላቸው ዘንድ ተቀባይነት ያለው የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓት የሚዘረጋበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ተግባራዊነቱን በቅርብ ይከታተላል፤

27) የግል ባለሀብቶች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ኅብረተ-ሰቡ በኢንተርፕራይዞች ልማትና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሚሳተፉበትን ሥልት ይቀይሳል፤

28) የቴክኖሎጂ ምርምር፣ የፍተሻ ቤተ-ሙከራ፣ የኢንዱስትሪ አሠራሮችና ተሞክሮዎች ማስተዋወቂያና የምክር አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በማቋቋም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን የማስተዋወቅ፣ የተለያዩ የፍተሻ/የኬሚካል ትንተና፣ የመካኒካል ሙከራ፣ የብረታ-ብረት፣ የልኬታና እነዚህን የመሳሰሉትን የምክር አገልግሎቶች ይሰጣል፤

25) Coordinate and support the expansion of research and technology development activities in the sector to accelerate the socio-economic development of the region, work in collaboration and integration with higher educational institutions and other similar bodies found in the region regarding on technology and research;

26) Facilitate the establishment of an acceptable internal revenue collection and utilization system enabling public TVET colleges to provide effective TVET, closely followup its implementation;

27) Devise a strategy whereby private investors, micro and small scale enterprises, governmental and non-governmental organizations and the public participate in the development of enterprises and the TVET sector;

28) Render advisory service to micro and small scale enterprises for the promotion of newly technologies, different testing/chemical analysis, mechanical testing, metalic measuring and soforth by establishing technological research, testing laboratory, industrial procedures and practices promotion service rendering centers;

29) የቴክኖሎጂ ሽግግር ለሚያካሂዱ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፤

30) የክልሉ ቴክኒክና ሙያ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ምክር ቤት እንዲቋቋም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 24. የገንዘብ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገንዘብ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1) የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ዘላቂና የተረጋጋ እንዲሆን የሚያስችሉ የፊሲካል ፖሊሲና ስልት ያመነጫል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

2) የክልሉ መንግሥት በየጊዜው ለሚያወጣቸው የታክስና የቀረጥ ሕጎች መሠረት የሚሆኑ የፖሊሲ ማዕቀፎችን ይቀርጻል፣ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንደ አስፈላጊነቱም የማሻሻያ ሐሳብ ያመነጫል፤

3) የክልሉ ፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር የሚመራበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

29) Provide financial and technical suppo[rt to] micro and smallscale enterprises carryin[g] technology transfer, and devise inc[entive] system thereby;

30) Facilitate conditions on the establishme[nt of] the regional technical and vocational, micr[o and] small scale enterprises development co[uncil] and shall serve as the Secretariat of the Co[uncil];

## 24. Bureau of Finance

Without prejudice to the existing or subse[quent] provision of other laws, the Regional Burea[u of] Finance shall, pursuant to this proclamation, ha[ve the] following specific powers and duties:

1) Initiate, implement and monitor fiscal po[licies] and strategies enablingto the sustainabilit[y and] stability of the regional economic growt[h and] development;

2) Formulate policy frameworks which wou[ld serve as] foundation of tax and custom laws to be [issued] periodically in the region, monitor their [proper] implementation, and propose amendme[nts as] deemed as necessary;

3) Stretch a system to administer the fina[nce,] procurement and property management [of the] region, cause its implementation, and m[onitor] the implementation therefrom;

4) በክልሉና በፌደራሉ መንግሥት መካከል የሚደረገዉን የፋይናንስና የፊሲካል ግንኙነት ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ በሁለቱ መካከል የተጣጣመ አሠራር መዘርጋቱን ያረጋግጣል፤

5) የክልሉ ዓመታዊ የበጀት ዝግጅት የሚመራበትን የመካከለኛ ዘመን፣ የማክሮ ኢኮኖሚና ፊሲካል ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ በተግባር ያውላል፤

6) የወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ብሔረ-ሰብ አስተዳደሮች የበጀት ማከፋፈያ ቀመር ያዘጋጃል፣ በቀመሩ መሠረት የበጀት ድርሻቸውን ይመድባል፤

7) በክልሉ የመንግሥት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት ጥያቄዎች መርምሮ የክልሉን መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ የተፈቀደዉንም በጀት ያስተዳድራል፤

8) የክልሉን የተጠቃለለ ፈንድ ይይዛል፣ ያስተዳድራል፣ የክልሉን የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታ የሚያሳይ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ የክልሉን ዓመታዊ የገቢና የወጪ ሒሣብ ሪፖርት በወቅቱ በማዘጋጀት ለኦዲት ተግባር ምቹ ያደርጋል፤

9) ከሀገር ውስጥና ከውጭ የሚገኙ ዕርዳታዎችን፣ ብድሮችንና ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ የሚደረጉ ስምምነቶችን በክልሉ መንግሥት ስም ይፈርማል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ከሌሎች የፌዴራል መንግሥት አካላትና መንግሥታዊ

4) Direct and coordinate the financial and fiscal relations between the Region and the Federal Government, and ensure the establishment of harmonization procedure of the two;

5) Prepare and implement the medium term, macro-economic and fiscal framework whereby the region's annual budget preparation will be administered;

6) Prepare budget distribution formulas for weredas, city administrations and national administrations, and allocate their budget share according to the formula;

7) Prepare the regular budget of the regional state office through reviewing the regular and capital budget prepared and submitted by the regional state bodies, and administer the authorized budget;

8) Hold and administer the consolidated funds of the region, submit general report showing the region's finance performance and holding by periodically preparing same to the regional administration council, make favorable to auditing by preparing the region's annual revenue and expenditure report on time;

9) Sign agreements concerning domestic and foreign aid, loans and projects on behalf of the regional government, and monitorand evaluate their implementation; closely followup resources and asset found from other federal bodies and non-governmental organizations,

ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ ሀብትና ንብረትን በቅርብ ይከታተላል፣ አጠቃላይ ወደ ክልሉ የሚገቡ ሀብቶችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

10) በክልሉ መንግሥት ተለይተው የሚሰጡትን የግዥና የንብረት ማስወገድ አገልግሎቶች ይሰጣል፤

11) በማንኛዉም አግባብ የክልሉ መንግሥት ንብረት የሆነ እና ማንኛውም በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ባለቤት አልባ የሆነ ንብረትን በመንግሥት ንብረትነት ይይዛል፣ ያስተዳድራል፤

12) በክልሉ የዉስጥ ኦዲት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ የዉስጥ ኦዲት ሥርዓቱን በበላይነት ይመራል።

## 25. የገቢዎች ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገቢዎች ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ውስጥ የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያስከብራል፣ ያስፈጽማል፤
2) በሕግ ተለይተው እንዲሰበሰቡ የተመደቡትንና የፌደራሉ መንግሥት በሚሰጠው ውክልና መሠረት በክልሉ መንግሥት እውቅና የፌደራሉንና የጋራ ገቢዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤



lead, administer and monitortotal resources entering into the region;

10) Provide procurement and property disposal services identified and given by the regional government;

11) Hold and administer any property owned by the regional state in any case and ownerless property found in the region as state property;

12) Establish an internal audit control system in the region, monitor its performance, and oversee the internal audit system.

## 25. Bureau of Revenue

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Revenue shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Cause the enforcement and implementation tax laws, regulations and directives in the region;
2) Determine and collect the federal and common revenues based on deligation of the federal government assigned to be collected through identified by law with the recognition of the regional state;

3) በክልሉ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ተመሥርቶ ጥናቶችን በማካሄድ ክልሉ ያለውን የገቢ መሠረት ለማስፋትና ገቢ የመሰብሰብ አቅሙን ለማሳደግ በትጋት ይሠራል፤

4) በግብር አስተዳደሩ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን በማጥናት እንዲፈቱ ያደርጋል፤

5) በክልሉ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አፈጻጸም በባለቤትነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

6) የታክስ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትንና በማንኛውም ሰው እጅ የሚገኙ ሰነዶችን ይመረምራል፤

7) የታክስ ሕጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፣ ይከሳል፣ ይከራከራል፣ ይህንኑ ለማከናወን እንዲረዱት የራሱን የታክስ ወንጀል መርማሪዎችና አቃብያነ-ሕግ ያደራጃል፣ አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፤

8) ግብር ከፋዩ ኅብረተ-ሰብ የሚፈለግበትን ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል እንዲያዳብርና መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ እንዲረዳ በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል፤

9) ለታክስ አስተዳደሩ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ለማፍራት የሚያስችለውን የሥልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስልት ይቀይሳል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤



3) Work diligently to expand the region's revenue base and increase its revenue collection capacity by conducting research based on the economic activities of the region;

4) Study and cause the solution of problems araised from the tax administration;

5) Lead in the sense of ownership and coordinate the implementation of the ongoing tax system reform program in the region;

6) Examine documents required for the enforcement of tax laws and found in the hand of any;

7) Investigate, charge and argue for crimes committed in violation of tax laws; organize its own tax investigators and prosecutors helping to doso, supervise their implementation;

8) Make the provision of education on different awareness creation platforms so that the taxpayer society develop a culture of paying tax voluntarily and properly know their rights and obligations;

9) Devise and implement training and professional improvement strategies enabling to produce qualified professionals for the tax administration;

10) በክልሉ ውስጥ ዘመናዊ የታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፣ በመስኩ የግልፅነትና የተጠያቂነት መርሆችን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፣ ግብር ወይም ታክስ-ነክ መብቶች በአግባቡ እንዲከበሩ ያደርጋል፤

11) በከተማ አስተዳደሮች ሥልጣን ሥር የሚሸፈኑ የአገልግሎት ገቢዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፣ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

12) ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ የሚደነገግ ሆኖ የከተማ ማዘጋጃ ቤቶችን ገቢ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

13) ለግብር አወሳሰን የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ እነዚህኑ በመጠቀም ታክሶችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

14) የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣት ወይም በሥራ ላይ ያሉትን ማሻሻል ሲያስፈልግ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ረቂቅ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ይህንኑ ለክልሉ መንግሥት አቅርቦ ያስወስናል፤

15) ለግብር ከፋዩ ኅብረተ-ሰብ አማራጭ የታክስ መክፈያ ተቋማትን ያመቻቻል።

## 26. የትምህርት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ትምህርት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦



10) Establish and implement a modern t collection system in the region, provide fa efficient and quality service in accordance wi the principles of transparency ar accountability in the field, and ensure t proper observance of tax or tax-related rights;

11) Determine and collectservice revenues und the jurisdiction of city administrations ar provide technical support therefor;

12) The details being determined by a directive be issued following this proclamatic determine and collect urban municipali revenue and provide professional supp therefor;

13) Collect and compile information required t tax determination, determine and collect tax using same;

14) Conduct research and cause preparation draft when issuing or revising tax lav regulations and directives, and cause to decided by submitting to the regional state;

15) Facilitate tax paying alternative institutions the taxpayer community.

## 26. Bureau of Education

Without prejudice to the existing or subsequ provision of other laws, the Regional Bureau Education shall, pursuant to this proclamati have the following specific powers and duties;

1) የሀገሪቱን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የክልሉን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂዊ እቅዶችና ፕሮግራሞች አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

2) ሀገራዊ የትምህርት ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ በየደረጃው ለሚገኙ የትምህርት ተቋማት ክልል-አቀፍ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ በስታንዳርዱ መሠረት መሟላቱን በኢንስፔክሽን ምርመራ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

3) ሀገራዊ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ ተግባራዊ የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት፣ የቅድመ አንደኛ (አጸደ-ሕፃናት)፣ የልዩ ፍላጎት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንዲሁም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ሥርዓተ-ትምህርቶችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ያሻሽላል፤ የሥርዓተ-ትምህርት ማቴሪያሎች በነጻ ገበያው በማወዳደር በጥራት እንዲታተሙና እንዲሠራጩ ያደርጋል፤ መጽሐፍቱም በገበያ ላይ በበቂ ሁኔታ መገኘታቸውን ያረጋግጣል፤

1) Implement, monitor and evaluate by preparing the region's short, medium and long term strategic plans and programs based on the country's education and training policy, and provide the necessary support thereto;

2) Prepare regionalwide standards for educational institutions found at all levels based on national education standards, followup and monitor the compliance of the standard through its inspectional examination, and take corrective measure when it finds necessary;

3) Prepare curriculums for practical adult basic education, preprimary (kindergarten), special need, primary educationas well as teacher's education colleges based on national standards; followup their implementation, evaluate and revise same; cause the publication of curriculum materials in quality by competing through the free market and to be distributed, and ensure the presence of the books sufficiently in the market;

4) የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጁን ተግባራዊ በማድረግ ለክልሉ ብሎም ለሀገሪቱ አጠቃላይ ልማት እውን መሆን ምክንያት የሚሆን ብቁ ዜጋ የሚፈራበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ሒደቱንም በየጊዜው እየገመገመ ያሻሽላል፤

5) የትምህርት አቅርቦቱን ሚዛናዊና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለማስፋፋት የሚረዱ ልዩ ልዩ ስልቶችንና አማራጮችን በመንደፍ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል፤

6) በክልሉ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታና ፍላጎት ያገናዘበ፣ የጾታ፣ የቦታና ማኅበራዊ ሚዛናዊነትን የጠበቀና ለተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚያግዝ ሆኖ ዴሞክራሲያዊና ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችንና አሠራሮችን ለማጎልበት የሚረዳ ስለ መሆኑ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

7) በክልሉ ውስጥ ከቅድመ- አንደኛ (አጸደ-ሕፃናት) ትምህርት አንስቶ እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚደርሱ ተቋማትን ያደራጃል፣ አዳዲሶችንም ይከፍታል፣ አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውም የትምህርት ግብዓቶችን ለማሟላት የተለያዩ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤



4) Devise a system in which qualified citizens be produced causing for the realization general development of the region as well as tl country by implementing the Gener Education Quality Assurance Packag implement and monitor, and revise samel periodically reviewing the process;

5) Cause the accessibility of quality education f all by designing various strategies and optio helping to promote the provision of educati in a balanced and equitable manner

6) Follow up and supervise the education provid in the region takes into account the realiti and needs of the environment, maintai gender, place and social balance and helps develop democratic and scientific thougl being to help for the practical activity;

7) Organize and open new institutions from pr primary (kindergarten) to high school educati in the region, devise different methods to fulf any educational inputs needed, and impleme same;

8) የክልሉ የትምህርት ፕሮግራሞች ከሀገራዊ የትምህርት ፕሮግራም ጋር ተናቦ ወጥና ሴኩላር ሆኖ እንዲተገበር ያደርጋል፣ ለተማሪዎችና መምህራን በሬዲዮ ትምህርት ማሰራጫ ማዕከላት ተደግፎ ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል፤

9) የመምህራንን፣ የርዕሳነ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮችን ብቃት ለማሳደግ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፣ በጥናቱ ውጤት መሠረትም የቅድመ-ሥራና ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ያደርጋል፣ ሒደቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

10) የግል ትምህርት ተቋማት ከፍተዉ በቢሮዉ ሕግ፣ ደንብና ዉሳኔ መሠረት የትምህርት አገልግሎት ሥራ ለመሥራት ጥያቄ ላቀረቡ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ማኅበራትና ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች ያላቸዉን አጠቃላይ ስታንዳርድ ማሟላታቸዉ ተረጋግጦ አስፈላጊነቱ በቢሮዉ ሲታመንበት የትምህርት አገልግሎት ሥራ እውቅና ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፡፡

11) በክልሉ የግል ትምህርት ቤቶችን እንዲስፋፉ ያመቻቻል፣ ይደግፋል፣ የትምህርት አገልግሎት ክፍያን የመማር ማስተማር አጠቃላይ ወጭንና ወቅታዊ የኑሮ ዉድነትን በባለሙያ በሚያስጠናዉ ጥናት ተመስርቶ ታሪፍን በመመሪያ ይወስናል፣ ያሻሽላል፣ ያስተዳድራል፣ ያስፈጽማል እንዲሁም አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤



8) Cause the provisionthe regional educational programs being inline with the national educational program and in a uniform and secular manner; cause the provision of education to students and teachers through radio supported with education distribution centers;

9) Conduct survey to enhance the competency of teachers, principals and supervisors; cause the provision of pre-employment and continuous professional development training based on the results of the study; monitor and evaluate the process, and take corrective measures;

10) Render educational service recognition license, when its necessity is believed by the bureau ensuring the compliance of standards, to individuals, organizations, associations and aid organizations which requested the bureau to render educational service opening their own private educational institution based on law, regulation and decision of the bureau; renew, supervise, and cancel thereof;

11) Facilitate and support the expansion of private schools in the region; determine tarrif depending on a study conducted by its expertabout tuition, general expenditure of teaching-learning and contemporary living inflation; improve, administer, cause its implementation as well as takes the necessary legal measure;

12) የግል ትምህርት ቤቶች በራሳቸው በጀት በቂ የመማሪያና ሪፈራንስ መጽሐፍት እንዲሁም ሌሎች የትምህርት ግብዓቶች በወቅቱ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

13) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፣ ውጤቱን ይወስናል፣ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ ፈተናዎችን በክልሉ ውስጥ ያስፈጽማል፤

14) ክልላዊ የተማሪ ቅበላና ማቋረጥን በጀት መድቦ ዓመታዊ ጥናት ያካሂዳል፣ በጥናቱም መሠረት የመፍትሔ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

15) ልዩ ልዩ የትምህርት ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያጠናቅራል፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላትና ለሌሎች ድርጅቶች ያሰራጫል፣ ለመረጃ ስብሰባና ትንተና የሚያግዝ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፤

16) በየአካባቢው የሚገኘው ኅብረተ-ሰብና አስተዳደር በየጊዜው በትምህርት አመራሩም ሆነ በበጀት አመዳደቡና አፈጻጸሙ ላይ ሙሉ ተሳትፎና ቁጥጥር ኖሮት ትምህርት ቤቶችን ከቢሮው ጋር በባለቤትነት የሚመራበትን፣ የሚደግፍበትንና የሚቆጣጠርበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

17) በክልሉ ውስጥ ትምህርትን ከማስፋፋትና ጥራቱን ከመጠበቅ አንፃር ልዩ ልዩ ሥልቶችን በመንደፍ በኅብረተ-ሰቡ፣ በግለሰቦችና በድርጅቶች አማካኝነት ተጨማሪ የትምህርት ማስፋፊያ ሀብት ያፈላልጋል፣ ይህንኑ ለትምህርቱ ሥራ ያውላል፤



12) Cause the addressability of sufficient text reference books as well as other educati inputs to private schools by their own budg

13) Prepare, administer and determine grade primary school leaving examinations, caus implementation of national examinations i region;

14) Conduct a research on the regional stu enrollment and retirement allocating bu and take remedial action based on the study

15) Collect, analyze and compile va educational statistics; distributesame concerning bodies and other organizations devise a modern information system assi for data collection and analysis;

16) Devise and implement a system whereby community and administration lead schoo sense of ownership with the bureau, suppor control having periodical full participation controll on the educational leadership, bu allocation and implementation;

17) Moblize additional educational expa resourcefrom the community, individuals organizationsin the view of expanding maintaining the quality of education in region by devising various strategies;

18) ለትምህርት የሚመደበውን የመንግሥትና ዕርዳታ በጀትና ንብረት ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ አጠቃቀሙም ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን ያረጋግጣል፤

19) በሥራ ላይ ያሉና ትምህርት-ነክ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከወጡበት ዓላማና ተግባር አንፃር በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፤

20) ትምህርት-ነክ ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ውሳኔዎችን፣ እቅዶችን፣ የክንውን ሪፖርቶችንና ሌሎች መረጃዎችን በተለያዩ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ለኅብረተ-ሰቡና ለትምህርት ያገባኛል ባዮች ያደርሳል፤

21) የክልሉ የበጀት አቅም በፈቀደዉ መጠን በክልሉ ውስጥ የመንግሥት ትምህርት ቤቶችን ይገነባል፣ ያስፋፋል እንዲሁም ከፌደራል መንግሥትና ወረዳዎች በቀጥታ በሚመደብ በጀትና በልማት ድርጅቶች፣ በግል ባለሀብቶች፣ በኅብረተሰብ ተሳትፎ እና እርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ ትምህርት ቤቶች እንዲገነቡ ያስተባብራል፣ ያስተዳድራል፣ የግንባታ ጥራትና ዲዛይን ሕጉን ጠብቆ ስለመገንባቱ ቁጥጥር ያደርጋል

22) ከትምህርት ግብዓት ጋር የተያያዙ ማናቸዉንም የሀገር ዉስጥና ዓለማቀፍ ግዥ በራሱ ውል ይዞ ይፈጽማል፣ በቂ የትምህርት መጽሐፍት፣ ግብዓትና ፈርኒቸር እንዲሟላ ይሠራል፤



18) Organize and administer the government and aid budget and property allocated to education, and ensure its utility to be cost-effective and efficient;

19) Ensure the practical application of exisiting and educational-related policies, laws, regulations and directives in accordance with their objective and function;

20) Access educational-related policies, programs, decisions, plans, performance reports and other information to the public and education concerned bodies through various media outlets;

21) Build and expand public schools in the region as much as the regional budget allows as well as coordinate the construction of schools by the direct allocated budgetof federal and woredas government and development enterprises, private investers, societal participation and aid organizations; administer same, and monitor its construction observing the construction quality and design law;

22) Implementany domestic and international procurement related to educational inputs contracting by itself, and work for the fulfilment of adequate educational books, inputs and furniture;

23) የዞን፣ ከተማ አስተዳደርና ወረዳ ተጠሪ የትምህርት ተቋማትና መሪዎች በቢሮዉ የወረደላቸውን የሥራ እቅድ በሕግና ደንብ መሠረት ሕዝብን የሚያረካ የመማር ማስተማር አጠቃላይ አገልግሎት ስለ መስጠታቸው ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣ ይገመግማል እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

24) በክልሉ የመንግሥት መምህራን ትምህርት ኮሌጆችንና ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን በቂ በጀት ይዞ ይገነባል፣ ያደራጃል፣ ያስፋፋል እንዲሁም በልማት ድርጅቶች፣ በግል ባለሀብቶችና እርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ የሚስፋፉበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ያስተዳድራል፤

25) የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በብቃት መወጣት የሚያስችሉ የሥርዓተ ትምህርት፣ የፈተና አስተዳደር፣ የተማሪና መምህራን አስተዳደር፣ የትምህርት ግብዓት አቅርቦት፣ የመምህራን ኮሌጆችና ትምህርት ቤቶች አስተዳደር፣ የትምህርት አመራርና ዲኖች አስተዳደር እንዲሁም የበታች ዞንና ወረዳ ትምህርት ተቋማት ቁጥጥር ሥርዓትና ሌሎች ተያያዥ ዝርዝር መመሪያዎችን በማዉጣት በሥራ ላይ ያውላል፤

26) በግልና በመንግሥት ትምህርት ተቋማት የሚካሄደውን የትምህርት አሰጣጥ አስመልክቶ የትምህርት ጥራት ኢንስፔክሽንና ኦዲት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰዱ ያደርጋል፤



23) Conduct an oversight and evaluate on the provision of public satisfying teaching-learning general service by zonal, cvity administration and wereda accoutable educational institutions and leaders in line with the work plan descended from the bureau on basis of law and regulation, evaluate as well as take corrective measure therefrom;

24) Build, organize and expand public teachers' colleges and special boarding schools in the region having sufficient budget as well as create conducive environment for their expansion by development enterprises, private investors and aid agencies, and administer same;

25) Implement byenacting detailed curriculum examination administration, student and teachers administration, supply of educational input, administration of teachers' colleges and schools, administration of educational leadership and deans as well aslower zonal and wereda education institutions monitoring system and other related directive enabling it to efficiently carry out its duties and responsibilities;

26) Takeand cause to be taken corrective measure by conducting educational quality inspection and audit regarding the provision of education in private and public educational institutions;

27) ወደፊት የትምህርት ጥራትና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ባለሥልጣን በደንብ እስኪቋቋም ድረስ በየደረጃው ለሚገኙ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፡፡

## 27. የጤና ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጤና ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ የክልሉ ሕዝብ ጤና የሚጠበቅበትን ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣ በክልሉ ውስጥ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
2) ስለሕዝብ ጤና አጠባበቅ የወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
3) በየደረጃው የሚገኙትን የጤና አገልግሎትም ሆነ የማሠልጠኛ ተቋማትና የጥናትና ምርምር ማዕከላት ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤
4) በክልሉ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ደረጃቸውንና ጥራታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፤



27) Render, renew and revoke Certificate of professional Proficiency to teachers, principals and supervisors at all levels until the Education Quality and Professional Qualification Authority is fully established in the future.

## 27. Bureau of Health

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Health shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1) Prepare the health care plans and programs whereby the health of community in the regional state might be protected in line with the country's health policy and strategy, and implemented same upon approval as well as cause the expansion of health services in the region;
2) Ensure the due observance of laws, regulations and directives issued about public health in the region;
3) Organize and administer health services as well astraining institutions and research centers found at all levels;
4) Supervise the observance of standards and qualities of drugsand medical equipments to be used in the region;

5) በክልሉ ውስጥ በግል ባለሀብቶችና በድርጅቶች ለሚቋቋሙ ጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮች፣ የዲያግኖስቲክ ማዕከላትና መድኃኒት ቤቶች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የወጡትን መስፈርቶች ጠብቀው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፤

6) አዲስ የተቋቋሙ የመንግሥት የጤና ተቋማት አስፈላጊውን ደረጃ ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ሥራ እንዲጀምሩ ያደርጋል፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን በበላይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

7) በክልሉ ውስጥ በሕዝብ ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ለዚሁ የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

8) ፍቱንነታቸው የተረጋገጠ የባህል መድኃኒቶችና የሕክምና ዘዴዎች ከዘመናዊው ሕክምና ጋር ተዋሕደው በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ ባለሙያዎችን ያደራጃል፣ ለዘርፉ የወጣውን ሕግና ደንብ ጠብቀው ስለመሥራታቸው ይቆጣጠራል፤

9) የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ ለማስፈጸም የተዘረጉና የሚዘረጉ ፕሮግራሞችንና ስትራቴጂዎችን በክልሉ ውስጥ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤

10) የጤና መሠረተ-ልማት ግንባታዎችን ያስፋፋል፣ አስፈላጊ ግብዓቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤



5) Render professional license to health scen clinics, diagnostic centers and drug vendors might be established by private investors organizations in the region, and oversee observance of standards issued by nat level;

6) Cause the commencement ofnewly-establi public health centers by ensuring compliance of the necessary level, as we follow up and monitor their service del thereof;

7) Ensure and supervise that professi engaged in the public health service acti throughout the region have met the stan set for such duties;

8) Cause the application of traditional medi and treatment methods, whose curative r has been ascertaind, integrated with m medications; organize professionals of and supervise their activity whethe compliance with the laws and regulations i for the sector;

9) Execute and cause the execution of pro and strategies set out or to be set c implement the national health policy throu the region;

10) Expand health infrastructure constructio ensure the fulfilment of necessary inputs;

11) የሕዝቡ ጤና እንዲጠበቅ ለማድረግ የኳራንቲን ቁጥጥር ያካሂዳል፤

12) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የመንግሥትም ሆነ የግል የጤና ኮሌጆች ለሚመረቁ የጤና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈተናና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሙያ ምዝገባ ያካሂዳል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፤

13) በመከላከል ላይ አተኩረው የሚፈጸሙ የጤና ልማት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስፈጽማል፤

14) በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ ጤና-ነክ የምርምር ተግባራትን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስፈጽማል፤

15) በክልሉ ውስጥ ለጤናዘርፉ ዕድገት የሚያግዝ የገንዘብ ማግኛ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

16) በክልሉ ውስጥ የጤና መድህን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

17) በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱትን የሀይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

18) የኅብረተ-ሰብ ጤና አደጋዎችንና ወረርሽኞችን ክስተት ይተነብያል፣ ይቃኛል፣ የዳሰሳ ጥናቶችና ዝግጅቶችን ያካሂዳል፣ እንዳስፈላጊነቱ ፈጣን ምላሽ ይሰጣል፣ የመልሶ ማቋቋም ተግባራትን ያከናውናል፤

11) Undertake quarantine control with the view to taking care of the public health;

12) In collaboration with pertinent bodies of the issue, administer competence assurance examinations and certificates for those health professionals who have graduated from public as well as private health colleges found in the region; effect professional registration; issue and renew license threreof;

13) Coordinate, direct and cause to execute health development activities implemented focusing on prevention;

14) Coordinate, direct and cause to execute health related research works undertaken in the region;

15) Devise financing system helping for the promotion of health care sector in the region as well as direct and supervise over its implementation thereof;

16) Put in place the health insurance system in the region; cause the implementation of same and follow up its implementation;

17) Direct and supervise over the hygiene and environmental health care activities;

18) Forcast the might be occurance of public health hazards and epidemics; undertake surveillance and preparation, as demmed as necessary it gives quick response, and conduct rehabilitation activities thereof;

19) በጤናው ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት፣ ለእናቶችና ሕፃናት ጤና አጠባበቅ፣ እንዲሁም ኤችአይ ቪ/ ኤድስን፣ የወባና የሳንባ ነቀርሳ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፤

20) የክልሉን የጤና መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ በጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

21) በክልሉ ውስጥ የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የሕዝብ ጤና አጠባበቅ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከትለው መሥራታቸውን በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ጥፋተኞች ሆነው ሲገኙም አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

22) የግል ክሊኒኮች፣ ላቦራቶሪዎች፣ ሆስፒታሎችና የመድኃኒት ንግድ መደብሮች የመንግሥትን ደንብና መመሪያ አክብረው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፣ ጥፋተኞች ሆነው ሲገኙም እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

23) በአዳዲስ የጤና ተቋማት ዘንድ ልዩ ልዩ የጤና አገልግሎቶች እንዲጀመሩ ጥያቄ ሲቀርብለት ፈቃድ ይሰጣል፣ ደረጃቸውን ጠብቀው መሥራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

24) የሀገሪቱ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ በተቀናጀ መንገድ እንዲተገበር ሁለንተናዊ ድጋፍ ይሰጣል፤



19) Work with special focus on the health care mothers and children as well as the prevention control of HIV/AIDS, malaria and TB diseases achieve the sustainable development goals in the hea sector;

20) Devise the regional health information system cause its utilization thereof;

21) Closely follow up and supervise that the food beverage service delivery institutions in the reg operate in compliance with the public hea regulations and directives; and take and cause to taken administrative measures against those found be at fault thereof;

22) Supervise over private clinics, laborator hospitals and drug dealers operate in compliance v the government regulations and directives; take cause to be taken administrative measures against th found to be at fault;

23) Authorize license for commencement of vari health services by new health instituions upon t request, and follow up and supervise over t activities as per the standard;

24) Render an overall support for the integr implementation of the country's HIV/AIDS polic the region;

25) በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ የሚሠሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ተገቢውን ሥልጠናና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በየደረጃው የሚገኙ አካላት ለችግሩ የበለጠ ትኩረት ሰጥተው የኅብረተ-ሰቡን ግንዛቤ ለማጎልበት ይቻል ዘንድ የተሟላ ድጋፍ በማሰባሰብ እንዲንቀሳቀሱ ያበረታታል፤

26) በክልሉ ውስጥ ለኤድስ በሽታና ለኮቪድ 19 የማያጋልጥ የተሟላ ግንዛቤና ጤናማ ባሕርይ ይጐለብት ዘንድ የክልሉን ኅብረተ-ሰብ በተለያዩ ዘዴዎች ይቀሰቅሳል፤

27) ሴቶች፣ ወጣቶችና ለበሽታው በይበልጥ የተጋለጡ ሌሎች የኅብረተ-ሰብ ክፍሎች ራሳቸውን ከበሽታው ለመከላከል ይቻላቸው ዘንድ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

28) ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች፣ ሕሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት፣ ታዳጊ ወጣቶችና ቤተ-ሰቦቻቸው ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበር በትጋት ይሠራል፣ ይኼው በሌሎች ዘንድ መከበሩን ያረጋግጣል፡፡

## 28. የፍትሕ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ፍትሕ ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-



25) Facilitate conditions in which organizations and individuals that work on HIV/AIDS prevention and control activities get the appropriate training and support; encourage bodies at different levels to work in focus by collecting complete support enabling to develop the society's awareness;

26) Aware the society of the region using different methods that fulfilled awareness and healthy conduct which does not expose for AIDS and COVID 19 to be developed in the region;

27) Cause women, youths and other parts of the society who are highly exposed for this disease get the necessary information to be able to prevent themselves from the disease;

28) Work hard for the enforcement of human rights of people who live with virus, patients and orphans due to the case of AIDS, youths and their families, and ensure the observance of same by others;

## 28. Bureau of Justice

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Justice shall, pursuant to this proclamation; have the following particular powers and duties:

1) በፌደራል መንግሥቱ ተዘጋጅቶ የጸደቀው የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ይሠራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
2) በክልሉ ውስጥ የወንጀል ፍትሕ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀት፣ ለመተንተንና ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፤
3) በሕግ ጉዳዮች ረገድ የክልሉ መንግሥት ዋና አማካሪ ሆኖ ይሠራል፤
4) የዓቃቤ-ሕግ የውሳኔ አሰጣጥና የፍቅደ-ሥልጣን አጠቃቀም ወጥነትን ለማረጋገጥ በፌደራሉ ፍትሕ ሚኒስቴር የጸደቀው መመሪያ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤
5) ዓቃብያነ-ሕግ የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች በሕግ መሠረት መሰጠታቸውን የሚያረጋግጥ የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎች ማከናወኛ ክፍል ያደራጃል፣ ጉድለቶችን በጥናት ላይ ተመሥርቶ ይለያል፣ በግኝቱ መሠረትም የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል ወይም በሌሎች አካላት እንዲወሰዱ ያደርጋል፤
6) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በትርፍ ላይ ያልተመሠረተ ዓላማ ይዘው የተቋቋሙና በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ማኅበራትንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ሕጋዊነት በማረጋገጥ ይመዘግባል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፤



1) Work for the application of thecriminal jus policy being prepared and approved by federal government in the region; coordin monitor and ensure same;
2) Establish and implement a system to coll organize, analyze and disseminate crim justice information in the region;
3) Work as Chief Advisor of the Regi Government in matters of law;
4) Ensure implementation of the direc approved by the federal ministry of justic the region to crosscheck consistency of prosecutor's decision-making and use of po of will;
5) Organize an oversight implementation uni ensure that decisions made by prosecutors made in accordance with law; identify based on research, take corrective meas based on findings and causeto be taken by bodies;
6) Register associations and non-governm organizations established on basis of non- and operatingin the region by crossche their legitimacy in collaboration with rel bodies; supervise and cancelsame collaboration with concerned bodies c issue;

7) በክልሉ ውስጥ በትርፍ ላይ የተመሠረተ ዓላማ ይዘው የሚንቀሳቀሱ የንግድ ማኅበራትን የመመሥረቻ ጽሑፎች፣ የመተዳደሪያ ደንቦችና የነዚህኑ ማሻሻያዎች ተቀብሎ በመመርመርና ሕጋዊነታቸውን በማረጋገጥ ይመዘግባል፤

8) ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 7 ድረስ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ:-

ሀ) በሌላ ሕግ ለክልሉ የገቢዎች ባለሥልጣን የተሰጠው የአቃቤ-ሕግነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉም ሆነ በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ስር የሚወድቅና በፖሊስ የተጀመረ የወንጀል ምርመራ ቢኖር አስቀድሞ እንዲያውቀው መደረግ ያለበት ሲሆን የምርመራ አካሄዱን ሕጋዊነት ይከታተላል፣ ይመራል፣ በተጀመረ የወንጀል ምርመራ ላይ ሪፖርት እንዲቀርብና ምርመራው በአግባቡ ተከናውኖ እንዲጠናቀቅ ያደርጋል፤

ለ) በሕዝብ ጥቅም መነሻነት ወይም በወንጀል የማያስጠይቅ ሁኔታ መኖሩ በግልፅ ሲታወቅ የወንጀል ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠ የወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል ሊያደርግ ይችላል፣ ምርመራው በሕግ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፣ ከነዚሁ ተግባራት ጋር በተያያዘም ለፖሊስ ወይም ወንጀል ለመመርመር ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል፤



7) Register commercial associations operating for profitmaking in the region by receiving and reviewing their founding documents, bylaws and amendments and ensuring their legitimacy:

8) Without prejudice to the provisions of sub-articles from 1 to sub-article 7 hereabove, concerning criminal cases:

A) Without prejudice to the prosecution authority given to the regional revenue authority in other law.followup and direct the legitimacy of the process of criminal investigation which lied under the jurisdiction of the regional as well as the federal courts and commenced by police being priorly notified to it; cause the completion of investigation on commenced criminal investigation being reported and properly investigated;

B) It may terminate criminal investigation or resume same when it is clearly known that there is a condition of public interest or non-criminal liability; ensure the implementation of the investigation inline with law, and give the necessary order to police or other party having power of investigation to crime in relation to these activities;

ሐ) በምርመራ መዛግብት ጥናትና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ከፖሊስ በኩል ተፈላጊውን ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፣ በወንጀል መዛግብት ላይ የተሰጡ የዓቃቤ-ሕግና የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለሚመለከተው ፖሊስ ያሳውቃል፣ የወንጀል ምርመራ መዛግብትን አስመልክቶ በየደረጃው ዓቃብያነ-ሕግ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ በፖሊስ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ ያጣራል፣ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤

መ) በየደረጃው የሚገኝ ዓቃቤ-ሕግ በትይዩ ባሉት ፍርድ ቤቶች ጉዳዮችን በከሳሽነት ይዞ የመከራከር መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በስር ዓቃብያነ-ሕግ የተሰጡ የክስ አያስቀርብም ውሳኔዎችን ይመረምራል፣ ግድፈት ያጋጠመው እንደሆነም ወዲያውኑ እንዲታረም ያደርጋል፣ የተጠናቀቁ የምርመራ መዛግብትን ከሕግና ከማስረጃ አንፃር መርምሮ የአያስከስስም ውሳኔ ይሰጣል፤

ሠ) የእጅ ተፈንጅ ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ውሳኔ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ለዚህም ከፖሊስና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤

ረ) ለወንጀል ጉዳይ ምስክሮች በወቅቱ መጥሪያ እንዲያደርስና ምስክሮችንም ወደ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ለፖሊስ ትእዛዝ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም የዓቃቤ-ሕግ ምስክሮች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

C) It may request the necessary assistance fro police onrecord investigation study a decision making process; inform prosecuti and court decisions given on criminal records concerned police; verify complaints submitt by police on dicisions given by prosecutions all levels concerning criminal investigati records, and makes decisions thereof;

D) Without prejudice to the right of litigation prosecutors found at all levels in the paral courts,review no-proceeding decisions made lower prosecutors, cuase the immedi correction if it faces errors; and give proceeding decision on completed investigat records in the light of law and evidence;

E) Facilitate speedy decision-making condition cases of red-handed crimes, work collaboration with police and other stakehol forsame;

F) Give order to police to criminal case sum witnesses in time and bring the witnesse court, and give the necessary protectio prosecution witnesses when necessary;

ሰ) የጥፋተኝነት ድርድር እንዲካሄድ ይወስናል፣ ድርድር ያደርጋል፣ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ እንዲወሰድ ይወስናል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ሸ) በተሻሻለው የክልሉ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 237/2008 ዓ.ም የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን አስፈጻሚ አካላት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባራቱን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 254/2010 ዓ.ም እና በሌሎች ሕጎች እንደ አግባቡ ለኮሚሽኑና ለንግድ ቢሮ ተሰጥቶ የነበረውን የዓቃቤ-ሕግነት ሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት በሥራ ላይ ያውላል፤

ቀ) በግብር (ታክስ) ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ለክልሉ ገቢዎች ቢሮ በዚህ አዋጅና በሌላ ሕግ የተሰጠው የአቃቤ-ሕግነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉን መንግሥት በመወከል በወንጀል ጉዳዮች ክስ ይመሠርታል፣ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ክስ ያነሣል፣ የተነሳ ክስ እንዲቀጥል ያደርጋል፤

በ) ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መፈጸማቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፣ ሳይፈጸሙ ከቀሩ ወይም አፈጻጸማቸው ሕግን ያልተከተለ ከሆነም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት በማመልከት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤



G) Determine conduction of guilt negotiation, negotiate, determine alternative remedial measure to be taken, and monitor its implementation;

H) Apply the prosecution power, pursuant to this proclamation, given it by the Revised Regional Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation No. 237/2016,the Revised Establishment and Determination of its Powers and Duties of the Executive Bodies of the National Regional State Proclamation No. 254/2018, and other laws to the Comission and Tade Bureau as its context;

I) Without prejudice to the prosecution power given to the regional revenue bureau pursuant to this proclamation and other law regarding criminals committed on tax, institute suit on behalf of the regional government concerning criminal cases; terminate suits when it finds necessary for the public good, and cause the resumption of terminated suits;

J) Monitor the implementation and enforcement of criminal decisions and orders made by courts; cause corrective measure to be taken by applying the case to the court which made the decision if same are not executed or their implementation is not in line with law;

ተ) በፍርድ ቤት የሚወሰኑ የወንጀል ቅጣቶች በአግባቡ እንዲፈጸሙ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ያደራጃል ወይም መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤

ቸ) የሞት ቅጣት ውሳኔዎችን ለሪፐብሊኩ ፕሬዚደንት ያቀርባል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡

9) የፍትሐብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ፡-

ሀ) የክልሉ ሕዝብና መንግሥት መብቶችና ጥቅሞች ሕጋዊ ወኪል በመሆን ይደራደራል፣ ይከራከራል፣ ያስከብራል፣ እንዲከበሩ ያደርጋል፣ የሚከበሩበትን ሒደት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ) የክልሉ መንግሥት ተቋማት ሀብትና ንብረት ያለአግባብ እንዳይባክንና እንዳይመዘበር ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሐ) ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ መንግሥት ፕሮጀክቶች የውል ዝግጅትና ድርድሮችን ያካሂዳል፣ የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የሕዝብ መብትና ጥቅም ይጎዳል ብሎ ሲያምን በሌሎች ጉዳዮች ጭምር የውል ሰነዶች ዝግጅትና ድርድር ያደርጋል ወይም የሚመለከታቸውን አካላት ያማክራል፤

K) Organize or ensure the organization of syste[m] enabling to properly implement crimi[nal] penalties made by court;

L) Submit death sentences to President of t[he] Republic and monitor their implementation;

9) Concerning Civil Matters:

A) Negotiate, argue, enforce, respect, and moni[tor] the rights and interests of the people a[nd] government of the region;

B) Make the proper oversight in order not t[o] regional government institutions' wealth a[nd] property to be improperly wasted and exploit[ed];

C) Conduct contract preparation and negotiati[on] in the region based on determination [of] regulation to be issued following [this] proclamation in collaboration with conce[rned] bodies, make preparation of contract docum[ents] and negotiateor consult concerned bodies [w]it believesthe regional government offices [and] public rights and interests will be harmed;

መ) ከክርክር በፊትም ሆነ በኋላ እንዲሁም በክርክር ወቅት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ምክር ይሰጣል፣ አቅጣጫዎችን ያሳያል፣ በሕግ መሠረት የፍርድ ውሳኔዎችን ያስፈጽማል፤

ሠ) ከሥር አቃብያነ-ሕግ በሚላኩለት ወይም በሚቀርቡለት የፍትሐብሔር መዛግብት ላይ የክስ አይቀርብም ውሳኔዎችን ይሰጣል፣ የሥር አቃቤ-ሕግ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብለት ወይም በራሱ አነሳሽነት ውሳኔውን መርምሮ ያጸናል፣ ይሽራል ወይም ተለዋጭ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

ረ) በየደረጃው ያለ ዓቃቤ-ሕግ በትይዩ ባሉት ፍርድ ቤቶች በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ጉዳዮችን ይዞ እንዲከራከርና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ደረጃውን ሳይጠብቅ ጉዳዩን ተረክቦ እንዲሟገት ያደርጋል፤

ሰ) ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ወደ ፊት በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች አንዱ ከሌላው ጋር ያልተግባቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች ያጋጠሙ እንደሆነ እርስ በርስ በማደራደር ዉሳኔ ላይ እንዲደርሱ ጥረት ያደርጋል፣ መስማማት ካልቻሉ ግን የመጨረሻ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡

ሸ) በልዩ የሥራ ጠባያቸው ምክንያት የራሳቸው ነገረ-ፈጅ ካላቸው መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ውጭ ያሉትን ክልላዊ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመወከል

D) Provide advice to government offices on necessary matters before, after, and during debates; show directions, and cause the execution ofdecisions in accordance with the law;

E) Render no-proceeding decisions on civil records sent from or submitted by lower prosecutors; approve the decision by reviewing same when complaint is submitted to it or by its initiation on a decision made by lower prosecutor; reverse, or give an alternative order;

F) Make prosecutors found at all levels debate cases in parallel courts as plaintiff or defendant, andcause the litigation of cases by receiving same without respecting the level if it finds necessary;

G) The details being determined by a regulation or directive to be issued in the future for implementation of this proclamation, make efforts to arrive at an agreement via negotiating each other if disagreements araise from the regional state offices on civil cases; and give final decision if they fail to agree;

H) Institute suit before federal and regional courts, any judicial hearing body or arbitration conference on behalf of regional public offices except offices and organizations those have their own prosecutor due to their unique work nature;

በፌደራልና በክልል ፍርድ ቤቶች፣ በማናቸውም የዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባኤ ፊት ክስ ይመሠርታል፣ ሲከሰሱም መልስ ይሰጣል፣ ይደራደራል፣ ይከራከራል፤

ቀ) በልዩ ሁኔታ የራሳቸው ነገረ-ፈጅ ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ተከራካሪ በሚሆኑባቸው የፍትሐብሔር ክሶችና የመብት ጥያቄዎች ዙሪያ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን ያከናውናል፣ የሕግ ድጋፍ ሲጠየቅ እገዛ ያደርጋል፤

በ) በሕግ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በሆኑ ጉዳዮች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በመወከል ሲከሱም ሆነ ሲከሰሱ ይከራከራል፣ ይደራደራል፣ እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች የሕግ ድጋፎችን ይሰጣል፤

ተ) በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት የደረሰባቸውና ገንዘብ ከፍለው መከራከር የማይችሉ አቅም የሌላቸው ሰለባዎች፣ የአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናት፣ ድሀ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የኤችአይ ቪ/ኤድስ ሕሙማንን ወክሎ በድርድር ወይም በክልሉ ፍርድ ቤቶችና በሌሎች የዳኝነት አካላት ዘንድ ክስ በመመሥረትና በመከራከር እነዚሁ ወገኖች ካሣ እንዲያገኙና ፍትሐብሔር ነክ ጥቅሞቻቸው እንዲከበሩ ያደርጋል፤



render response, negotiate and debate when they are sued;

I) Conduct oversight workson civil litigations of civil suits and right enquiries where public offices having their own prosecutor due to their unique nature of work are litigants, and assist when asked legal support;

J) Litigate and negotiateon behalf of cooperatives when they sue as well as to be sued in matters exceeding the amount of money specified by law, and provide other legal support as deemed;

K) Cause effect of compensation and observance their civil benefits by instituting suit and litigating thereof on behalf of rigorous victim of crime and unaffordable for litigation vulnerable children for harm, poor women disables, the elderly and HIV/AIDS patient through negotiation or before the regiona courts and other judicial bodies;

ቸ) በክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በሌሎች ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው የሕብረተ-ሰብ ክፍሎች መካከል በሚነሱ የፍትሐብሔር ክርክሮች ጉዳዩን በድርድር ለመፍታት ይወስናል፣ በድርድር መፍታት ያልተቻለ እንደሆነ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ጉዳይ ይዞ ይከራከራል፡፡

10) የሕግ ማርቀቅና ሕጎች ማጠቃለልን በተመለከተ፡-

ሀ) ከክልሉ መንግሥት ተቋማት የሚመነጩ የሕግ ሐሳቦችን ተቀብሎ ረቂቅ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ በሌሎች አካላት ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት ጥራታቸውን ጠብቆ ያበለጽጋል፣ የተዘጋጁ መመሪያዎችን በተመለከተም ለአሠራር ያመች ዘንድ ተገቢውን ቁጥር ይሰጣል፣ ለሕዝብ ይፋ መሆናቸውንም ይከታተላል፤

ለ) በክልሉ ውስጥ የተለያዩ አካላት የሚያዘጋጇቸው የሕግ ረቂቆች ከሕገ-መንግሥቱም ሆነ ከክልሉና ከፌደራል መንግሥቱ ሕግጋት ጋር የተጣጣሙ ስለመሆናቸው ይከታተላል፣ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ሙያዊ አስተያየት ያቀርባል፤

ሐ) የክልሉ መንግሥት ሕጎች ተግባራዊ መደረጋቸውንና አተገባበራቸውም ወጥነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፣ የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ሥራቸውን በሕግ መሠረት ማከናወናቸውን በቅርብ ይከታተላል፤



L) Decide to resolve disputes through negotiation on civil litigations araised between the regional government offices and other sections of the society in need of support, and litigate on behalf of the government officesif it is not resolved through negotiation.

10) Concerning Legislative Drafting and Consolidation Laws:

A) Prepare draft proclamations, regulations and directivesreceiving legal proposals imanated from the regional government institutions; develop same maintaining their quality when submitted to it being prepared by other bodies; provide appropriate numbers for use of simplification and monitor their officiality to the public concerning prepared directives;

B) Monitor the comformity of legal drafts prepared by various bodies in the region with the Constitution as well as the laws of the State as well as the federal state; submit professional feedback to direct concerning sections;

C) Ensure the applicability and uniformity of the regional laws; and closely followup the performance of the regional executive offices in accordance with law;

መ) በሥራ ላይ ያሉትን የክልሉ ሕጎች በየጊዜው እያጠና ወይም በሌሎች እያስጠና የሚሻሻሉበትን የውሳኔ ሐሳብ በማዘጋጀት ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ለማሻሻያዎቹ የሚያስፈልጉትን ረቂቆችን በማዘጋጀት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥልጣን አካላት አቅርቦ ያስጸድቃል፤

ሠ) የሕግ ጉዳዮችን በተመለከተ የክልሉን መንግሥት ተቋማት ያማክራል፤

ረ) ዓቃብያነ-ሕግ ስለሥራቸው ያላቸውን አመለካከት፣ እውቀትና ክህሎት በተከታታይና በየደረጃው ለማሳደግ ይቻላቸው ዘንድ ተገቢውን የአቅም ግንባታ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ሰ) የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ለክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት፣ ሌሎች ተሿሚዎች፣ የሕዝብ ተመራጮች፣ ሠራተኞች፣ እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ተሳታፊዎች እንዳስፈላጊነቱ የንቃተ-ሕግ መርሃ-ግብሮችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

ሸ) የክልሉንና በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት ያላቸውን የፌደራል መንግሥት ሕጎች የማሰባሰብና የማጠቃለል ሥራዎችን ያከናውናል።



D) Submit recommendation by preparing same t the regional government on the amendment c existing laws of the region through reviewin and causing to be reviewed by others; cause th approval by preparing drafts necessary to th ammendments submiting to the concerne authoritative bodies upon permission

E) Advise the regional government institutions c legal matters;

F) Cause the gain of proper capacity building fc prosecutors enabling them to develop the attitude, knowledge and skills continously an level-by-level;

G) Organize legal awareness programs to th regional government officials, other nominee elected officials, civil servantsas well as priva sector participants as demeemed as necessary s as to ensure the rule of law; provide same ar cause to be provided;

H) Carry out the collection and consolidati works of regional and federal laws applicat within the region.

11) ሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ፡-

ሀ) የሰብዓዊ መብት ጥሰትን በተመለከተ የሚቀርቡ አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ እንዲመረመሩ ያደርጋል፤

ለ) የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እቅድ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን ያካተተ ስለመሆኑ በቅርብ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

ሐ) ነፃ የሕግ ድጋፍ አሰጣጥ ስትራቴጂዎችን ይቀርፃል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ በመስኩ የሚሰማሩ አካላትን ያስተባብራል፤

መ) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በፌደራል ደረጃ የወጣው የብሔራዊ ሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ-ግብር በክልሉ ውስጥ ያለውን ተፈጻሚነት ይከታተላል፤ በክልል-አቀፍ ደረጃ ተሳታፊ የሚሆኑትን ወገኖች እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፣ አግባብ ላላቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

ሠ) በፖሊስ ጣቢያና በማረሚያ ቤት ጥበቃና ቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎችን ይጎበኛል፣ አያያዛቸውና ቆይታቸው በሕግ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፣ ሕግን ተላልፈዋል በተባሉ ሰዎች ላይ በሕግ መሠረት እርምጃዎችን ይወስዳል ወይም እንዲወሰዱ ያደርጋል፤



11) Concerning Human Rights:

A) Investigate and cause the investigation ofappeals and complaints submitted concerning human rights violations;

B) Closely Follow up and support about the inclusion of human rights issues by the regional government plan;

C) Develop free legal aid delivery strategies, monitor their implementation, and coordinate parties to be engaged in the field;

D) Monitor the implementation of the National Human Rights Action Plan issued by federal level in the region in collaboration with concerned bodies of the issue; coordinates activities of participants at the regional level, and report same to appropriate authorities;

E) Visit people in police station and correction center, ensure that their treatment and detention is carried out in accordance with law, and take legal measure against those who transpassed law;

ረ) የክልሉ ኅብረተ-ሰብ ሰብአዊ መብቶቹንና ግዴታዎቹን በውል ተገንዝቦ ሕግ አክባሪና አስከባሪ እንዲሆን በተለያዩ ዘዴዎች የሰብአዊ መብትና የንቃተ-ሕግ ትምህርት ይሰጣል፣ በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤

ሰ) ሀገሪቱ ያጸደቀቻቸው ወይም የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በክልሉ ውስጥ ያላቸውን ተፈጻሚነት ይከታተላል፤

ሸ) እንደ ሥርዓተ-ጾታና ኤድስ ያሉ ዘርፈ-ብዙና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተ-ሰብ ክፍሎችን ያካተቱ የሰብአዊ መብት ተግባራትን ያከናውናል፤

ቀ) ሰብዓዊ መብትን የሚመለከቱ ፕሮጀክቶችን ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

በ) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ብሔራዊ የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ረገድ ይተባበራል፣ ያግዛል።

12) የጠበቆች አስተዳደርን በተመለከተ፡-

ሀ) በክልሉ ፍርድ ቤቶች ደረጃ የጥብቅና አገልግሎት ለሚሰጡ ጠበቆች በሕግ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

ለ) የጠበቆችን አገልግሎት አሰጣጥ በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤



F) Provide human rights and legal-awareness education in various ways so that the regional people become obedient to law and cause the respect of lawfully recognizing their human rights and obligations, and coordinate the activities of those involved in the sector;

G) Monitor the implementation of international and continental human rights treaties ratified or adopted by the country;

H) Perform human right activities on multifaced sectors such as gender and AIDS, and inclusive of vulnerable groups;

I) Coordinate, support, and monitor projects concerning human rights;

J) Coordinate and assist in the preparation of national implementation report on human rights treaties that the country has received upon request from concerned bodies.

12) Concerning the Administration of Attorneys:

A) Render, renew, suspend, and cancel license for attorneys giving prosecution service in the regional courts level;

B) Closely followup and monitor the provision of services of attorneys;

ሐ) ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ደሀ የኅብረተ-ሰብ ክፍሎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማስከበር የግል ጠበቆችን፣ የጠበቆች ማኅበራትን ወይም ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ያላቸውን የሲቪል ማኅበራት በማስተባበር ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

13) የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጥን በተመለከተ:-

ሀ) በክልሉ ውስጥ የሰነዶችን ሕጋዊነት ያረጋግጣል፣ ይመዘግባል፤

ለ) የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የሽያጭ ውልን ሕጋዊነት በማረጋገጥ ይመዘግባል፤

ሐ) የተጭበረበረ ሰነድ ወይም ያለአግባብ የተረጋገጠና የተመዘገበ ሰነድ በሚገኝበት ጊዜ ይህንኑ ያግዳል፣ ያጣራል፣ ያለአግባብ ተሰጥቶ ሲገኝም ይሰርዛል፡፡

14) የአገልግሎት አሰጣጥ፣ የቅሬታ ማስተናገጃና ስነ-ምግባር ክትትልን በተመለከተ:-

ሀ) ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የደንበኞች ፍላጎቶች በጥናት በመለየት የአገልግሎት አሰጣጥ ስልት ይቀይሳል፤

ለ) በግልም ሆነ በወል የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ ያጣራል፣ ፍትሐዊ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤



C) Cause on the provision of free legal aid services to vulnerable sections of the society by coordinating private attorneys, attorneycivic associations having special prosecution license in order to respect the justice aquiring rights of the vulnerable poor sections of the society.

13) Concerning Registration and Verification of Documents:

A) Verify and record the legality of documents in the region;

B) Register sales contract of immovable properties by verifying the legality of same;

C) Block and filter when fraudulent document or improperly verified and registered document is found, and delete when it is improperly provided.

14) Concerning the Followup of Service Delivery, Grievance Handling and Ethics:

A) Design service delivery strategies by identifying the prioritize customer needs through study;

B) Verify complaints and suggestions given by private as well as in common by receiving them, and give fair decisions therefor;

ሐ) ይህንን አዋጅና በሥራ ላይ ያሉ ሌሎች ሕጎችን በመተላለፍ የዲሲፕሊን ጥፋት በፈጸሙ የየደረጃው አቃብያነ-ሕግና ጠበቆች ላይ እንደተገቢነቱ በአቃብያነ-ሕግ አስተዳደርም ሆነ በጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባኤዎች ፊት የዲሲፕሊን ክስ ይመሰርታል፣ ይከራከራል፤

መ) ከዲሲፕሊን ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ ዓቃብያነ-ሕግንና ጠበቆችን አስመልክቶ መሥሪያ ቤቱ በሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ ለመደበኛፍርድ ቤቶች በሚቀርቡ የይግባኝ ጉዳዮች ላይ መልስ ይሰጣል፣ ፍርድ ቤት ቀርቦ ይከራከራል፤

ሠ) የተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የቅሬታ አቀባበልና የስነ-ምግባር ደንቦችና መመሪያዎች በሁሉም ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ዘንድ ተገቢውን ግንዛቤ አግኝተው በአግባቡ እንዲተገበሩ ለማስቻል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

ረ) በቢሮው ውስጥ የለውጥ ፕሮግራሞችን ገቢራዊነትና የክልሉን ፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ውጤታማነት በቅርብ ይከታተላል፡፡

15) በዚህ አዋጅ ከዚህ በላይ የተደነገገው እንተጠበቀ ሆኖ፡-

የቢሮ ኃላፊው፡-

C) Institute suit on prosecutors and attorneys at all levels who committed fault transgressing this proclamation and other exisiting laws as properly before prosecutors administration as well as discipline council of attorneys, and debate thereon;

D) Respond to appeal cases to be submited to regular courts on decisions made by the office regarding desciplinary decisions on prosecutors and attorneys; debate for same presented in courts;

E) Work in integration with concerned bodies enabling to the proper implementation of service delivery, grievance handling and ethical rules and regulations of the institution by all professionals and support staff after the proper understanding;

F) Closely monitor the implementation of change programs in the bureau and the effectiveness of the regional justice reform program.

15) Without prejudice to the provisions of this proclamation above,

The head of the Office shall:

ሀ) የወንጀልና ፍትሐብሔር-ነክ ክሶችን አስመልክቶ በተሻሻለው የክልሉ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 237/2008 ዓ.ም እና በሌሎች ሕጎች ለኮሚሽነሩ ተሰጥተው የነበሩትን ሥልጣንና ተግባራት ተረክቦ በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በግብር (ታክስ) ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ በክልሉ ገቢዎች ባለሥልጣን የሚተዳደረው ዐቃቤ-ሕግ አጣርቶ የክስ አይቀርብም ውሳኔ የሰጠባቸውን ወይም የወንጀል ክስ መሥርቶ ባካሄዳቸው ክርክሮች ያስገኛቸውን ውጤቶች ይከልሳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ክርክሩ በተዋረድ የተካሄደባቸውን መዛግብት አስቀርቦ የተፈጸመ ስህተት ቢኖር ጉዳዩ እንደገና እንዲንቀሳቀስና ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲታረም ያደርጋል፤

ሐ) ረቂቅ የዓቃብያነ-ሕግ መተዳደሪያ ደንብን አዘጋጅቶ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) የየደረጃውን ዐቃብያነ-ሕግ በሚወጣው ደንብ መሠረት ይሾማል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

A) Take over the powers and duties assigned to the Commissioner by the amended Establishment of the Regional Ethics and Anti-Corruption Commission Proclamation No. 237/2016 and other laws regarding criminal and civil cases;

B) Revise the no-proceeding decisions given or the results of criminal charges litigated by public prosecutors administered under the regional revenue authority regarding crimes committed on tax; and as may be as necessary when an error is found, by causing files to be presented that are decided at different levels, it may cause the case to be seen again and the mistake be corrected after the cases are pleaded before an authorized court;

C) Present the draft public prosecutors' administration regulation prepared by the regional public prosecutors' administration council to the council of regional government and implement same upon approval;

D) Appoint, administer and dismiss the public prosecutors at different level in accordance with the regulation to be issued;

ሠ) በምክትል ቢሮ ኃላፊና በሌሎች ዐቃብያነ-ሕግ የተሰጡ ውሳኔዎችን ይሽራል፣ ይለውጣል፣ ያሻሽላል ወይም ጉዳዩ እንዲጣራ ወይም ውሳኔውን በሰጠው አካል እንደገና እንዲታይ ያደርጋል፤

16) ከዚህ በላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቢሮ ኃላፊው የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ሆኖ ያገለግላል።

## 29. የሰላምና ጸጥታ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ውስጥ ሰላምን ለማስጠበቅ ይሠራል፣ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

2) አግባብ ካላቸው የክልልና የፌደራል መንግሥቱ አካላት ጋር በመተባበር በየትኛውም የክልሉ አካባቢ የሚኖሩ ዜጎችና ማኅበረ-ሰቦች ተገቢውን ሕጋዊ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

3) የክልሉ ሕዝብ ሰላም፣ ደህንነትና ነፃነት እንዲከበር የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤

4) የሰላም እሴቶችን በመገንባትና በማስፋፋት ረገድ በኅብረተ-ሰቡ ውስጥ ተከታታይነት ያላቸው የግንዛቤና የንቅናቄ ተግባራት እንዲከናወኑ ያደርጋል፤



E) Revoke, alter, amend the decisions given by deputy bureau head and other prosecutors or refer for re-examination or revision by the one that has given the decision;

16) Without prejudice to the above provisions, the head of the bureau shall serve as the Attorney General of the Region.

## 29. Bureau of Peace and Security

Without prejudice to existing or subsequent provisions of other laws, the regional Bureau of Peace and Security shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1) Work for the protection of peace in the region follow up and ensure the maintenance of law thereof;

2) Cause the accessibility of proper laga protection of citizens and communities residin in any place of the region in collaboration wit pertinent bodies of the region and federal state;

3) Devise mechanisms enabling to obseve peac security and freedom of the regional people;

4) Cause the execution of continuous awarene and mobilization activities to be carried out i the society regarding to building and promotir peace values;

5) በክልሉ ውስጥ በሚኖሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ወይም የተለያየ ሃይማኖትም ሆነ እምነት ተከታዮች በሆኑ ማኅበረ-ሰቦች መካከል እርስ በርስ የመከባበርና የመቻቻል ባህል እንዲዳብር ለማድረግ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት፣ የባህልና የሃይማኖት ተቋማት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

6) ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስና በሕዝቡም ሆነ በመንግሥት ጥቅም ላይ በስውር ጉዳት ለማድረስ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችንና ድርጅቶችን በመከታተል ተግባራቸውን ቀድሞ ያመክናል፣ ተገቢውን ጥበቃ ያደርጋል፤

7) በክልሉ ውስጥ በተዋቀሩ የበታች አስተዳደር እርከኖችም ሆነ ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚነሱ አለመግባባቶችና ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ ሊፈቱ የሚችሉባቸውን ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥራል፤

8) ለአካባቢያዊ ግጭቶች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ይለያል፣ ኅብረተ-ሰቡ ወደ ግጭትና አለመረጋጋት እንዳያመራ የቅድመ-መከላከል እርምጃዎችን ይወስዳል፣ በሌሎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

9) በጥናት ላይ ተደግፎ የግጭት መንስኤዎችን ይለያል፣ ግጭት ሲከሰት ባህላዊና ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲፈታ ይጥራል፣ በግጭቱ ውስጥ የተካፈሉ ተዋናዮችን የማረጋጋትና የማስተዳደር ተግባራትን ያከናውናል፤



5) Work with pertinent government bodies, cultural and religious institutions to develop the culture of respect and tolerance among individuals and groups or different religion as well as faith followers residing in the region;

6) Paralyze in advance, by pursueing them, the activities of those individuals, groups and organizations that try to disband the constitutional order by force and thereby jeopardize public and government interests in a clandestine manner, and provide the necessary protection thereof;

7) Create favorable conditions for the pacific settlement of misunderstandings and conflicts arising between the bottom administration levels in the region as well as neighbouring regions;

8) Identify causes of local conflicts through study; take prevention measures in order not the society lead into conflicts and instability, and cause the measure to be taken by others;

9) Identify causes of conflicts having been supported by studies; strive to resolve same upon its emergence using traditional and modern conflict resolution mechanisms, and carry out stabilization of actors and conflict management;

10) ወንጀል እንዳይፈጸም አስቀድሞ በመከላከል የክልሉን ሕዝብ ሰላምና ደህንነት ያስጠብቃል፣ ኅብረተ-ሰቡ በወንጀል መከላከል ተግባር ንቁ ተሳታፊ እንዲሆንና የራሱን ሰላምና ደህንነት እንዲጠብቅ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

11) የሕግ ታራሚዎች የኅብረተ-ሰቡን ሰላምና ደህንነት በማያውክ ሁኔታ መጠበቃቸውን፣ በአግባቡ ታርመው ወደ ማኅበራዊ ኑሮ መመለሳቸውንና ብቁ ዜጎች ሆነው መውጣታቸውን ይከታተላል፣ ለዚህም ተገቢ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ያረጋግጣል፤

12) በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሕግ አስከባሪ አባላትና አመራሮች በሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አያያዝና አጠባበቅም ሆነ በሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች ዙሪያ አቅማቸውን በመገንባት የሕዝብ አገልጋይነት ሚናቸው እንዲዳብር ያደርጋል፤

13) የክልሉ ፖሊስና ሌሎች የጸጥታ ተቋማት የሚመሩባቸውን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ስትራቴጅዎችና የአሠራር ሥርዓቶች ያመነጫል፤ ተልዕኳቸውን ለመፈጸም የሚያስፈልጋቸውን የሰው ኃይል፣ የትጥቅና የሌሎች አጋዥ ቁሣቁሶች ፍላጎት ያጠናል፣ በጥናቱ መሠረትም ግብአቶቹ በወቅቱ እንዲሟሉ ያደርጋል፤



10) See to it that the peace and security of the region's people is safeguarded through an early prevention of the commission of crimes; and encourage the community so that the latter may participate in crime-prevention activities and hence-force take care of its own peace and security as well as extend the appropriate support thereof

11) Follow up that prisoners of law are confined in such away as not to disrupt the peace and security of the community, are properly corrected and rehabilitated back to social life and released from detention as competent citizens as well as ensure that appropriate measures are taken to such an end.

12) Cause the enhancement of the role of law enforcement members and their leaders, belonging to the region, in becoming public servants by building their capacity in the areas of handling and protection of human and democratic rights as well as regarding the constitution.

13) Initiate policies, laws, strategies and working procedures in which the regional police and other security institutions are to be directed; study their needs of necessary manpower, armament and other supporting materials with the view to accomplishing their mission and cause its fulfillment thereof as per the studies;

14) ጉዳዩ በሚመለከተው የፌደራል መንግሥት አካል ውክልና ሲሰጠው በሕግ አግባብ ተደራጅተው በግል የደህንነት ጥበቃ ሥራ መሠማራት ለሚፈልጉ አካላት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፤

15) ለክልሉ ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት በሕግ የተሰጠው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የፌደራሉ መንግሥት አካል እውቅና በክልሉ ውስጥ የግል ደህንነት መጠበቂያ የጦር መሣሪያ ለሚያስፈልጋቸው ተቋማትና ግለሰቦች የማስታጠቅ፣ ፈቃድ የመስጠትና የማደስ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ይቆጣጠራል፣ ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውሮችን ይከታተላል፤

16) በግጭት መከላከል፣ አያያዝም ሆነ አፈታትና በሕዝብ ደህንነት አጠባበቅ ረገድ አግባብ ካላቸው የፌደራሉ መንግሥትና ሌሎች አካላት ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፣ ችግሮችን በጋራ መድረኮች ይፈታል።

## 30. የቱሪዝም ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ቱሪዝም ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-



14) Issue and renew license, supervise and delete same when it has been given deligation by the federal government in respect of parties who want to engage in private security guard organized by law;

15) Without prejudice to the responsibilities given to the regional militia office, supervise the undertaking activities of arming, licensing and renewing same in respect of those institutions and private persons qualifying to carry guns for self defense purposes in the region _in the recognition of federal pertinent body; and follow up illegal transfer of firearms;

16) Maintain working relationships with the appropriate federal government and other bodies in matters of involiving in conflict prevention, management and resolution as well as public safety and security observance and thereby resolve problems in common forums.

## 30. Bureau of Tourism

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Tourism shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) የቱሪዝም ልማት ቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕግ ማዕቀፎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከክልሉ እና ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ-ግብር ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
2) የክልሉን መልካም ገጽታና የቱሪዝም ሀብቶች፣ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር በማስተዋወቅ ቱሪዝምን ያስፋፋል፤
3) የክልሉን የቱሪዝም፣ የማኅበረሰብ አቀፍና የኢኮ-ቱሪዝም መስህቦች በመለየት እና በማስተዋወቅ ለቱሪዝም ገበያ አመቺ ሆነው እንዲደራጁና እንዲለሙ ያደርጋል፤
4) የቱሪዝም የገበያ ጥናት በማካሄድ ባለ ድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በመለየት፣ የቱሪዝም ገበያ በመፈለግ እና የገበያ ትስስር በመፍጠር የዘርፉን የኢኮኖሚ ድርሻ ያሳድጋል፤
5) አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦች እንዲለሙ በማድረግ፣ ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎች በመሠረተ ልማት እንዲጎለብቱ እና የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት በዓይነትና በመጠን እንዲያድጉ በማድረግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
6) የክልሉን ቅርሶች ደረጃ በመለየት እና አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦች እንዲለሙ ነባሮችን በመሠረተ ልማት በማጎልበት መስፈርቱን ሲያሟሉ በዓለም አቀፍ ቅርስነት እንዲመዘገቡ ይሠራል፣ የቅርስ ጥገናና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ያደርጋል፣ የሙያ ድጋፍም ይሰጣል፤



1) Initiate policies, strategies and legal frameworks to ensure the sustainability of tourism development; prepare a detailed program for its implementation in line with the regional and national development directions, and applies same upon approval;
2) Promote tourism by promoting the region's good image and tourism resources at home and abroad;
3) Cause the region's tourism, community-based and eco-tourism attractions to be organized and developed for the tourism market through identifying and promoting them;
4) Increase the economic role of the sector by researching the tourism market on activities stakeholders conduct, searching for tourism market and creating market ties;
5) Cause same to be competitive by making new tourism attractions be developed, existing tourism destinations be strengthend through infrastructures and product and service of tourism be grown in type and amount;
6) Work for the registration of the regional heritages as the world heritage when they meet the standard through identifying the region's heritage status and todevelop new tourism attractions, strengthening the existing one with infrastructure; cause the provision of heritage maintainance and care, and also render professional support;

7) የቱሪዝም የገበያ ጥናት በማካሄድ የገበያ ምልክት (የብራንዲንግ) ሥራዎችን በማቀናጀት ይመራል፤

8) በክልሉ ውስጥ የስፖርት፣ የኢግዚቢሽንና የስብሰባ ቱሪዝም እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

9) የክልሉን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ መስህብ ሀብቶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁ እና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

10) ዘርፉ በቴክኖሎጅ፣ በጥናትና ምርምር እንዲደገፍ እና ለክልሉ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዎጽኦ እንዲያድግ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተልል፤

11) በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮች፣ ፓርኮች፣ ጥብቅ ስፍራዎች እና የማኅበረሰብ አቀፍ ጥብቅ ስፍራዎች እንዲሁም የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎች ለኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያመነጩ ያደርጋል፤

12) በክልሉ በሚገኙ ፓርኮችና ሌሎች ጥብቅ ስፍራዎች፣ የቱሪዝም መዳረሻና የቱሪዝም አገልግሎትን በተመለከተ ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በትብብር ይሠራል፤

13) በቱሪዝም ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻጸም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

14) የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደረጃዎች ይወስናል፤



7) Lead by integrating market trade mark (branding) works through conducting tourism market research;

8) Casuse the promotion of sports, exihibition and coference tourism in the region;

9) Make the regional natural and man-made resources to be studied, preserved and utilized being comfortable for tourism;

10) The sector will be supported by technology research and its contribution to the region's economy; monitors its performance;

11) Enable national parks in the region, parks, protected areas and community-wide protected areas as well as wildlife preserved places generate economic benefits for the community;

12) Work in collaboration with the environmental protection Authority regarding parks and other protected areas found in the region, tourism destination and tourism services;

13) Set up a system that will increase the private sector participation in tourism sector development; creata conducive environment for performance;

14) Determim standards of tourism service provider institutions;

15) በክልሉ ውስጥ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ለሚሰማሩ አካላት የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

16) በክልሉ ውስጥ በቱሪዝም ዘርፍ ለሚሰማሩ የባለ ኮከብ ሆቴሎችና መሰል አገልግሎቶች የፕሮጀክት ሐሳቦችን በመገምገም የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለሚመለከተው ያስተላልፋል፤

17) ከቱሪዝም ተዋናዮች ማለትም በመንግሥት፣ በማኅበረሰብ፣ በማኅበር እና በግል የተሰማሩ አካላት ጥራት ያለው የቱሪዝም ምርትና አገልግሎት ማቅረብ ይቻል ዘንድ ከአጋር አካላት ጋር ትብብር በመፍጠር ይሠራል፤

18) የክልል የቱሪዝም ምክር ቤት የሚጠበቅበትን ሚና እንዲያበረክት ምቹ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

19) የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶችን ይለያል፣ ይመዘግባል፣ የሕገ ወጥ ቅርሶችን ዝውውር ለመከላከልና የተዘረፉትን ለማስመለስ ከተለያዩ ባለ ድርሻና አጋር አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፣

20) የቅርሶች ይዞታ ሕጋዊ ወሰን፣ የይዞታ ማረጋገጫና የአስተዳደር እቅድ እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት በትብብር ይሠራል፣

21) በክልሉ በሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎች እና መስህብ ስፍራዎች የጎብኝዎችን የመግቢያና የሌሎች አገልግሎት ክፍያዎችን የክፍያ ተመን በጥናት ይወስናል፤



15) Provide service qualification assurance for parties to be engaged in Hotel and Tourism sector in the region;

16) Evaluate project proposals of parties to be engaged in star hotels and similar services in the tourism sector in the region and transfer same to concerned body to get investment license;

17) Work in collaboration with stakeholders for the provision of quality tourism product and service from parties engaged in tourism actor such as in government, community, association and private;

18) Facilitate conducive environment so that the Regional Tourism Council contribute its role expected therefrom;

19) Identify and record tangible and intangible heritages and work with various stakeholders and partners to prevent the illegal heritage transfer and return of looted heritages;

20) Work incollaboration with concerned bodies so that heritage holdings have legal boundaries holding certificate and administration plan;

21) Determin the fee of tourist entrances and other services at tourist destinations and attraction found in the region;

22) በክልሉ ውስጥ ቱሪዝም-ነክ የሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

23) ከቱሪዝም ሚኒስቴርና ከክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት በክልላዊና አገራዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ውስጥ ለማዋሐድ ሥርዓት ይዘረጋል።

## 31. የሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳዮች ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1) በክልሉ ውስጥ የሴቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች መብቶችንና ጥቅሞችን ለማስከበር የሚረዱ የፖሊሲ ሐሣቦችን ያመነጫል፣ የማስፈጸሚያ ስልቶችን በመቀየስ ለተግባራዊነታቸው አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤

2) በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን መብቶች ዙሪያ የተደነገጉ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች በክልሉ ተፈጻሚ ስለመሆናቸው ክትትል ያደርጋል፤

3) ብሔራዊ የሴቶች፣ የማኅበራዊ ጥበቃ እና የሕፃናት ፖሊሲዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ ጥረቶችን ያስተባብራል፤

22) Collect, compile, analyse and disseminate tourism-related information within the region;

23) Setup a system to integrate a satellite account in the regional and national economic account system in collaboration with the Ministry of Tourism and the Regional Planning and Development Bureau;

## 31. Bureau of Women, Children and Social Affairs

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Women, Children and Social Affairs shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Initiate policy proposals with the view to enforcing the right and interest of women, children, elders and disables in the region; make the necessary follow up by devising implementation strategies;

2) Oversee the implementation of international and continental conventions on the rights of women, children, disables and elders in the region;

3) Coordinate efforts taken place in the region to implement the national women's, social protection and children's policy;

4) በክልሉ መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ሪፖርቶች የሥርዓተ-ጾታን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንንና የአካል ጉዳተኞችን ጉዳዮች ለማካተት የሚያስችላቸውን ስልት በመንደፍ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ በሒደቱም የሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንንና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፤

5) በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚቃጡ መድልኦዎችንና የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጥናት በመለየት እነዚሁ የሚወገዱባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ያመነጫል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

6) ልዩ ፍላጎት ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ በማኅበረ-ሰቡ ዘንድ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመቀየር የሚያስችሉ ቀጣይነት ያላቸው የግንዛቤና የንቅናቄ ሥራዎችን ያከናውናል፤

7) በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ሕገ-ወጥ ዝውውርና ፍልሰት፣ የጉልበት ብዝበዛ እና ሌሎች የመብት ጥሰቶችን ለመከላከል የሚረዱ የአሠራር ሥርዓቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይዘረጋል፤



4) Make the necessary followup and support by devising a sytem enabling policies, laws development programs, projects and report prepared by the regional state include gender children, elders and disables; ensure the participation and benefit of women, children elders and disables in the process;

5) Identify discrimination and harmful traditiona practices committed on women, children, elder and disables through study, and initiat recommendations onhow to avoid same an monitor the implementation;

6) Carry out continuous awareness an mobilization activities enabling to change th bad attitude attached to the society regardin sections of the society having special needs;

7) Devise procedural sytems in collaboration wit concerned bodies to prevent child trafficking migration, labour exploitation and othe violations of right;

8) ሴቶች ለዘመናት በበታችነትና በልዩነት ከመታየታቸው የተነሣ የደረሰባቸውን ተፅዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ረገድ ተሳትፏቸውን ለማሳደግ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ መስጠት ስለሚቻልበት ሁኔታ ለክልሉ መንግሥት ሐሳብ ያቀርባል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

9) ሴቶችና አካል ጉዳተኞች በክልሉ ውስጥ በሚሰጡ የሥራ ቅጥር፣ የሥልጠናና የደረጃ እድገት እድሎችም ሆነ እነዚህኑ ለማስፈጸም በሚደራጁ የተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በሚገባ ስለ መወከላቸው ይከታተላል፤

10) የተለያዩ የክልሉ መንግሥት አካላት ሴቶችን በውሳኔ ሰጭነት ቦታዎች በመመደቡ ረገድ በቂ ትኩረት ስለ መስጠታቸው ይከታተላል፣ ብቃት ያላቸውን ሴቶች እየለየ በየደረጃው ለሚገኙ ወሳኝ አካላት ያቀርባል፤

11) ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንንና የአካል ጉዳተኞችን እንደየ ችግሮቻቸው ዓይነት በነጻ ፍላጎታቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸውና ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሙሉ አቅማቸው እንዲሳተፉና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደርጋል፣ በየተቋቋሙበት አግባብ ተግባራቸውን እየተወጡ ስለመሆኑም በቅርብ ይከታተላል፤



8) Submit a recommendation to the regional government on how to give special attention and support to increase their participation regarding economic, social and political affairs in consideration of the women's impact of inferiority and discrimination for centuries; followup the implementation thereof;

9) Monitor the representations of women and disables in employment, training and promotion opportunities in the region as well as in various committees organized to implement same;

10) Monitor the allocation of womenin decision-making positions by various regional government bodies and submit by identifying qualified women to decisive bodies found at all levels;

11) Provide an overall support to women, children, elders and disables to fight for their rights and interests being organized in their free will accordingly the type of their respective problems and to fully participate and benfit in building democratic system, good governance and development activities, and monitors their performance in their perspective establishment;

12) በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ እንዲጠኑ ያደርጋል፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ በዚሁ ዓላማ ላይ ተመሥርተው ለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

13) ሥርዓተ-ጾታን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከተለያዩ የማኅበረ-ሰብ ተቋማትና ከራሳቸው ከሴቶች ማኅበራት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤

14) የጾታ እኩልነትን ለማስፈን፣ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ለማጎልበትና ኅብረተ-ሰቡ በሴቶች ላይ ያለውን የተሳሳተ ግንዛቤ ለመቀየር የሚረዱ ሥልጠናዎችንና ዓውደ-ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ውጤቶቻቸውንም ይገመግማል፤

15) አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን እና ሌሎች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ፍትሐዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚረዱ ሥልጠናዎችንና ዓውደ-ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ውጤቶቻቸውንም ይገመግማል፤



12) Conduct and cause to be conducted studies improve the living conditions of women lower living standard, children, elders, disab and other vulnerable groups to socio-econon problems; implement programs and projects formulating same; and provide the necessa support to organizations operating for tl purpose;

13) Work in collaboration with non governmen organizations, various community institutic and their own women's assocations regardi gender issues;

14) Conduct trainings and workshops helpi tosecure gender equality, strengthen womer participations in various activities and char society's misconceptions about wom evaluate their results;

15) Conduct trainings and workshops helping secure fair, social and economic benefits elders, disables and other socio-econor vulnerable groups;

16) ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንንና አካል ጉዳተኞችን ለሚያግዙና ለክልሉ ዘላቂ ልማት አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ሀብት ያፈላልጋል፤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆንም ድጋፉ የነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች ሕይወት ለማሻሻል ስለመዋሉና ውጤታማ ስለመሆኑ ይከታተላል፤

17) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተሰብና የሕፃናት ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግና የጋብቻ ሥርዓትን ለመንከባከብ የወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

18) ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን እና ሌሎች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ማዕከል አድርገው የሚሠሩ የተለያዩ አካላትን የተግባር ዕቅድና አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖራቸው ያስተባብራል፣ የተጠያቂነት አሠራር ይዘረጋል፤

19) የሀገሪቱ ማኅበራዊ ጉዳይ ፖሊሲዎችና ሕጎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

20) ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በሥራ ላይ ያሉትን የአረጋዊያንና የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ፣ ተሐድሶና እንክብካቤ ማዕከላት ያስተዳድራል፣ በክልሉ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች እንደ ተገቢነታቸው መሰል ማዕከላትና ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤



16) Findout resources helping for the implementation of programs and projects that support women, children, elders and disables and contribute to the sustainable development of the region; followup the utilization of the support to improve the lives of these sections of the society with concerned bodies;

17) Implement policies designed to protect safety of family and children and to care marriage system in collaboration with pertinent bodies;

18) Followup and control action plan and implementation of different bodies working at the center of women, children, elders, disables and other vulnerable groups; coordinate them to have integrated procedure, and set up procedure of accountablity;

19) Enforce the implementation of the country's social affairs policies and laws in the region;

20) The details being determined by a regulation to be issued for the implementation of this proclamation, administer the existing support and rehabilitation centers for the elders and disables, and cause the establishment of similar centers and organizations in different parts of the region;

21) የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች ይወገዱ ዘንድ የክልሉን ኅብረተ-ሰብ ሁለንተናዊ ጥረት ያስተባብራል፤ እንደሴተኛ አዳሪነትና ጎዳና ተዳዳሪነት ባሉ አስከፊ ችግሮች ላይ የወደቁ ወገኖችን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፤

22) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ምክንያት ለከፋ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን የድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ አማራጭ የድጋፍ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተጋላጮችን ይለያል፣ ድጋፉን ያስተባብራል፤

23) በገጠርም ሆነ በከተማ የሴፍትኔት ፕሮግራም ውስጥ በቀጥታ ተጠቃሚ የሆኑ የኅብረተ-ሰብ ክፍሎችን መረጃ ይለያል፣ ያደራጃል፤ ለተጠቃሚነታቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

24) የሴቶች፣ ሕፃናት እና ሌሎች የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የኅብረተ-ሰብ ክፍሎችን የሚመለከት ዘመናዊ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፤

25) የማኅበራዊ ጥበቃ ተቋማትን ያቋቁማል፣ ውጤታማ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

26) የዜግነት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት እንዲዘረጋና የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተ-ሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል።



21) Coordinate the overall efforts of the region t eliminate harms of social life; establish an organizes victims of serious problems such a prostitution and street living;

22) In collaboration with pertinent bodies formulate alternative support strategies to th provision of necessary support for groups of th society exposed for serious social and economi problems due to natural and artificial disasters identify vulnerables and coordinate the support

23) Identify and organize data of direct safety-ne program users in rural as wellas urban; work i integration with concerned bodies for the beneficiary;

24) Devise a modern information administratio system regarding women, children and oth social and economic vulnerable groups of th society;

25) Establish social protection institutions, suppo and monitor for their success;

26) Work in collaboration with concerned bodi so that civic volunteer service system to l established and social and economical problen vulnerable groups of the society to be benefite

27) የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የሕፃናት መልካም አስተዳደግና ስብዕና ግንባታ፣ ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና ተሐድሶ ላይ ለወላጆችና አሳዳጊዎች ተገቢውን ግንዛቤና ሥልጠና በመስጠት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፤

28) በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡና ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት ጉዲፈቻን ጨምሮ በሀገር ውስጥ ባሉ አማራጭ ድጋፍና እንክብካቤ ዘዴዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## 32. የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ውስጥ የወጣቶችን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚረዱ የፖሊሲ ሐሳቦችን ያመነጫል፣ የማስፈጸሚያ ስልቶችን በመቀየስ ለተግባራዊነታቸው አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤
2) ወጣቶችን በተመለከተ የወጡ ሀገር-አቀፍ ፖሊሲዎች፣ ፓኬጆችና ስትራቴጂዎች በአግባቡ ስርፀው በክልሉ ውስጥ እንዲፈጸሙ ይሠራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
3) ወጣቶች በክልሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው ስለመሆኑ በቅርብ ይከታተላል፤



27) Work focusing on giving the appropriate awareness and training to parents and guardians on children's well-behave and personality building, support, care and rehabilitation by coordinating concerned bodies;

28) Devise and implement local alternative support and care systems including adoption to benefit vulnerables due to various reasons and orphaned children.

## 32. Bureau of Youths and Sport

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Youths and Sport shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Generate policy ideas to protect the rights and interest of the youths in the region, make the necessary monitoring by formulating implementation strategies;
2) Work, monitor coordinate and supervise the implementation of national policies, packages and strategies issued regarding youths;
3) Closely monitor opportunities for youths to actively participate in the region's political, economical and social activities;

4) ወጣቶች እንደየ ችግሮቻቸው አይነት በነጻ ፍላጎታቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸውና ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሙሉ አቅማቸው እንዲሳተፉና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደርጋል፣ በየተቋቋሙበት አግባብ ተግባራቸውን እየተወጡ ስለመሆኑም በቅርብ ይከታተላል፤

5) ወጣቶችን ማዕከል አድርገው የሚሠሩ የተለያዩ አካላትን የተግባር ዕቅድና አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖራቸው ያስተባብራል፤

6) የክልሉ ወጣቶች በክልሉም ሆነ በሀገሪቱ የሚገኙትን ብሔሮች፣ ብሔረ-ሰቦችና ሕዝቦች ባህልና ታሪክ ለማወቅ የሚያስችሏቸውን የማኅበረ-ሰብ ንቅናቄና የተሳትፎ መድረኮች ያዘጋጃል፣ ሥራውን ያስተባብራል፤

7) የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በክልሉ እንዲስፋፋና ባህል እንዲሆን ያስተባብራል፣ የበጎ ፈቃድ ማኅበራትን ያደራጃል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ተግባሩንም ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

8) በወጣቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዙሪያ የላቀ አበርክቶ ላደረጉና ልዩ የፈጠራና ክህሎት ላላቸው ወጣቶች፣ ግለሰቦች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ አደረጃጀቶች፣ ስፖርትን በማስፋፋትና በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ የስፖርት ግለሰቦች፣ ማኅበረ-ሰቦች፣ ሲቪክ ማኅበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ግልፅ መመሪያ በማዘጋጀት የማበረታቻ ሽልማቶችን ይሰጣል፣ ለበለጠ ሥራ ያነሣሣል፤



4) Provide an overall support to youths to fig their rights and interests being organiz their free will accordingly the type of respective problems and to fully participat benfit in building democratic system, governance and development activities, monitors their performance in their perspe establishment;

5) Followup and control action plan implementation of different bodies worki the center of youths;

6) Organize and coordinate social mobili and participation forums enabling the re youths to know the culture and histo nation, nationalities and pople of the regi well as the country;

7) Coordinate the expansion and acculturati youths' volunteer servicein the region; or and support volunteer service associations and control the activity;

8) Render reinforcements by preparing directive to youths, individuals, volu organizations those have made sign contribution regarding the over all partici and beneficiary of the youths and have s creativity and skill, sport indiv communities, civic associations, govern and non-governmental organizations thos made significant contribution regardin promotion and strengthment of sport;

9) ወጣቶችን ከማኅበራዊ ጠንቆች፣ ከአደንዛዥ እጾችና አሉታዊ መጤ ባህሎች እንዲሁም ሌሎች ጤንነታቸውን ከሚጎዱ ነገሮች በመከላከል በሥነ-ምግባር የታነጹ፣ ንቁና ሀገር ወዳድ ዜጎች እንዲሆኑ እና ብሔራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል፤

10) የወጣቶችን ስብዕና መገንቢያ ተቋማት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና የሥልጠና ማዕከላት ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፣ በየደረጃው እንዲገነቡና የተገነቡ የስፖርት ሥልጠና ማዕከላትን በየደረጃው የሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች በባለቤትነት በመያዝ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፣ የሕግ ከለላ እንዲኖራቸው ድጋፍ ይሰጣል፤

11) የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የወጣቶች ልማት ፈንድ ያቋቁማል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፤



9) Work in collaboration with concerned bodies to make youths wel-behaved, active and lover of country and give national service by protecting them from social harm, drugs and negative foreign cultures as well as other harmful things for their life; monitor its implementation;

10) Prepare standards for youths' personality building institutions, sport frequent places and training centers; cause the construction of same at all levels and the provision of service of already constructed ones being hold in sense of ownership by administrative levels found at all levels; provide support same have legal protection;

11) Establish, coordinates and direct the Youths' Development Fund to ensure the over all participation and beneficiary of the youth;

12) የክልሉን ወጣት እና ስፖርት-ነክ መሠረታዊ መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሠራጫል፣ ወጣት-ተኮር የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ የሥልጠና ስታንዳርዶችንና የአቅም ግንባታ ፓኬጆችን እያዘጋጀ ከትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ለወጣቶችና ለስፖርት ልማት ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

13) ስፖርትን በተመለከተ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች በክልሉ ነዋሪ ኅብረተ-ሰብ ዘንድ በሚገባ ሠርፀው በክልሉ ውስጥ እንዲተገበሩ ይሠራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

14) የክልሉን ስፖርት እድገት እውን የሚያደርጉ ረቂቅ ሕጎችንና ደንቦችን በማዘጋጀት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቦ ያስጸድቃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

15) በክልሉ ውስጥ የተለያዩ ስፖርቶች ሊስፋፉ የሚችሉባቸውን አካባቢዎች ወይም ለስፖርቱ እድገት የሚውሉትን የተፈጥሮ ጸጋዎች በመለየት በልዩ ሁኔታ የስፖርት ፕሮጀክቶችንና ተቋማትን ያቋቁማል፣ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

16) ኅብረተ-ሰብ አቀፍ የስፖርት ተሳትፎ ፕሮግራም ወይም ፓኬጅ በማዘጋጀት ማኅበረ-ሰቡ በሚኖርበት፣ በሚሠራበትም ሆነ በሚማርበት አካባቢ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፤

12) Gather, organize and analyze the regional youths and sport-related basic data, and disseminate same to concerning bodies; conduct youth-oriented research activities; cause the provision of training for youths and sports development by prearing training standards and capacity building packages in collaboration with educational institutions, and monitor its implementation;

13) Work for the application of policies and strategies issued by national level in the region being properly indoctrinated; followup, coordinate and monitor thereof;

14) Cause the approval of draft laws and regulations preparing same enabling to realize the regional sport development by submitting them to the concerned bodies of the issue; followup and control their implementation;

15) Establish sport projects, in the region, in special way that different sports to be expanded in different places or by identifying natural resources those could be used for development of the sport; and make the necessary support thereby;

16) Make the society to participate in sport activities and be beneficial from them, where the society live, work as well as learn, by preparing societal-wide sport participation program;

17) የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን በመጠቀም የስፖርት ገቢዎችን ያሰባስባል፣ የስፖርት ማኅበራት የሚሰበስቡት ገቢ ለዓላማቸው ማስፈጸሚያ ብቻ መዋሉን ለማረጋገጥ ሒሳባቸውን ይመረምራል፣ ይቆጣጠራል፤

18) በክልሉ ውስጥ በስፖርት ኢንቨስትመንት ለሚሠማሩ ባለሀብቶች ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ በስታንዳርዱ መሠረት የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይኼው መከበሩን ይቆጣጠራል፤

19) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በወጣት ስብዕና ማዕከላት፣ በታላላቅ ሆቴሎች፣ ሪል-ስቴቶች፣ ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ በጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ በፋብሪካዎችና የኢንዱስትሪ መንደሮች እና በመሳሰሉት ሌሎች አካባቢዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መሥሪያ ቦታዎች ተካተው መሠራታቸውን ወይም መገንባታቸውን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

20) ስፖርት ለሥራ ፈጠራ የሚኖረውን ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት በሽያጭና በዝውውር አማካኝነት በክለቦች የታቀፉ ስፖርተኞች የጉልበት ብዝበዛ እንዳይደርስባቸው ይከታተላል፣ የስፖርት ሥልጠና ማዕከላትን እና ስብዕና ልማት ማዕከላትን ከፍተው የራሳቸውን ሥራ ለሚያከናውኑ አካላት ተገቢውን ሙያዊ ፈቃድ ይሰጣል፣ ድጋፍም ያደርጋል፤

21) በክልሉ ውስጥ በየደረጃው ለሚቋቋሙ የስፖርት ማኅበራት ስታንዳርድ ያወጣል፣ በስታንዳርዱ መሠረት ያቋቁማል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ የሥራ ውል ይይዛል፣ ፕሮግራሞቻቸውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤



17) Collect sport revenues by using different revenue collection systems; audit the account of sport societies that the collected money is utilized only for the achievement of their objective, and control therefrom;

18) Prepare standards for affluents to be engaged in sport investment in the region; give professional license in line with the standard; and control the observance of same;

19) In consultation with pertinent bodies, follow up the construction of physical exercising places in youths personality centers, big resorts, real-estates, hospitals, schools, condominiums, factories, industry villages and soforth areas, and give support therefrom;

20) Follow up that sport persons those are embraced under clubs due to sale and transfer, by considering the importance of sport for job creation, do not exposed for labour exploitation; give the necessary professional support and give license for those parties operating their work opening their own sport training and personality development centers;

21) Issue standards for sport societies to be established at each level in the region; establish them based on the standard; give license, make work contract, coordinate their programs, and control themfrom;

22) በክልሉ ውስጥ በየደረጃው የስፖርት ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

23) የክልሉን ስፖርታዊ ውድድሮች ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ውድድሮችን ያካሂዳል፣ ውድድር እንዲያዘጋጁም ፈቃድ ይሰጣል፤

24) በክልሉ ውስጥ ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲዳብርና በጨዋታ ወቅት የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈጽመው በተገኙ ስፖርተኞችም ሆነ ደጋፊዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃዎችን ይወስዳል ወይም እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

25) ክልላዊ የስፖርት ውድድሮችን በሚመለከት በስፖርት ማኅበራትና በሌሎች አካላት መካከል የሚነሡ አለመግባባቶችን መርምሮ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፤

26) በክልሉ ውስጥ ባህላዊ ስፖርቶች የበለጠ እንዲታወቁ ይሠራል፣ የራሳቸው ሕግና ደንብ እንዲወጣላቸው ይሠራል፣ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

27) በክልሉ ውስጥ ከኅብረተ-ሰቡ አቅም ጋር የተገናዘቡ የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች የሚመረቱበትንና ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር በድጋፍ መልክ የሚገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤



22) Cause the establishment and strengthenment of sport councils at all levels in the region;

23) Prepare standards of the regional sport competitions; conduct competitions in collaboration with concerning bodies of the issue; give them license to organize completion;

24) Take and cause to be taken legal measures on sport persons as well as supporters who committed ethical defect during play in order to sport wel-behaviour to be developed in the region;

25) Give administrational decision through investigating misunderstandings created between sport societies and other parties concerning regional sport competitions;

26) Work for cultural sports in the region to be more known and their own law and regulation to have been made; encourage to be improved and grow; and give support thereof;

27) Facilitate conditions in which sport wear and materials in line with the capacity of regional society to be produced, and to be gained from in the country as well as outside the country through support;

28) ከክልሉ ሚዲያ ኮርፖሬሽንና ሌሎች የሚዲያ ተቋማት ጋር በመተባበር ለኅብረተ-ሰቡ ጠቃሚ የሆኑ የአካል ብቃት እንቅስቃሴና የወጣቶችና የስፖርት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች በሬዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን እንዲሁም በሌሎች የሚዲያ አማራጮች እንዲተላለፉ በትጋት ይሠራል፤

29) ከክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ጋር በመተባበር ከስፖርቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጤና-ነክ ተግባራት በእቅድ አካቶ ያከናውናል፡፡

## 33. የፕላንና ልማት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1) የክልላዊ መንግሥቱን ረቂቅ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ከአቻ የፌደራል መንግሥት ማዕቀፎች ጋር በማገናዘብና በማስተሳሰር ይነድፋል፣ ያበለጽጋል፣ ያስጸድቃል፤

2) የኢኮኖሚና የልማት ፖሊሲ ትንተናና ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ስትራቴጂካዊ የሶሾ-ኢኮኖሚ ጉዳዮችን ይለያል፣ በትንተናና ጥናቶች በሚገኙ ውጤቶች መሠረት የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያካሒዳል፤

3) የክልሉን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶችን ለማዘጋጀት የሚረዱ የኢኮኖሚ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፣ አጠቃላይ የኢኮኖሚያዊና የማኅበራዊ ሁኔታ መለኪያዎችንና መመዘኛዎችን ያዘጋጃል፤

28) Work hard for the transmission of physical exercise and youths and sport awareness creation lessons useful to the society through radio as well as television and other media alternatives in collaboration with the Regional Media Corporation and other media institutions;

29) Implement health-related activities those have relation with sport by incorporating them with its plan in collaboration with the Regional Health Bureau.

## 33. Bureau of Planning and Development

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Planning and Development shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Design, enrich, and approve the draft policies and strategies of the regional government in consideration and conjugation with equivalent federal government frameworks;

2) Conduct economy and development policy analysis and studies; identify strategic socio-economic issues; submit policy recommendations to the concerned body based on the result of the analysis and research, and conduct policy research;

3) Conduct economic research helping to develop the short, medium and long term development plans of the region; prepare general economic and social condition standards and measurements;

4) በሀገሪቱ የልማት ስትራቴጂዎች ላይ የተመሠረተና በክልሉ መንግሥት የሚፈጸም የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

5) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን ሕዝብ ፍትሐዊ የመልማትና የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

6) ለክልሉ መንግሥት አካላት በተለይም ለክልሉ ከፍተኛ አስፈጻሚና አስተዳደራዊ አካል የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶች ዝግጅት፣ ክትትል፣ አተገባበርና ግምገማ ማዕከል ሆኖ ይሠራል፤

7) የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ተቋማትን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችን አተገባበር፣ ውጤታማነትና ጥረት በላቀ ሙያዊ ኃላፊነትና በሀቀኝነት ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ለዚህም ያመቸው ዘንድ በስትራቴጂካዊ የትኩረት መሥኮች ከፋፍሎ የየዘርፉን ዕቅዶችና ሪፖርቶች ይቀበላል፣ ለበላይ አመራሩ የሚቀርበውን የተጠቃለለ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

8) በክትትልና በግምገማው የተገኙትን ውጤቶች በጥልቀት በመመርመርና በመተንተን ከተገማች እንድምታዎቻቸው ጋር ለበላይ አመራሩ እናአግባብ ላላቸው ፈጻሚ አካላት በወቅቱ ያስተላልፋል፤



4) Prepare short, medium and long term development plans based on the country's development strategies and that shall be implemented by the regional government;

5) In collaboration with concerned bodies, devise a system helping to ensure the equitable development and development beneficiary of the regional people, and monitor its implementation;

6) Work as being the center of preparation of short, medium and long term development and good governance, monitoring, implementation and evaluation for organs of the regional government_ especially for the top executive and administrative body of the region;

7) Monitor and evaluate the implementation, effectiveness and effort of short, medium and long term plans of national regional government institutions with greater professionalism and honesty; receive plans and reports for each sector by deviding into strategic focus areas for this purpose, and prepare a comprehensive report submitted to the top leaders;

8) Timely transfer to the top leaders and pertinent executive bodies by deeply examining and analyzing results found from the monitoring and evaluation with their estimated implications;

) የእርስ በርስ ግንኙነቶችን በማጠናከር በክልሉ ውስጥ የተደራጁትን ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ተቋማት፣ የግል ተቋማትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሰፊው የሚያሳትፉበት ተጠያቂነትን ያሰፈነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተል፤

0) የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱን ለማስተዋወቅና በክልሉ መንግሥታዊ ተቋማት ዘንድ ለማስረፅ የሚያግዙ የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን ያከናውናል፣ ሥርዓቱን በማላመድና በማስተግበር ረገድ የየደረጃው ፈጻሚ አካላት ክህሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚገነባበትን ስልት ይቀይሳል፤

1) የልማት ዕቅድን ለማሳካት እንዲሁም የመንግሥትን የማስፈጸም አቅም ለማጠናከርና ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር የሥርዓት ማሻሻያ ጥናት ያካሄዳል፣ በጥናቱ ላይ ተመሥርቶ የተቋማትን አደረጃጀት በተመለከተ የውሳኔ ሐሳብ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

2) በመንግሥት በጀት፣ በመንግሥት ዋስትና ብድር እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ የበጀት ምንጮች እንዲከናወኑ የታቀዱ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአዋጭነትና አስፈላጊነት ግምገማ በማከናወን ወጤቱን ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤

3) የልማት ፕላን ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት ሥርዓት በመዘርጋት በሥራ ላይ እዲውል ያደርጋል፣ የቴክኒካል ምክር አገልግሎትና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤



9) Establish a comprehensive monitoring and evaluation system that ensured accountability in which various governmental institutions, private institutions and non-governmental organizations are fully involved in the region strengthening interpersonal relations, and followup its implemetation;

10) Perform public relations activities assisting the promotion monitoring and evaluation system and indoctrinate in the regional government institutions; devise a system in which the skill of executive organs at all levels to be built from time to time regrading the adaption and implementation of the system;

11) Conduct a study of system improvement to achieve development plan as well as to strengthen the execution capacity of the government and for the creation of sustainable institutional capacity; on the basis of the study submit recommendation regarding to organization of institutions to concerned body;

12) Inform the result of feasibility and relevance evaluation on development projects planned to be implemented in the government budget, government-guaranteed loans and other similar budget sources to concerned body;

13) Cause the implementation by devising a system of development plan programs and projects preparation; provide technical advice service and capacity building support;

14) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት አካላት ጋር በመመካከር በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶች ውስጥ ሊንፀባረቁ የሚገባቸውና በክልሉ መንግሥት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑና እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይገመግማል፤

15) በክልሉ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶችን ለማሳካት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

16) አለም ዓቀፍና ሀገራዊ የስታትስቲክስና የጂኦ-ስፓሻል መረጃ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ መረጃዎች በክልሉ እንዲሰበሰቡ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤

17) የክልሉን የተፈጥሮ ሀብት፣ የጂኦ-ስፓሻል፣ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ የምርት፣ የአገልግሎትና የመሳሰሉትን መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፤

18) ለክልሉ ዘላቂ ልማትና ዕድገት ፋይዳ ያላቸው የቅየሳ፣ የካርታና የጂኦግራፊ ጥናት ሥራዎችን ያከናውናል፣ እንዲከናወን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤

19) የተቋማትን የመረጃ የመሰብሰብ ተግባራት ይቆጣጠራል፣ የአሠራር ስታንዳርድ እና የናሙና ዘዴዎችን ያጸድቃል፣ የትክክለኛነት ማረጋገጫ ይሰጣል፤



14) Cause the study, preparation and evaluate, in consultation with concerned bodies of the regional government, projects that could be reflected in short, medium and long term development plans and could be implemented by the regional government;

15) Monitor, evaluate and prepare report on the implementation of projects carried out to achieve the short, medium and long term development plans in the region;

16) Establish a system of data collection in the region on the basis of international and national statistics and geo-spacial information standards; monitor and enforce same;

17) Collect andcompile data of natural resources, geo-spacial, agriculture, industry, production, services and so on of the region, and disseminate same to concerning bodies;

18) Conduct surveying, mapping and geographical research activities having importantance of sustainable development and growth of the region;

19) Supervise the data collection activities of institutions, approve procedural standards and sampling methods, and render assurance of accyracy;

20) በክልሉ ውስጥ በወሰን ተለይተው ለሚቋቋሙ የከተማና የገጠር አስተዳደራዊ እርከኖች የአስተዳደር ወሰን ይሠራል፣ መለያ ኮዶችን በመስጠት የካርታ ሥራ ይሠራል፣ የሥነ-ሕዝብ መረጃዎችን ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎችም ያሰራጫል፤

21) በክልሉ ውስጥ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጃዎችን ያመነጫል፣ ለተጠቃሚዎችም ያሰራጫል፤

22) የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን አስመልክቶ ጥናትና ምርምር ያካሔዳል፣ መረጃዎችን ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎችም ያሰራጫል፤

23) መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በብሔራዊው የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አፈጻጸም ረገድ የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ከነዚሁ አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል፤

24) በክልሉ መንግሥት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡትን የመደበኛና የካፒታል በጀት ጥያቄዎች ከክልሉ የልማት እቅድ ጋር ተገናዝበው እዲዘጋጁና ፍትሐዊ የሆነ የበጀት ቀመር እንዲኖር የሚያስችል መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ከአስተያየት ጋር ለገንዘብ ቢሮ ያስተላልፋል፤



20) Make administrative boundaries for urban and rural administrative levels to be established being identified in boundary in the region; make mappings by giving identification codes, organize demographic data, and distribute them to users;

21) Generate macro-economic datain the region, and disseminate same to users;

22) Conduct research concerning demographic issues, organize the data, and disseminate same to users;

23) Coordinate and direct the activities of both governmental and non-governmental organizations regarding the implementation of the National Population policy; work in integration with these bodies;

24) Collect information enabling to have fair budget formula and in line with the regional development plan of the regular and capital budget requests being prepared by the regional government bodies; transfer same with suggestion to bureau of finance;

25) ከሀገር ውስጥና ከውጭ በመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ሆነ በበይነ መንግሥታት የሚቀርቡ የልማት ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ከክልሉ የልማት እቅድ ጋር ተመጋጋቢ እዲሆኑ ያደርጋል፤ እንዲሁም የሥራ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን በመሰብሰብ ከአጠቃላይ የክልሉ ሪፖርት ጋር በማገናዘብ ጥቅል ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

26) የአየር ንብረት ለውጥን የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፡፡

## 34. የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የክልሉን ሲቪል ሰርቪስ በተመለከተ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችንና ደንቦችን ያመነጫል፣ የደመወዝ ስኬል፣ ልዩ ልዩ አበሎችንና ጥቅማ ጥቅሞችን አጥንቶ ያስወስናል፣ በተለያዩ የሰው ሀብት ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር ያካሄዳል፤

2) ለክልሉ ሕዝብ የሚሰጠውን የመንግሥት አገልግሎት አስመልክቶ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችንና ደንቦችን ያመነጫል፣ ያሻሽላል፣ ከክልል ጀምሮ እስከ ታችኛው ተዋረድ በሚገኙ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ ችግሮችን በጥናት ይለያል፤



25) Make development programs and projects submitted by local and foreign non-governmental organizations as well asinter-governmental comply with the regional development plan, as well as submit comprehensive report to concerned body by preparing their performance report in consideration with the regional consolidated report;

26) Coordinate, support and follow up concerning bodies to build resilient green economy to climate change;

## 34. Commission of Civil Service and Human Resource Development

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Comission of Civil Service and Human Resource Development shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Generate policies, laws and regulations regarding to the civil service of the region cause the determination of salary scale, various allowances and benefits through study, and conduct research on various issues of human resource;

2) Generate and revise policies, laws and regulations regarding the provision of public service given regional people; make service delivery support and monitorfor institutions found from region to the lower level; identify problems by research;

3) ለክልሉ ዘላቂ እድገት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የተቋማት ሪፎርም ሥራዎችን በማጥናት ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ ተቋማት በአሠራር እንዲጠነክሩና በተገቢ መንገድ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ያግዛል፣ ከተቋማት በተናጠል የሚቀርቡ አስፈላጊ የሥራ መደቦችን ይፈቅዳል፤

4) የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ያካሂዳል፣ ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

5) በክልሉ የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ዘመናዊና የተሟላ ሰብአዊ ሀብት አመራርና ልማት አጠቃቀም ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ በተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

6) በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ላይ የተለያዩ የለውጥ ፕሮግራሞችን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ ያካሂዳል፣ ይኼው በሥራ ላይ እንዲውል የክልሉን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያማክራል፤

7) የክልሉን መንግሥት ሠራተኞች የሥራ አፈጻጸም ውጤት መመዘኛ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ስለመዋሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

8) የክልሉን የመንግሥት ሠራተኞች የሰው ሀብት ስምሪት መመሪያ ያወጣል፣ ሕግንና መርህን ተከትሎ እንዲፈጸም ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ ሕግንና መርኅን የጣሰ ስምሪት ሲፈጸም የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤



3) Submit a recommendation to the concerned body by studying institutional reform works enabling for contribution to sustainable development to the region, followup upon approval, support, assist institutions to be strengthened in procedure and implement works in the appropriate way, permit necessary positions individually submitted from institutions;

4) Conduct job evaluation and grading study, monitor and support for its implementation;

5) Cause the establishment ofa system of modern and complete human resource management and development utilization in the civil service institutions of the region; followup and support for its application;

6) Establish procedural system enabling for the effectiveness of implementations of various change programs in the civil service institutions of the region; monitor, evaluate and support same; advise the regional government offices same to be implemented;

7) Prepare the performance evaluation of the regional government employees; support and monitor for their implementation upon approval;

8) Issue a directive of the regional civil servants human resource operation, support and followup for its implementation to be on basis of law and principle, take corrective measures in case of implementation violating law and principle;

9) በክልሉ ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞች የሚያቀርቡትን ቅሬታ ከሥራ መታገድ፣ በከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ከሕግ ውጭ በደመወዝ መያዝ ወይም መቋረጥ፣ በሥራ ምክንያት በደረሰ ጉዳት ሳቢያ የመብት መጓደል ሲያጋጥም ወይም የሥራ መልቀቂያና የአገልግሎት ማስረጃን አስመልክቶ በተወሰዱ እርምጃዎች የሚቀርቡለትን የይግባኝ ጉዳዮች በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አማካኝነት መርምሮና አጣርቶ በፍሬ ነገር ደረጃ ውሳኔ ይሰጣል፤

10) የክልሉን የመንግሥት ሠራተኞች ዝርዝር መረጃ መዝግቦ ይይዛል፣ ስታስቲካዊ መረጃዎችን ያጠናቅራል፣ ውጤታማና ብቃት ያለው ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፤

11) በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ዘመናዊ የተሟላ የሰብአዊ ሀብት አመራር እንዲኖር በክልሉ የመንግሥት ሠራተኞች ላይ የሚታዩ የአቅም ክፍተቶችን በጥናት በመለየት በትምህርትና ሥልጠና ለማብቃት እና የሰው ሀብት ልማቱን በተማከለ መልኩ ለመምራት የሚያስችል ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ በተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ አሠራሩ ተጥሶ ሲገኝ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል።

## 35. የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለሥልጣን

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ አካባቢና ደን ጥበቃ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦



9) Render decision through its administrative court at the substance level of appeal cases on taken actions regarding suspending from work, illegal holding or termination of salary due to rigorous disciplinary punishment, right violation due to employment injury or leaving of work and service by public servants in the region;

10) Keep detailed data of the regional civil servants by recording same; compile statistical data, and establish an effective and qualified modern information system;

11) Cause the establishment of a system enabling to qualify with education and training and centrally lead the human resource development through identifying capacity gaps seen on the regional civil servants for the presence of modern complete human resource management in the regional civil sevice, followup its application, support, take the necessary corrective measure when the procedure is violated;

## 35. Authority of Environment and Forest Protection

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Authority of Environment and Forest shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) በክልሉም ሆነ በፌደራሉ መንግሥት የተደነገጉ የአካባቢ ደህንነት ዓላማዎች እና በሀገሪቱ የአካባቢ ፖሊሲ ውስጥ የሰፈሩት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል፤

2) አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች፣ ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላትና ከነዋሪው ሕዝብ ጋር በመመካከር ረቂቅ የአካባቢ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ሕጎችን፣ መርሃ-ግብሮችንና ስልቶችን ያዘጋጃል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፤

3) ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን (የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችን) ያስተባብራል፣ ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ በሆኑ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ላይ የተፅዕኖዎች ማቃለያ እና መቋቋሚያ ስልቶችን ተቋማት በዕቅዳቸው ውስጥ አካተው እንዲተገበሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ የሚቀንሱትን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን ያረጋግጣል፤

4) የአካባቢን ደህንነት ለመጠበቅ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የተጎዳ ወይም የተጐሳቆለ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነቶችን ይፈጥራል፣ እንደ አስፈላጊነቱ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ይሰጣል፤

5) የአካባቢ ብክለትና ብክነትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ደረጃውን የጠበቀ ቤተ-ሙከራ ወይም ላባራቶሪ በማቋቋም የወጡ የአካባቢ ደረጃዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

6) በመንግሥትም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች፣በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስልቶች፣ ሕጎችና መርሃ-ግብሮች ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማለማካሄድ የሚያስችል ክልል አቀፍ ሥርዓት ይዘረጋል፤



1) Coordinate activities enabling to ensure the achievement of environmental safety objectives provided by the regional as well as the regional government and basic principles set in the local policy of the country

2) Prepare, evaluate and supervise draft environmental policy enforcement laws, programs and strategies in consultation with the relevant authorities, other stakeholders and the resident population;

3) Coordinate resilientgreen economy to climate change (green development works); monitor and support for the implementation of impact mitigation and resistance systems by including in their plan on sector offices vulnerable to climate change, and ensure their reduction of the heating gas emission;

4) Create contacts with pertinentoffices to protect the environment well-being or to rehabilitate the damaged or degraded environment in any way, and provide capacity building support as needed;

5) Cause for theimplementation of local standards issued to prevent and control environmental pollution and wastage by establishing a standardized laboratory;

6) Devise a regional-wide system enabling to conduct environmental impact assessment on on public as well as private projects, social and economoic development policies, strategies, laws and programs;

7) በአካባቢ ጉዳይ ላይ የተሠማሩ በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ዉጭ ያሉ ግሪን ኢንተርፕራይዞች፣ ክበባት፣ የአካባቢ ተቆርቋሪ ማኅበራት እና በአካባቢ ጉዳይ የሚሠሩ ማኅበራት ስለአካባቢ ደኅንነት ጉዳይ እና በአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ሥልጠና ይሰጣል፣ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፣ የተሻለ ተሞክሮ ሲኖር ይቀምራል፣ ያሰፋል፤ ለጥሩ ተሞክሮዎች እውቅና ይሰጣል፣ ያበረታታል፤

8) አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ በረሃማነትን ለመከላከልና የድርቅን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ መፍትሔዎችን ያዘጋጃል፣ ለአተገባበራቸውም ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

9) ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን እና ማኅበረ-ሰቡን በማስተባበር የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥርዓትን በከተሞች ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም የሚችሉ አረንጓዴ ቴክኖሎጅዎችን እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ ያበረታታል፣ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤

10) በልማት እቅዶችና በኢንቨስትመንት መርሃ-ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጪነት ማስያ ቀመሮችንና የስሌት ሥርዓትን አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ እንደ ሁኔታውም በጥቅም ላይ የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፤



7) Provide training to green enterprises engage on environemetal damage in and outsid schools, clubs, environmental concernin associations and associations to be engaged in environmental issue to aware abou environmental well-being issue and climat change impacts; followup and support formulate and expand when there is bes experience, recognize and encourage goo experiences;

8) Conduct studies to prevent desertification an reduce negative impact of drought in th regionin collaboration with pertinent offices prepare solutions and creat favorable condition for their implementation;

9) Monitor and support for the implementation o integrated solid waste management and disposa systems in urbans through coordinatin concerned bodies and the society, cause for th implementation green technologies to recycl wastages, encourage and establish contr system;

10) Prepare or cause for the preparatio ofenvironmental feasibility calculating formula and calculation system included developme plans and investment programs in collaboratio with pertinent bodies, and monitor the application as if necessary;

11) ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀምና ልምድን፣ የአካባቢ ጉስቁልናን ወይም ብክለትን ለመከላከል በሚያስችሉ የመግቻ እርምጃዎች ወይም የማበረታቻ ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር ሐሣብ ያቀርባል፤

12) አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትንና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

13) የአካባቢና የደን ጥበቃ ምርምሮችን ያስተባብራል፣ ያበረታታል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ራሱ ያካሂዳል፤

14) አግባብ ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በገጠርም ሆነ በከተማ አስተዳደር ሥልጣን ሥር ወደሚገኝ ማናቸውም መሬት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ ይገባል፤ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ነገር ይፈትሻል፣ ናሙናዎችን ይወስዳል፤

15) የክልሉን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለመንግሥትም ሆነ ለሕዝብ እንዲደርስ ወይም እንዲሰራጭ ያደርጋል፤

11) Suggest in consultation with pertinent offices onlack of sustainable natural resources use and practices, environmental degradation or pollution preventive systems or use of encouragement systems;

12) Devise a system expeditingfor the collection, organization and use of environmental data in collaboration with pertinent bodies, cause for its application;

13) Coordinate and encourage environment and forest protection researches, and conduct by itself as needed;

14) Enter into any land, compound or other place under the jurisdiction of rural and city administration to ensure the observance of environmental protection obligations on basis ofpertinent legal provisions; inspect anything necessary for carrying out its responsibility, and take any sample;

15) Make the addressability or distribution of the regional environment condition by preparing same periodically to the government as well as to people;

16) መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ ትምህርት መርሃ-ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርቱን ይሰጣል፣ አካባቢያዊ ጉዳዮችን በመደበኛ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ለማካተት አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ትብብር ያደርጋል፤

17) የአካባቢ ጥበቃ የድርጊት እቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ዝግጅት ያበረታታል ወይም ያግዛል፣ ለድርጊት ዕቅዶቹና ፕሮጀክቶቹ ማስፈጸሚያ የሚውሉ እገዛዎችን ያፈላልጋል፤

18) ሀገር አቀፍ የአካባቢ ደኅንነት፣ የደንና የዱር እንስሳት ጥበቃና አጠቃቀም ሕጎችን በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ያወጣል፣ በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

19) የአካባቢ አያያዝንና ጥበቃን ተቀዳሚ ዓላማው በማድረግ ለሚሠራ ለማናቸውም ድርጅት ወይም ግለሰብ ምክር እንዲሁም የሚቻል ሲሆንና የአካባቢ ምክር ቤቱ ሲስማማበት የፋይናንስ ወይም የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፤

20) አግባብ ያላቸው መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተጣሉባቸውን ኃላፊነቶች በሚወጡበት ሁኔታ ላይ ተገቢውን የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣ እንደ አስፈላጊነቱም እርምት ሊወሰድባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ለክልሉ መንግሥት የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፤

16) Promote non-formal environmental education programs, provide the education, and make collaboration with pertinent offices to incorporate environmental issues into the formal curriculum;

17) Encourage or assist in the preparation of environmental protection action plans and projects; seek supports for the implementation of the action plans and projects;

18) Issue directivesof national-wide environmental security, forest and wildlife protection and use to make applicable in the region, and cause for their applicability;

19) Render advice or if possible and upon the agreement of the environmental council finance or technical support to any organization or individual working as the primary objective of environmental handling and protection;

20) Provide the appropriate advice to pertinent offices on carrying out their responsibilities by this proclamation and other laws, and submita recommendation to the Regional Government on matters that need to be corrected as necessary;

21) አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር በሳይንሳዊና በአካባቢያዊ መርሆች ላይ የተመሠረቱና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የአካባቢ ደረጃዎች ያዘጋጃል፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት መረጃ ይሰጣል፣ ያሰራጫል፤

22) በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሠራሽ አደጋዎችን ለመቋቋም ስለሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች የክልሉን መንግሥት ያማክራል፤

23) የክልሉን የአካባቢ ጥበቃና የደን ይዞታ በሚመለከቱ ጉዳዮች አግባብ ላላቸው አካላት ሥልጠናና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

24) የአካባቢና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ለሚያማክሩ እና ለሚያጠኑ ድርጅቶችና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

25) በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የደን ሀብት ውጤቶች ዝውውር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

26) የክልሉ ኅብረተ-ሰብ በዱር እንስሳት አያያዝ፣ ልማትና አጠቃቀም ረገድ በቂ ግንዛቤ ሊያገኝ የሚችልበትን ስልት ይቀይሳል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ብርቅየ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤



21) Prepare local standards based on scientific and environmental principles and applicable in consultation with pertinent offices, provide and disseminate information to concerned bodies of the issue;

22) Consult the regional government on precautionary measures to resist natural as well as man-made emergencies happened on an environment;

23) Provide training and professional support to appropriate bodies in matters relating to the environmental protection and forest holding of the region;

24) Prepare, issue, renew, and cancel certificate of competence for organizations and professionals those consult and study environmental and social issues;

25) Monitor and supervise the transfer of forest resource products taken place in the region;

26) Devise a system on how the regional people get sufficient awareness about the wildlife handling, development and use; cause for its application, facilitate conditions so that rear wildlife species get special protection and care;

27) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ወንዞችንና ሐይቆችን የሚያዋስኑ አካባቢዎችን እንዲሁም ውኃ (እርጥበት) አዘል ረግረጋማ መሬቶችን (ስፍራዎችን) ደኅንነት ይጠብቃል፣ ይንከባከባል፣ መረጃ ያሰባስባል፤ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

28) የብዝኀ-ሕይወት፣ የሥርዓተ ምኅዳሮችንና የሌሎች የአካባቢ ሀብቶችን አያያዝ፣ አጠቃቀምና ልማት ለማሻሻል የሚያግዙ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በጥናቱ ለተለዩ ችግሮች የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የመፍትሔ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

29) የአካባቢ ሀብቶችን አስመልክቶ የዋጋ ትመና ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በትመናው ውጤት መሠረትም ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ሲነደፉ በአዋጪነት ስሌታቸው ውስጥ የአካባቢ ሀብቶች ዋጋ እንዲካተት ያደርጋል፣ በትግበራ ወቅት ለሚደርሰው ማናቸውም የአካባቢ ሀብት ጥፋት በሀብት ትመናው መሠረት ተመጣጣኝ ካሣ እንዲከፈል ያደርጋል፤

30) የአካባቢ ደኅንነትን ለማስከበር ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ተግባር በተሰጣቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ተግባር ላይ የምርመራና የክትትል ሥራዎችን ያከናውናል፣ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡት ላይ ደግሞ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤



27) protect, care and collect data of areas as well as water (wetland) swampy lands (places) bordering rivers and lakes security found in the region in collaboration with pertinent bodies; cause problems faced therein to be solved;

28) Conduct studies helping to improve the handling, utilization and development of biodiversity, ecosystems and other environmental resources; and take short, medium and long term solutions to specific problems identified by the study;

29) Conduct cost valuationstudies regarding environmental resources,cause for the incorporation of the environmental resources value in their feasibility formula on basis of the valuation result when programs and projects are designed, and cause for the adequate compensation payment accordingly the asset valuation for any damage happened during the implementation on the environmental resource;

30) Carry out investigation and monitoring works onactivities of governmental and non-governmental institutions authorized and responsible to observe environmental security, and take appropriate measure on against those who do not carry out their responsibilities;

31) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማዎችን ለማካሄድ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ሪፖርቶችን በመመርመር የእርምትና የማስተካከያ አስተያየቶችን ይሰጣል፣ ተስተካክለው በቀረቡ ሰነዶች አንፃር የይሁንታ ፈቃድ ይሰጣል፤

32) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ የደን አይነቶችን፣ ፓርኮችና ሌሎች ጥብቅ ስፍራዎች ያጠናል፣ ይከልላል፣ ይመዘግባል፣ ያስተዳድራል፣ ያለማል፤ በሌሎች እንዲለሙ ያደርጋል፤

33) የክልሉ የደን ሀብት ትርጉም ያለዉ ኢኮኖሚያዊና ስነ-ምኅዳራዊ ጥቅም እንዲሰጥ ለማስቻል የደን ሀብት አጠቃቀም እና አያያዝ እቅድ ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

34) የክልሉን የደን ሀብት መረጃ በዘመናዊ መንገድ ያደራጃል፣ ይተነትናል፤

35) የደን ምርት ዉጤት አምራች ኢንዱስትሪዎችን ሁለንተናዊ አቅም ለማሳደግ የምክር አገልግሎት እና የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፣ የድጋፍ ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፤

36) በክልሉ ዉስጥ የሚካሄዱ የደን ጥበቃ አጠቃቀም እና አስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፤

37) የደን ምርት ዉጤቶች የእሴት ሰንሰለት እና የገበያ ትስስር ጥናት ያካሂዳል፣ የጥናት ዉጤቱን ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ያደርጋል፤



31) Develop strategies for conducting environmental impact assessments, render corrective suggestuions through reviewing reports, and render acceptance license on parallel to correctly submitted documents;

32) In collaboration with the concerned parties, it shall study, delimit, register, administer and developdifferent forest types, parks and other preserved places found in the region in collaboration with concerned bodies of the issue, and case same to be developed by others;

33) Prepare and cause for the preparation of forest resource use and handling plan enabling the region's forest resource provide significant economic and ecological benefits;

34) Organize and analyze the forest resources of the region in a modern way;

35) Provide consulting and technical support to develop the overall capacity of the forest products manufacturing industries, and develop supportive frameworks;

36) Coordinate on top of forest protection use and administrative works taken place in the region;

37) Conduct value chain and marketing ties for forest product results, deliver the results to consumers;

38) የክልሉ የደን ሀብት ለአየር ንብረት ለዉጥ የሚያበረክተዉን አስተዋፅኦ በተመለከተ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የጥናት ዉጤቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ያስተባብራል፤

39) የግሉ ዘርፍ በደን ጥበቃ አጠቃቀም እና ግብይት ሥራዎች ላይ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲኖረዉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።

## 36. የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የክልሉ መንግሥት ዋነኛ የኢንፎርሜሽን ምንጭ በመሆን ያገለግላል፣መንግሥታዊ መልእክቶችን ያሰራጫል፣ በክልላዊ ጉዳዮች ላይ ደግሞ የክልሉን መንግሥት ውሳኔዎችና አቋሞች ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤

2) በክልሉ መንግሥት አቋሞችና አሠራሮች ላይ የሚሰነዘሩ ሒሶችንና የሚሰጡ አስተያየቶችን በንቃት ይከታተላል፣ የሕዝብ አስተያየቶችን በማሰባሰብና በመተንተን ውጤቱን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት አካላት ያሰራጫል፤

3) የሀገር ውስጥና የውጭ መገናኛ ብዙኃን የዕለት-ተዕለት ዘገባዎችን ቅኝት ያካሂዳል፤

4) በክልሉ መንግሥት ፖሊሲዎችና በተለያዩ ክልላዊም ሆነ ሀገር-አቀፍ ጉዳዮች ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ ለማስያዝና ግልጽነትን ለማስፈን ሕዝባዊ የውይይትና የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፤



38) Conduct studies on the contribution of the region's forest resourcefor climate change, and coordinate the implementation of research findings;

39) Support and monitor the private sector to have significant contribution on forest protection useand marketing works.

## 36. Bureau of Government Communication

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Government Communication shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1) Serve as the main source of information for the regional government, disseminate governmental messages and publicize decisions and stands of the regional government on regional matters;

2) Actively follow criticisms and suggestions givenon the regional government stands and procedures, disseminate the result to the concerned regional government bodiesby collecting and analyzing the public opinion;

3) Conduct a survey of local and foreign media day-to-day reports;

4) Organize and coordinate public discussion and dialogue forums to appropriately aware and secure transparency on the regional state policies and different regional as well as nation-wide issues;

5) በክልሉ መንግሥት ስም የመረጃ መረብ ሥራዎችን ያከናውናል፣ የድረ-ገፅ ልውውጦችን ያካሂዳል፤
6) ለክልሉ፣ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች በየወቅቱ መግለጫዎችን ይሰጣል፤
7) ክልሉ በውጭው ዓለም ዘንድ ሊታወቅበት በሚገባው ትክክለኛ ገጽታ እንዲወከል ሰፋፊ መረጃዎችን ይሰጣል፣ በክልሉ ላይ የሚነዙ የተሳሳቱ መረጃዎችን ይከላከላል፣ ይመክታል፤
8) በክልሉ የበላይ አመራር የሚካሄዱ ፕሬስ ኮንፍረንሶችና የሚሰጡ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ቢኖሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ መገናኛ ብዙኃንን ይጠራል፣ ጥያቄዎቻቸውን በቅደም ተከተል እንዲያቀርቡና ምላሽ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
9) የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ ሹማምንት ኅብረተ-ሰቡን በአካል አግኝተው እንዲያነጋግሩና የተለያዩ ተቋማትን በመጎብኘት የሥራ ክንውኖችንም ሆነ ኩነቶችን በውል ለመገንዘብ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤
10) በክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር ውክልና ሲሰጠው የክልሉ ተቋማት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊዎችን ሹመት ይሰጣል፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ከኃላፊነት ያነሳል።



5) Carry out networking activities on behalf of the regional government, and conduct web-site exchanges;
6) Provide periodic statements to the region, local and foreign journalists;
7) Provide extensive information to represent the region in the right image the region should be known for by the outside world, prevent and defend misinformation spread on the region;
8) Facilitate conditions if there are press conferences and press release given by the regional top leaders, call formass media, make them present their questions in order and get response for;
9) Create favorable conditions for top officials of the regional government to talk the public meeting in person and better understand the implementations and eventsby visiting various institutions;
10) Render appointments to the regional institutions' public relations heads when it is given delegation by the head of government, and remove from head position when necessary;

## 37. ስለ ሌሎች የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት

1) የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ሌሎች አስፈጻሚ አካላትና ተቋማት በየተቋቋሙባቸው ሕጎች በተደነገገው መሠረት ባሉበት ሁኔታ ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

2) የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት በቀጥታ ለብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል፡-

ሀ) የሥነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ጽሕፈት ቤት፤

ለ) የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፤

ሐ) የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አገልግሎት፤

መ) የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን፤

ሠ) የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር

ረ) ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት፡፡

3) የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ግብርና ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን፤

ለ) የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፤

ሐ) የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ጽሕፈት ቤት፤

መ)የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ባለሥልጣን፤

ሠ) የግብርና ጥራትና ደኅንነት ባለሥልጣን፤

4) የሚከተሉትአስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የፖሊስ ኮሚሽን፤

ለ) የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን፤

ሐ) የሚሊሻ ጽሕፈት ቤት፡፡



## 37. About Other Executive Bodies of the Regional State

1) Other Executive Bodies and institutions of the National Regional State shall continue to function in accordance with the provisions of their respective established laws;

2) The following Executive Bodies shall be directly accountable to the Head of Government of the National Region:

A) The Office of Ethics and Anti-corruption;

B) The Management Institute;

C) The Vital Events Registration Service;

D) The Science and Technology Commission;

E) The Administration of Governmental Development Enterprises;

F) The Grand Renaissance Dam Coordinating Office.

3)The following Executive Bodies shall be accountable to the Regional Agriculture Bureau:

A) The Disaster Prevention and Food Security Commission;

B) The Agricultural Research Institute;

C) The Office of Livestock and Fish Resource Development;

D) The Cooperative Expansion Authority;

E) The Agricultural Quality and Safety Authority;

4) The following Executive Bodies shall be accountable to the Regional Bureau of Peace and Security:

A) The Police Commission;

B) The Correction Centers Commission;

C) The Militia Office;

5) የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ቱሪዝም ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የቅርስ ጥበቃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት፤

ለ) የሙሉዓለም ባህል ማዕከል፤

ሐ) የአማራ ሕዝብ ዝክረ-ታሪክ ማዕከል፡፡

6) የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ተጠሪነት ለክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ይሆናል፡፡

7) የከተሞች ፕላን ኢንስቲቲዩት ተጠሪነት ለክልሉ ከተሞችና መሠረተ-ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

8) የውኃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነት ለውኃና ኢነርጂ ቢሮ ይሆናል፤

9) የቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ተጠሪነት ለክልሉ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

10) የመንገዶች አስተዳደር ተጠሪነት ለክልሉ መንገድ ቢሮ ይሆናል፤

11) የሕግ ኢንስቲትዩት ተጠሪነት ለክልሉ ፍትሕ ቢሮ ይሆናል፤

12) የሕብረተ-ሰብ ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት ተጠሪነት ለክልሉ ጤና ቢሮ ይሆናል፤

13) የጣና ሐይቅና ሌሎች የውሃ አካላት አስተዳደር ተጠሪነት ለአካባቢና ደን ጥበቃ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

5) The following Executive Bodies shall be accountable to the Regional Tourism Bureau:

A) The Heritage Protection Development Fund Office;

B) The Mulualem Cultural Center;

C) The Amhara People History-Memorial Center;

6) The Industrial Parks Development Corporation shall be accountable to the Regional Industry and Investment Bureau;

7) The Urban Planning Institute shall be accountable to the Regional Urbans and Infrastructure Bureau;

8) The Water Development Fund Office shall be accountable to Water and Energy Bureau;

9) The Kobo Girana Valley Development shall be accountable to the Regional Irrigation and Lowland Areas Development Bureau;

10) The Road Administration shall be accountable to the Regional Road Bureau;

11) The Legal Institute shall be accountable to the Regional Bureau of Justice;

12) The Public Health Research Institute shall be accountable to the Regional Health Bureau;

13) Lake Tana and Other Water Bodies Administration shall be accountable to the Environment and Forest Conservation Authority;

## 38. አስፈጻሚ አካላት በየደረጃው የሚቋቋሙ ስለ መሆናቸው

1) በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋሙና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት የሆኑ አስፈጻሚ አካላት በክልሉ ውስጥ እንዳስፈላጊነቱ በየዞኑ መምሪያዎቻቸውን ወይም ተጠሪ ጽሕፈት ቤቶቻቸውን ሊያደራጁ ይችላሉ፡፡

2) በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የብሔረ-ሰብና የወረዳ አስተዳደሮች በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግሥት በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ቀጣይነት ላለው ልማትና ለተፋጠነ አገልግሎት አስፈላጊ ሆነው የሚያገኟቸውን የአስፈጻሚ አካላት መምሪያዎችና ጽሕፈት ቤቶች የማቋቋም መብት ይኖራቸዋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር በተደነገገው መሠረት የብሔረ-ሰብና የወረዳ አስተዳደሮች መንግሥታዊ ተቋማትን ለማደራጀት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚያቀርቡትን ጥያቄ መሠረት በማድረግ አግባብ ያላቸው የክልሉ አስፈጻሚ አካላት ተገቢውን ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡



## 38. Establishement of Executive Bodies at All Levels

1) The executive bodies established in accordance with this proclamation and which are members of the regional administrative council may organize their departments in each zone or their respective offices in the region as necessary;

2) The national and woreda administrations found in the region shall have the right to establish executive bodies departments and offices which they found necessary for sustainable development and accelerated service in accordance with the powers vested in them by the revised regional constitution;

3) Pertinent executive bodies of the region shall be responsible for providing appropriate support to the requests made by the national and woreda administrations for the establishment of public institutionsin accordance with the provisions of sub-article (2) of this article.

# ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 39. አስፈጻሚ አካላትን ስለ ማደራጀት

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የክልሉን አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት አስመልክቶ በጥናት ላይ የተመሠረቱ ለውጦችን ከማድረግ ባሻገር አዳዲስ ተቋማትን የመመሥረት፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውን የመወሰን፣ አንደኛውን ከሌላው ጋር የማዋሐድ፣ እንዲሁም በሕግ መሠረት ሥልጣንና ተግባራቸውን የማንሣት ሥራዎችን እንዲያከናውን በዚህ አዋጅ አማካኝነት ቋሚ የውክልና ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

### 40. የስያሜ ለውጥ

በአዋጅ ቁጥር 101/1996 ዓ.ም እና በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት የተቋቋመው የክልሉ አደጋ መከላከል ምግብ ዋስትና ፕሮግራምና ልዩ ድጋፍ የሚሹ አካባቢዎች ማስተባበሪያ ኮሚሽን፣ በአዋጅ ቁጥር 221/2007 ዓ.ም የተቋቋመው የአመራር አካዳሚ እና በአዋጅ ቁጥር 234/2008 ዓ.ም የተቋቋመው የክልሉ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ኮሚሽን፣ በአዋጅ ቁጥር 236/2008 ዓ.ም የተቋቋመው የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ድጋፍና ክትትል ባለሥልጣን፣ በደንብ ቁጥር 120/2006 የተቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ፣ በአዋጅ ቁጥር 160/2001 ዓ.ም የተቋቋመው የአማራ ሕዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ጽሕፈት ቤት እንደ ቅደም-ተከተላቸው በዚህ አዋጅ መሠረት ከዚህ በታች የተመለከተው የስያሜ ለውጥ ተደርጎባቸዋል፡-



# PART FIVE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 39. Organizing Executive Bodies

In addition to making changes based on research regarding the organization of the executive bodies of the region, the regional administrative council has given permanent deligative power to establish new institutions, determine their duties and responsibilities, merge one with another, as well as to remove from their position in accordance with law;

### 40. Change of Nomenclature

The Regional Disaster Prevention, Food Security Program and Special Needs Coordination Commission established in accordance with Proclamation No. 101/2004 and Proclamation No. 264/2019, the Leadership Academy established in Proclamation No. 221/2015 and the Regional Science, Technology and Information Communuication Commission established in Proclamation No. 234/2016, the Public Development Enterprises Support and Monitoring Authority established in Proclamation No. 236/2016, the Vital Events Registration Agency established in Regulation No.120/2014, and the Amhara People's Martyrs' Monument office established in Proclamation No. 160/2019 respectively have been renamed in accordance with this Proclamation;

1) የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን፤
2) የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፤
3) የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን፤
4) የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር፤
5) የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አገልግሎት፤
6) የአማራ ሕዝብ ዝክረ-ታሪክ ማዕከል፡፡

## 41. ስለ ተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

1) በሥራ ላይ ያለው የክልሉ አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም (እንደተሻሻለ) ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡

2) የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

ሀ) የክልሉን ጠቅላይ አቃቤ-ሕግ መሥሪያ ቤት ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 263/2011 ዓ.ም፤

ለ) የክልሉን ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 265/2011ዓ.ም፤

ሐ) የክልሉን ስፖርት ኮሚሽን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 266/2011 ዓ.ም፤

መ) የአካባቢ፣ የደንና የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 232/2008 ዓ.ም፤

ሠ) የክልሉን ማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 238/2008 ዓ.ም፤



1) The Disaster Prevention and Food Security Commission;
2) The Management Institute;
3) The Science and Technology Commission;
4) The Public Development Enterprises Administration;
5) The Vital Events Registration Service;
6) The Amhara Peoples History-Memorial Center.

## 41. Repealed and Inapplicable Laws

1) The Existing Regional Executive Bodies Establishement and Determination of their Powers and Duties Proclamation No. 264/2018 (as amended) has been repealed and replaced by this proclamation:

2) The following laws are repealed by this proclamation:

A) Proclamation No. 263/2019 Issued to Establish the Regional Office of the Attorney General;

B) Proclamation No. 265/2019 Issued to Establish the Regional Civil Service Commission;

C) Proclamation No. 266/2019 Issued to Establish the Regional Sports Commission;

D) Proclamation No. 232/2016 Issued to Establish the Environment, Forest and Wildlife Conservation Authority;

**E)** Proclamation No. 238/2016 Issued to Establish the Regional Mineral Resources Development Promotion Agency;

ረ) የክልሉን መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ለማቋቋም የወጣው ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 18፭/2011 ዓ.ም፡፡

3) ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 42. መብቶችና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት፡-

ሀ) መሬትን በተመለከተ ለክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ እንዲሁም ለክልሉ ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮዎች ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት እንደየአግባብነታቸው በዚህ አዋጅ አዲስ ወደ ተቋቋመውየመሬት ቢሮ እንዲሁም ለከተሞችና መሠረተ ልማት ቢሮዎች ተላልፈዋል፤

ለ) የመስኖ ልማት ጉዳዮችን በተመለከተ ለክልሉ ግብርና፣ እንዲሁም ለክልሉ ውኃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮዎች ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ወደተቋቋመው የክልሉ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤



F) Regional Administrative council Proclamation No. 18፭/2019 Issued to Establish the Regional State Communication Affairs Office;

3) Any law, regulation, directive or customary practice contrary to this Proclamation shall not apply to the matters covered by this Proclamation.

## 42. Transfer of Rights and Obligations

Pursuant to Proclamation No. 264/2018:

A) The rights and obligations vested to the Regional Rural Land Administration and Use as well as to theUrban Development, Housing and Construction Bureaus concerning land are transferred to of the State have been transferred to the newly established Land and to the Urbans and Infrastructure Bureaus in their respective appropriateness in accordance with the powers vested in them by this Proclamation;

B) The rights and obligations given to the Regional Agriculture, as well as to the Regional Water, Irrigation and Energy Development Bureaus regarding Irrigation Development issues have been transferred to the newly established Regional Irrigation and Lowland Development Bureau;

ሐ) በአዋጅ ቁጥር 238/2008 ዓ.ም ለክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤

መ) በአዋጅ ቁጥር 263/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ጠቅላይ አቃቤ-ሕግ መሥሪያ ቤት ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ፍትሕ ቢሮ ተላልፈዋል፤

ሠ) በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ገንዘብ ቢሮ ተላልፈዋል፤

ረ) መንገድን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ወደ ተቋቋመው ወደክልሉ መንገድ ቢሮ ተላልፈዋል፤

ሰ) በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች እንደየ አግባብነታቸው በዚህ አዋጅ ወደ ተቋቋሙት የሥራና ሥልጠና ቢሮ እንዲሁም ወደ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳዮች ቢሮ ተላልፈዋል፤



C) The rights and obligations granted to th Regional Minerals Development Promotio Agency under Proclamation No. 238/2016 hav been transferred to the newly establishe Regional Mineral Development Bureau in thi Proclamation;

D) The rights and obligations vested in th Regional Prosecutor General Office i accordance with Proclamation No. 263/201 have been transferred to the newly establishe Regional Justice Bureau in this Proclamation;

E) The rights and obligations vested i Proclamation No. 264/2019 to the Bureau c Finance and Economic Cooperation have bee transferred to the Regional Finance Burea established by this Proclamation;

F) The rights and obligations granted to th Regional Road and Transport Bureau i accordance with Proclamation No. 264/201 regarding Road have been transferred to th newly established Regional Road Bureau und this Proclamation;

G) The rights and obligations granted to th Regional Bureau of Labor and Social Affairs i accordance with Proclamation No. 264/201 have been transferred to the Bureau of Lab and Training as well as to the Bureau c Women, Children and Social Affairsin the respective establishment by this Proclamation;

ሸ) በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ሥራና ሥልጠና ቢሮ ተላልፈዋል፤

ቀ) በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ሰላምና ደኅንነት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ወደ ተቋቋመው የክልሉ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ተላልፈዋል፤

በ) ሴቶችና ሕፃናትን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተላልፈዋል፤

ተ) ወጣቶችን አስመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ፣ እንዲሁም ስፖርትን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 266/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ስፖርት ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ተላልፈዋል፤

H) The rights and obligations given to the Regional Technic, Vocational and Enterprise Development Bureau in accordance with Proclamation No. 264/2019 have been transferred to the newly established Regional Work and Training Bureau in this Proclamation;

I) The rights and obligations granted to the Regional Peace and Security Bureau in accordance with Proclamation No. 264/2019 have been transferred to the newly established Regional Peace and Security Bureau established in accordance with this Proclamation;

J) The rights and obligations given to the Regional Women, Children and Youths Affairs Bureau in accordance with Proclamation No. 264/2019 regarding women and children have been transferred to the newly established Regional Women, Children and Social Affairs Bureau in accordance with this Proclamation;

K) The rights and obligations given to the Regional Women, Children and Youths Affairs in accordance with Proclamation No. 264/2019 concerning Youths, and to the Regional Sport Commission in accordance with Proclamation No. 266/2019 concerning Sports have been transferred to the newly established Regional Youths and Sport Affairs Bureau pursuant to this Proclamation;

ቸ) በአዋጅ ቁጥር 265/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን ተላልፈዋል፤

ኀ) በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ ፕላን ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤

ነ) በደንብ ቁጥር 181/2011 ዓ.ም መሠረት ለክልሉ መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ተላልፈዋል፤

ኘ) በአዋጅ ቁጥር 232/2008 ዓ.ም መሰረት ለክልሉ አካባቢ፣ ደንና ዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ እንደገና ወደ ተቋቋመው የክልሉ አካባቢና ደን ጥበቃ ባለሥልጣን ተላልፈዋል።

L) The rights and obligations granted to th Regional Civil Service Commission i accordance with Proclamation No. 265/201 have been transferred to the newly establishe Regional Civil Service and Human Resourc Development Commission;

M) The rights and obligations given to th Regional Planning Commission in accordanc with Proclamation No. 264/2019 have bee transferred to the newly established Regiona Planning and Development Bureau i accordance with this Proclamation;

N) The rights and obligations granted to th Regional Government Communication Affair Office in accordance with Regulation No 181/2019 have been transferred to the newl established Regional Governmen Communication Affairs Bureau in accordanc with this Proclamation;

O) The rights and obligations granted to th Regional Environment, Forest and Wildlif Conservation and Development Authority i accordance with Proclamation No. 232/201 have been transferred to the re-establishe Regional Environment and Forest Protectio Authority by this Proclamation.

## 43. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም መሠረት ተቋቁመው የነበሩና በዚህ አዋጅ መሠረት እንዳዲስ ወደ ተደራጁት የክልሉ አስፈጻሚ አካላት ያልተጠቃለሉ የሥራ ዘርፎች በሌሎች ሕጎች ወደፊት በሚቋቋሙ አዳዲስ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች እስከሚያዙ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት በተደራጁትና ለሥራው ቀደምት ባለቤቶች በነበሩት ተቋማት አማካኝነት መከናወናቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ሆኖም አዋጁ በክልሉ ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከ3 ወር በኋላ የዚህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይቋረጣል፡፡

## 44. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ሙሉ ተፈጻሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 45. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሰ) ድንጋጌ ሥር ለክልሉ አስፈጻሚ አካላት የተሰጠው የወል ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ-መስተዳድሩ ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 46. አዋጁ ስለሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ባሕር ዳር**

**ጥር 15 2014 ዓ.ም**

**ይልቃል ከፋለ (ዶ/ር)**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚደንት**



## 43. Transitory Provisions

Sectors previously established under Proclamation No. 264/2019 andare not included in the newly reorganized Executive Bodies of the Region in accordance with this Proclamation shall continue to be carried out under institutions which are organized in this Proclamation and original owners until they are incorporated under other new executive offices to be established in the future.However, the applicability of this provision shall be terminated after three months since the publication of the proclamation by regional Zikre Hig Gazette.

## 44. Power to Issue Regulation

The Regional Administrative Council may issue regulations requiring to the full implementation provisions of this Proclamation.

## 45. Power to Issue Directive

Without prejudice to the common power vested in the Executive Bodies of the Region under the provisions of Article 11, Sub-article 1 Number (G) of this Proclamation, the Head of Govrnment may issue detailed Directives for the full implementation of this Proclamation Regulations to be issued on basis of the proclamation.

## 46. Effective Date of the Proclamation

This Proclamation shall come into force as of its publication on the Zikre Hig Gazette of the regional state.

**Done at Bahir Dar,**

**This 23th Day of January, 2021.**

**Yilkal Kefale (PhD)**

**President of the Amhara National Regional State.**